# ምእራፍ ፡ ፳፫

## ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ መስቀል ፡

ስብለ ፡ ወንጌል ፡ ከታሰረችበት ፡ ባስረኛው ፡ ቀን ፡ እስከትፈታ ፡ ድረስ ፡ አባትዋም ፡ እግራቸው ፡ በግር ፡ ብረት ፡ ውስጥ ፡ አይግባ ፡ እንጅ ፡ እንደሷ ፡ እስረኛ ፡ ሆነው ፡ ሰነበቱ ።

የጅዋ ፡ መታሰር ፡ በመብልና ፡ በመጠጥ ፡ ልብስ ፡ በመልበስም ፡ ጊዜ ፡ ችግር ፡ ስለፈጠረ ፡ ወዲያውም ፡ እሳቸው ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ ካጠገብዋ ፡ የማይለዩ ፡ በመሆናቸው ፡ የማያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ ስለተገኘ ፡ በታሰረች ፡ ማግስት ፡ እጅዋን ፡ እንድትፈታ ፡ ተደረገ ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለት ፡ ወይም ፡ ሹልነት ፡ ያለው ፡ ብረትም ፡ ሆነ ፡ እንጨት ፡ ባጠገብዋ ፡ እንዳይደርስ ፡ የምትበላውንም ፡ ሆነ ፡ የምትጠጣውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ በሳቸው ፡ ፊት ፡ አቅራቢዎቹ ፡ ሳይቀምሱት ፡ ለስዋ ፡ እንዳይቀርብላት ፡ አጥብቀው ፡ ይጠነቀቁ ፡ ነበር ።

ፊታውራሪ ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ልጃቸውን ፡ ሲጠብቁ ፡ ፊትዋ ፡ ህይወት ፡ እንደሌለው ፡ ጥሩ ፡ ምስል ፡ ፍዝዝ ፡ ብሎ ፡ አይኖችዋ ፡ ቡዝዝ ፡ ብለው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተተክለው ፡ ይቆዩና ፡ ድንገት ፡ እንባዋ ፡ በጉንጭዋ ፡ ያወጣውን ፡ መንገድ ፡ ተከትሎ ፡ ሲሄድ ፡ የማያቋርጥ ፡ ሳግ ፡ ሲተናነቃት ፡ ያዩና ፡-
"ወይ ፡ እኔ ፡ መሸሻ ! ይህ ፡ አጥማጅ ፡ ይህ ፡ አስማተኛ ፡ ተማሪ ፡ በልጄ ፡ ተጫወተባት ! ምነው ፡ ጌታየ ! ላንድ ፡ አፍታ ፡ በጄ ፡ ጥለኸው ፡ በልጄ ፡ እንደተጫወተ ፡ ጀርባውን ፡ የዝንብ ፡ መጫወቻ ፡ ባደርገው ! ሌላ ፡ ምንም ፡ አልለምንህም ! ይህን ፡ ብቻ ፡ ጌታየ ! ይህን ፡ ብቻ ፡ አድርግልኝ !" ይላሉ ፡ በብርቱ ፡ ስሜት ፡ አይኖቻቸውን ፡ እግዚአብሄር ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንስተው ። ነገር ፡ ግን ፡ ፈረሰኞች ፡ የማንኩሳን ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ የደብረ ፡ ወርቅንና ፡ የሲናዳን ፡ መንገድ ፡ እየተከተሉ ፡ እግረኞች ፡ ዲማ ፡ ውስጥ ፡ የበዛብህ ፡



ወዳጆች ፡ ናቸው ፡ የሚባሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ቤት ፡ በዩም ከናያቱ ፡ እዩገቡ ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ በዛብህን ፡ ፈልገው ፡ ስላጡት ፡ እንደማይገኝ ፡ ተስፋ ፡ ተቆርጦ ፡ ፊታውራሪ ፡ መፍትሄ ፡ ጸርና ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ የሚያውቅ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በምስጢር ፡ ተፈልጎ ፡ ቢገኝ ፡ የጠዩቀውን ፡ ዋጋ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብለው ፡ ያስፈልጉ ፡ ጀመር ።

በዛብህ ፡ በበኩሉ ፡ የፍቅርና ፡ የፍራት ፡ እስረኛ ፡ ሆኖ ፡ እጉዱ ፡ ካሳ ፡ ቤት ፡ ተሸሽጎ ፡ በስብለ ፡ የደረሰው ፡ ከሰማው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጎልቶ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በርክቶ ፡ እዩታዩው ፡ ነጻ ፡ ሳለች ፡ የነበረችውና ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሆነችው ፡ እዩተለዋወጠ ፡ እዩታዩው ፡ የሚበላው ፡ ባፉ ፡ እየተንከራተተ ፡ አይዋጥለት ፡ ቢተኛ ፡ እንቅልፍ ፡ አይወስደው ፡ እያደር ፡ እንደ ፡ ቀረፈቱት ፡ ዛፍ ፡ እዩጠወለገና ፡ እዩደረቀ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

"ያሰሩዋት ፡ እኔን ፡ አስማት ፡ አድርጎባታል ፡ ብለው ፡ ከሆነና ፡ እኔ ፡ ሄጄ ፡ ፈታሁ ፡ ካላልሁ ፡ የማይፈትዋት ፡ ከሆነ ፡ አሁን ፡ ብሄድና --- ነአኩተከን ፡ ወይም --- ጸሎተ ፡ ሃይማኖትን ፡ ደግሜ ፡ ፈትቻታለሁ ፡ ብል ፡ ምናለ ? መቸም ፡ ፄም ደግመውን ፡ እያሰማሁ ፡ ድገም ፡ አይሉኝ !" አለ ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ ጋር ፡ ይህኑ ፡ ነገር ፡ አንስተው ፡ ሲወያዩ ።

"ነገሩ ፡ በዚህ ፡ ብቻማ ፡ የሚያልቅ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ ያስቸግር ፡ ኖሮዋል ?"

"ታዲያ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ይኖራል ?"

"ምነው ፡ ነግሬህ ፡ የለም ? እገርፈዋለሁ ፡ ብለውኮ ፡ ነው ፡ የሚፈክሩ ! ደግሞ ፡ ካገኙህ ፡ እንደ ፡ ፈከሩት ፡ ማድረጋቸው ፡ አይቀርም ፡ ባለጌ ፡ ናቸው !"

"ታዲያ ፡ ይግረፉኝ ፡ እንጂ ፡ ምናለ ! እሷ ፡ ታስራ ፡ ከምትሰቀይ ፡ ይግረፉኝ ! ነገ ፡ የሚድን ፡ ቁስል ፡ አይደል ?"

"አዎ ፡ የተገረፈ ፡ ጀርባ ፡ ቶሎ ፡ ይድን ፡ ይሆናል ፡ የተሰበረ ፡ ልብ ፡ ግን ፡ እንጃ !"

"እንዴት ?"

"ስትገረፍ ፡ አይታ ፡ ወይም ፡ መገረፍህን ፡ ሰምታ ፡ ሰው ፡ የምትሆን ፡ ይመስልሀል ? ባትሞት ፡ ልብዋ ፡ እንደ ፡

ተሰበረ ፡ ይቀራል ። ለምን ፡ ሰደቡት ፡ ብላ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ያለቀሰች ፡ ያን ፡ ያክል ፡ የምትሆነውን ፡ ያጣች ፡ መገረፍ ህን ፡ ያዩች ፡ ወይም የሰማች እንደሆነ ፡ ሰው ፡ እንደማትሆን ፡ አውቃለሁ ። ስለዚህ ፡ ከምትሞት ፡ ወይም ፡ ልብ ፡ የሚሰብር ፡ አዘን ፡ ከሚደርስባት ፡ ታስሩ ፡ ብትቆይ ፡ ይሻላል ። ወዲያውስ ፡ ስንት ፡ ቀን ፡ አስረው ፡ ያኖርዎት ፡ መሰለህ ? አሁን ፡ ይፈትዎታል !”

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሲናገር ፡ በተብህ ፡ እንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ እዬሰማ ፡ እንባው ፡ ፊቱን ፡ ሳይነካ ፡ እመሬት ፡ ላይ ፡ ይንጠባጠብ ፡ ነበር ።

እውነትም ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንዳለው ፡ መፍትሄ ፡ ጸርና ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ የሚያውቁ ፡ ሰው ፡ እዚያው ፡ ዲማ ፡ ተገኝተው ፡ መፍትሄውን ፡ ስላደረጉላት ፡ ሰብለ ፡ በታሰረች ፡ ባስረኛው ፡ ቀን ፡ ተፈታች ።

“ ጌቶች ! አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለብቻ ፡ ባነጋግርዎ ፡ እወድ ፡ ነበር ፡ ” አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ፊታውራሪ ፡ እልፍኛቸው ፡ እሰብለ ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጠው ፡ ዳዊት ፡ በሚደግሙበት ፡ በችኮላ ፡ ገብተው ።

“ ወዬው ፡ ጉድ ! ምን ፡ እንደማደርግ ፡ አያዩም ? ዳዊቴን ፡ አቋርጨ ፡ ነው ፡ እስዎን ፡ የማነጋግር ?”

“ ግዴለም ፡ ያቋርጡት ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ነው ! ”

ከዚያ ፡ ፊታውራሪ ፡ የንስሀ ፡ አባታቸው ፡ እሳቸውን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ካልያዙ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ እንደማይደፍሩ ፡ ስለሚያውቁ ፡ ያባ ፡ ሞገሴን ፡ ቃል ፡ ለማክበር ፡ ሳይሆን ፡ ወሬያቸውን ፡ ለመስማት ፡ በመቸኮል ፡ ዳዊታቸውን ፡ አጥፈው ፡ በሩን ፡ ወጣ ፡ እሉና ፡ ሰብለን ፡ ለማየት ፡ በሚችሉበት ፡ ቦታ ፡ ሄደው ፡ ቆሙ ።

“ የምስራች ! ” አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ሰብለ ፡ እንዳትሰማ ፡ ድምጻቸውን ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ።

“ ምስር ፡ ይብሉ ! ምንድነው ? ”



“መፍትሄ ፡ ጸርና ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ የሚያውቁ ፡ ሰው ፡ እዚሁ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ ተገኙ ። ”

“ የት ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፊታቸው ፡ ሁሉ ፡ በቅጽበት ፡ ተለውጦ ። ከደስታቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ ፈገግ ፡ እንዳሉ ፡ ከንፈሮቻቸውና ፡ ጉንጮቻቸው ፡ ሲንቀጠቀጡ ፡ አይናቻቸው ፡ እንባ ፡ ሲሞሉ ፡ ይታዩ ፡ ነበር ።

“ እዚሁ ፡ ዲማ ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ የሚኖሩ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ የሚባሉ ፡ መነኩሴ ፡ ናቸው ። ”

“ መቼ ፡ የመጡ ፡ ናቸው ? ”

“እ —ከመጡስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜያቸው ፡ ነው ! ብቻ ፡ ከመቃብር ፡ ቤታቸው ፡ አይወጡም ፡ አንዳንድ ፡ ምክር ፡ ሊጠይቁዋቸው ፡ ከሚሄዱ ፡ ወዳጆቻቸው ፡ በቀር ፡ ከብዙ ፡ ሰውም ፡ አይገናኙ ። ”

“ ታዲያ ፡ እስዎ ፡ እንዴት ፡ አወቁዋቸው ? ደግሞስ ----- እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰው ፡ ከሆኑ ፡ ይህን ፡ ነገር ---ደህና ፡ አድርገው ፡ የሚያውቁ ፡ ይመስልዎታል ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መጠራጠር ፡ እሉና ።

“ እኔማ ፡ በዬጊዜው ፡ እዬሄድሁ ፡ መንፈሳዊ ፡ ምክር ፡ ስለምጠይቃቸው ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ አውቃቸዋለሁ ። ይህ ፡ ነገር ፡ ከደረሰብን ፡ ወዲህ ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ የማይነገር ፡ ስለሆነ ፡ እስቲ ፡ እግዚአብሄር ፡ ከኛ ፡ ለሳቸው ፡ ቅርብ ፡ ነውና ፡ ጸሎት ፡ አድርገው ፡ የሚገልጽላቸውን ፡ መንገድ ፡ ያሳዩን ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ ሄጀ ፡ በምስጢር ፡ ባዋያቸው ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ላደርገው ፡ እችላለሁ ፡ ” አሉኝ ።

“ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ዘርዝረው ፡ ነግረዋቸው ፡ አውቃለሁ ፡ አሉ ? ”

“ አዎ ፡ ለማንም ፡ የሚነገር ፡ አለመሆኑን ፡ ጭምር ፡ አደራ ፡ ብዬ ፡ ነግሬያቸው ፡ ለሁሉም ፡ ግዴለም ፡ ብለውኛል ። ”

“እንግዲህ ፡ ማታ ፡ ያምጡዋቸውና ፡ ለብቻ ፡ ላነጋግራቸው ። ”

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ልደታቸው ፡ በወሊጋ ፡ ውስጥ ፡

ትድሩ ፡ በሚባል ፡ ክፍል ፡ ነው ። በልጅነታቸው ፡ በዘር ፡ መዝሪያ ፡ አካላቸው ፡ አደጋ ፡ ደርሶባቸው ፡ ወዲያው ፡ ቁስሉ ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ ከዘመዶቻቸው ፡ ኮብልለው ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ ተሻግረው ፡ ካንዱ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ንባብና ፡ ዜማ ፡ ከዚያም ፡ ትንሽ ፡ ቅኔ ፡ ከተማሩ ፡ በሁዋላ ፡ መንኩሰው ፡ ከጎጃም ፡ አድባራትና ፡ ገዳማት ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ አመት ፡ ያልተቀመጡበት ፡ አይገኝም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዲማ ፡ ከተቀመጡ ፡ አንድ ፡ አመት ፡ አልፎዋቸዋል ። በደረሰባቸው ፡ አደጋ ፡ ምክናያትም ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ከፍጥረታቸው ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ከመጨመር ፡ ብቸኝነትን ፡ ከመናገር ፡ መስማትን ፡ የሚመርጡ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ። ብዙ ፡ ሰምተው ፡ ትንሽ ፡ የተናገሩ ፡ እንደሆነም ፡ ያን ፡ ትንሹን ፡ ሳይጨርሱ ፡ ወዝፈው ፡ ስለሚተውት ፡ በብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ የሚተረጎም ፡ ይሆንና ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ “ አባ ፡ ተክለሀይማኖትማ ፡ ብለው ፡ ነበር ፡ ” የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ባለመጥፋቱ ፡ አዋቂ ፡ ባህታዊ ፡ ይባላሉ ። “ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖትን ፡ ለማናገር ፡ ቀጥሎም ፡ የተናገሩትን ፡ ለማስተዋል ፡ ከተቻለ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ቃላቸው ፡ እመሬት ፡ ጠብ ፡ አይልም ። ” ይባላል ።

ስለዚህ ፡ እንደሳቸው ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ በጸሎት ፡ ለተጠመዱ ፡ ምእመናን ፡ ከቤተክርስቲያን ፡ ከሚላክላቸው ፡ መሀራ ፡ ሌላ ፡ በመልክም ፡ በወሬም ፡ የሚያውቁዋቸው ፡ ሰዎች ፡ “ አደራችሁን ፡ ” እያሉ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ ልብስም ፡ ገንዘብም ፡ እየላኩላቸው ፡ ደህና ፡ ይቀመጣሉ ።

ነገር ፡ ግን ፡ አዘውትረው ፡ የሚለብሱት ፡ ደበሎ ፡ ስለሆነ ፡ ሰው ፡ የሚሰጣቸውን ፡ ጋቢም ፡ ሆነ ፡ ኩታ ፡ መልሰው ፡ ልብስ ፡ ለሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ይሰጡታል ። እንዲሁም ፡ ገንዘብና ፡ መጠጥ ፡ ሲሰጡ ፡ አይታዩም ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ከሚልክላቸው ፡ ምግብ ፡ የሚበልጠውን ፡ መሸት ፡ ሲል ፡ ተሸክመው ፡ ወስደው ፡ ደጀሰላምና ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ለወደቁ ፡ ድሆችና ፡ በሽተኞች ፡ እየዞሩ ፡ ይመጸውታሉ ። ታዲያ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያዩ ፡ ስለሚያወሩ ፡ ተመጽውተው ፡ መመጽወታቸውም ፡ የሚመጸውቱበት ፡ ሁኔታም ፡ ለት



ልቅ ፡ ጻድቅነታቸው ፡ ተጨማሪ ፡ ምስክር ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠርላቸው ፡ ነበር ።

ፊታውራሪ ፡ አባ ፡ ሞገሴንና ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖትን ፡ በቀጠሩበት ፡ ማታ ፡ ከራት ፡ በሁዋላ ፡ ምሽታቸውን ፡ ከሰብለ ፡ ጋር ፡ አስቀምጠው ፡ “ ስእል ፡ ቤት ፡ ” በሚሉዋት ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ ብቻቸውን ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጠብቁ ፡ የንስሀ ፡ አባታቸው ፡ እንግዳውን ፡ ይዘው ፡ ደረሱ ።

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ እንደሳቸው ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ እንደ ፡ ደረሰባቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ዘለግ ፡ ብለው ፡ ከትከሻቸው ፡ ትንሽ ፡ ሰገደድ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። ልብሳቸውም ፡ ቆባቸውም ፡ ደበሎ ፡ ነው ።

ከርዝመታቸውና ፡ ከቅጥነታቸው ፡ የተነሳ ፡ የለበሱት ፡ ደበሎ ፡ በረዥም ፡ መስቀያ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተንጠለጠለ ፡ ሁሉ ፡ ከጉልበታቸው ፡ በታች ፡ ረዥም ፡ ቅልጥማቸውን ፡ ራቁት ፡ አድርጎ ፡ ባሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ የተጠቀለለ ፡ ነገር ፡ በሁለት ፡ እጆቻቸው ፡ ቀደም ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡ ፊታውራሪን ፡ ምህረት ፡ እንደሚለምኑ ፡ ሁሉ ፡ አንገታቸውን ፡ ቀልሰው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ሳይተነፍሱ ፡ እፊታቸው ፡ ቆሙ ። ሲገቡ ፡ ሰላምታ ፡ እንኩዋ ፡ ባለመስጠታቸው ፡ ፊታውራሪ ፡ ገርሞዋቸው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ አይናቸውን ፡ ፍጥጥ ፡ አድርገው ፡ ይመለከቱዋቸው ፡ ጀመር ።

“ጌቶች ! አባቴ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ እሳቸው ፡ ናቸው ።” አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ የተፈጠረውን ፡ ሁኔታ ፡ ሲያዩ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሸበር ፡ አሉና ።

“ እህ ---- እሳቸው ፡ ናቸው ? እንደምን ፡ ነዎ ፡ አባቴ ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ። አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ አንገታቸውን ፡ ከደፉበት ፡ አሁንም ፡ ትንሽ ፡ ዝቅ ፡ አደረጉ ፡ ሰላምታውን ፡ ለመመለስ ።

“ ይምጡ ፡ እዚህ ፡ ይቀመጡ ! ” አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ መቀመጫ ፡ ላባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ እያሳዩ ፡ አባ ፡ ሞገሴን ፡ እውጭ ፡ ቆመው ፡ ሰው ፡ ሲመጣ ፡ እንዲከለክሉ ፡ አዘዙዋ

ቸው ።

" የደረሰብኝን ፡ ችግር ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ነግረዎዎታል ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ።

" አ -- አዎ ! "

" ታዲያ ፡ ይሆንልዎታል ? "

" ለግዚአብሄር ----- የማይሆን ፡ አለ ? "

" ለግዚአብሄርማ ፡ ምን ፡ የማይሆን ፡ አለ ! አዩ ? ለልጄ ፡ መፍትሄ ፡ ጸርና ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ እንዲያደርጉላት ፡ ነው ፡ ያስመጣሁዎ ! ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ከዛሬ ፡ ቀደም ፡ አድርገዋል ፡ ወይ ፡ ማለቴ ፡ ነው ! "

" እኔስ --- እሱን ፡ ማለቴ ፡ አይደል ! "

" ድጋም ፡ ነው ? ወይስ ፡ ምንድነው ፡ የሚያደርጉላት ? "

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ለተጠዩቁት ፡ ጥያቄ ፡ የቃል ፡ መልስ ፡ በመስጠት ፡ ፈንታ ፡ ባሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ ጠቅለው ፡ የያዙትን ፡ ነገር ፡ ገልጠው ፡ ለፊታውራሪ ፡ አሳዩዋቸው ።

" እእ --- መስቀል ! ታዲያ ፡ በመስቀሉ ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ? "

"በሰው ፡ እጅ ፡ የተሰራ - - - - መስቀል ፡ አይደለም ።

"ታዲያስ ? "

" አስራ ፡ አምስት ፡ ቀንና ----- አስራ ፡ አምስት ፡ ሌሊት ፡ ባንድ ፡ እግሬ ፡ ቆሜ ፡ ስጸልይ ፡ የተሸለምሁት ፡ ነው ፡ በአቃቤ ፡ ስራይ ፡ በጸላኤ ፡ ሰናይ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ስልጣን ፡ ያለው ፡ ነው ! "

"ከማን ፡ ነው ፡ የተሸለሙት ? "

" ጸሎቱ ፡ ላረገለት ፡ ፍጡር ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ ሸላሚ ፡ አለ? "

" ከእግዚአብሄር ፡ የወረደልዎ ፡ መስቀል ፡ ነው ? "

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆዩና ፡ " አለመጠርጠር ፡ ነው ፡ ምንም ፡ የሚያስቸግር ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ነገሩ ---- ቀላል ፡ ነው ። ነገ ፡ ማታ ----እዚሁ ፡ ቦታ ፡ ልጅቱን ፡ ብቻዋን ፡ ላገኛት ! " ብለው ፡ ለመሄድ ፡ ተነሱ ።



" ይቆዩ ፡ መጠጥ ፡ ጠጥተው ፡ ይሂዱ ፡ አባቴ ! " አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

" አይደለም ፡ ይቆዩኝ ፡ "

ፊታውራሪ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖትን ፡ አሰናብተው ፡ ወደልፍኛቸው ፡ ተመልሰው ፡ የተነጋገሩትን ፡ ሁሉና ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ መስቀል ፡ ማየታቸውን ፡ ለሰብለ ፡ ሲነግሩዋት ፡--- ደብተሮችና ፡ አንዳንድ ፡ አዋቂዎች ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ አታላዮች ፡ ብዙዎችን ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ ተቆራኝቶዋቸዋል ፡ ወይም ፡ አብነት ፡ ተደርጎባቸዋል ፡ እያሉ ፡ በማጥመቅ ፡ በመግረፍ ፡ ሰውነት ፡ በማቃጠል ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ደስ ፡ የማያሰኝ ፡ ነገር ፡ በማብላትም ፡ ሆነ ፡ በማጠጣት ፡ እንደሚያሰቃዩዋቸው ፡ በሰዋም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ እንዳይደርስባት ፡ ለጊዜው ፡ ፈራች ። ይህን ፡ ስታወጣ ፡ ስታወርድ ፡ ሌሊቱ ፡ እስኪገባደድ ፡ እንቅልፍ ፡ አጥታ ፡ ቆይታ ፡ በመጨረሻ ፡ ታስራ ፡ ከመቀመጥ ፡ የደረሰ ፡ ደርሶባት ፡ ከታሰረችበት ፡ መፈታት ፡ የሚሻል ፡ መሆኑን ፡ ወሰነች ። ይልቁንም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የታሰረችበት ፡ እግር ፡ ብረት ፡ በጨርቅ ፡ ቢጠቀለል ፡ እግሮችዋን ፡ ክፉኛ ፡ አቁስሎ ፡ በተቀመጠችበትም ፡ መንቀሳቀስ ፡ ስላቃታት ፡ ከግር ፡ ብረት ፡ እስክትገላገል ፡ ቸኮለች ።

በማግስቱ ፡ ማታ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ በተቀጠሩበት ፡ ጊዜ ፡ ሲመጡ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሰብለን ፡ ይዘው ፡ በእልፍኝ ፡ ቤት ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ።

" እንዴት ፡ዋሉ ፡ አባቴ ! እሰዎ ፡ እስኪመጡ ፡ ብቻዋን ፡ እንዳትሆን ፡ ብዬ ፡ ነው ፤ እዚህ - - - - የቆዩሁዎ ! ይበሉ ፡ እንግዴህ ፡ ሲጨርሱ ፡ ያጨብጭቡ ፡ እወዲያኛው ፡ ቤት ፡ እቆያለሁ ! " አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ ወጡ ። አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ሰብለን ፡ ትንሽ ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ አዩና ፡ እንደ ፡ ማፈር ፡ ብለው ፡ እንደገና ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ቆሙ ።

" ወዲህ ፡ ይም ጡ ፡ እንጂ ፡ አባቴ ፡ ይም ጡ ፡ እዚህ ፡ ይቀመጡ ! " አለች ፡ ሰብለ ፡ መቀመጫ ፡ በጅዋ ፡ እሳይታ ። አባ ፡ ተክለ ሀይማኖት ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ መስ

ቀላቸውን ፡ ከተጠቀለለበት ፡ አሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ ይፈቱ ፡ ጀመር ።

ከዚያ ፡ የብረት ፡ መስቀላቸውን ፡ በሁለት ፡ እጃቸው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይዘው ፡ ትንሽ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ እግሮቻቸውን ፡ ገጥመው ፡ ቆመው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ ይደግሙ ፡ ጀመር ። አፋቸው ፡ ሲንቀሳቀስ ፡ ከመታየት ፡ በቀር ፡ ድምጻቸው ፡ አይሰማም ። ይደግሙ ፡ ይደግሙና ፡ እፍፍ ፡ እፍፍ ፡ እያሉ ፡ አዩሩን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ በመስቀሉ ፡ ይቀዝፉታል ። እንዲህ ፡ ላይና ፡ ታች ፡ እያዩ ፡ ሲደግሙ ፤ እፍፍ ፡ እፍፍ ፡ እያሉ ፡ አዩሩን ፡ በመስቀል ፡ ሲቀዝፉ ፡ ደግሞ ፡ ሲደግሙ ፡ ደግሞ ፡ አዩሩን ፡ ሲቀዝፉ ፡ ብዙ ፡ ቆይተው ፡ በመጨረሻ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ ቀረብ ፡ አሉና ፡ ጎንበስ ፡ ብለው ፡ "መስቀሉን ፡ ሳሚ !" አሉ ። ሰብለ ፡ መስቀሉን ፡ ሳመች ።

" ተሳለሚው ! "

ሰብለ እንደ ፡ ታዘዘችው ፡ አደረገች ። ከዚያ ፡ መስቀሉን ፡ ገልብጠው ፡ ያዙና ፦ "በይ ፡ አፍሽን ፡ እመስቀሉ ፡ ላይ ፡ ግንባርሽን ፡ እመያዣው ፡ ላይ ፡ አሳርፊሽ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለሽ ፡ ቆይና ፡ በሁዋላ ፡ ለምጠይቅሽ ፡ ትመልሽልኛለሽ ፡"

አሁንም ፡ ሰብለ ፡ እንደ ፡ ታዘዘችው ፡ አደረገች ።

"አይንሽን ፡ ጨፍኚው !"

" እሺ ፡ "

" ምን ፡ ይታይሻል ? "

"ምንም ፡ አይታዩኝ "

" ምን ፡ ይሰማሻል ?

" ምንም ፡ አይሰማኝ ! "

" እስቲ ፡ አስቢና ፡ መጀመሪያ ፡ ባሳብሽ ፡ ውስጥ ፡ የሚመጣውን ፡ ንገሪኝ ! "

" እሺ ። "

" አሁን ፡ ባሳብሽ ፡ ምን ፡ መጣ ? "

"መስቀል ፡ ሀይልነ ፡ መስቀል ፡ ቤዛነ ፤ መስቀል ፡ ጽንዕነ ፤ መስቀል ፡ መድሀኒተ ፡ ነፍስነ ፡ የሚለው ፡ ንባብ ፡ ታሰበኝ ! "

" መልካም ! ሌላ ---- ምንም ፡ አልታሰበሽ ? "



"የለም ።"

"ይህን ፡ ሁሉ - - - - ችግር ፡ ያመጣብሽ ፡ ሰው ፡ አልታሰበሽም ?"

ሰብለ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ቆዩችና ፡ የ --- የለ --- የለም !" ስትል ።

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ መስቀሉን ፡ ይዘውላት ፡ እንዳጎነበሱ ፡ በጃቸው ፡ ለበብ ፡ ያለ ፡ ውሀ ፡ የፈሰሰባቸው ፡ መስሎ ፡ ተሰማቸውና ፡ እንደ ፡ መደንገጥ ፡ ብለው ፡ -- "እንግዴህ ፡ በቃ ፤ ቀና ፡ በይ ! "አሉ ።

ከዚያ ፡ አባ ፡ ተክሌ ፡ መስቀሉም ፡ እጃቸውም ፡ የታጠበበትን ፡ እንባ ፡ መስቀላቸውን ፡ በሚጠቀልሉበት ፡ አሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ ጠራርገው ፡ አድርቀው ፡ ሲያጨበጭቡ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቶሎ ፡ መጡ ።

"ለብቻዎ ፡ ላነጋገርዎና ፡ ልሂድ ! "አሉ ፡ መነኩሴው ።

ፊታውራሪ ፡ ሰብለን ፡ ደግፈው ፡ አስነስተው ፡ ወደልፍኛቸው ፡ ወስደው ፡ ከናትዋ ፡ ጋር ፡ ካስቀመጥዋት ፡ በሁዋላ ፡ ተመልሰው ፡ መጥተው ፡ እመደባቸው ፡ ላይ ፡ ሲቀመጡ ፡ "ይበሉ ፡ እንግዴህ ፡ ሁሉንም ፡ ይንገሩኝ ፡ አባቴ ! አደራዎ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዳይሰውሩኝ ! "አሉ ፡ በዛብህ ፡ ልጃቸውን ፡ ያቀራኛት ፡ ክፉ ፡ መንፈስና ፡ ያደረገባት ፡ አስማት ፡ ምን ፡ አይነት ፡ እንደነበረ ፡ ለማወቅ ፡ እጅግ ፡ ቸኩለው ።

"ከንግዲህ ፡ ----ምንም ፡ የሚያሰጋ ፡ ነገር ----የለም ! " አሉ ፡ አባ ፡ ተክሌ ፡ በጣም ፡ በለሰለሰ ፡ ድምጽ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ።

" ምን ፡ ኖሮዋል ፡ ለመሆኑ ? ጸላኤ ፡ ሰናይ ፡ ነው ? "

"የለም ፡ ጸላኤ ፡ ሰናይ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ - - - አይደለም ! "

"ታዲያስ ? "

"ብርቱ ፡ አስማት ፡ ብርቱ ፡ ድጋም ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ ያልተለመደና ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ ሊፈታ ፡ የማይቻል ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያስጠላ ፡ ድጋም ፡ ነበር ፦ ተፈታ ፡ አሁን ፡ የሚያሰጋ ፡ ነገር ---የለም ፡ "

"እንዴትኮ ---እዚህ ፡ አገር ፡ ያልተለመደ ፡ ከሆነ ፡--- እዚህ ፡ አገር ፡ ሊፈታ ፡ የማይቻል ፡--- ከሆነ ፡ እንዴት ፡ ነው ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በሻከረ ፡ ድምጽ ፡ ልቅሶ ፡ መጥቶባቸው ።

"ከየት ---እንደ ፡ ተማረው ፡ እንጃ ! ብቻ ፡ ለመፍታቱ ፡ ግን ፡---መቼም ፡ የመስቀሉ ፡ ስልጣን ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ባለመሆኑ ፡ የመስቀሉ ፡ ስልጣን ፡ ካጽናፍ ፡ እስካጽናፍ ፡ በመሆኑ ፡ የማይፈታው ፡ እስማት ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ ተፈታ ።"

"እዎ ፡ እግዚአብሄር ፡ ጥሎ ፡ አይጥለኝም ! እግዚአብሄር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ነው ፡ እግዚአብሄር ፡ ስላልጣለኝ ፡ ነው ፡ እስዎን ፡ የጣለልኝ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አይኖቻቸው ፡ እንባ ፡ ሞልተው ፡ የእግዚአብሄርን ፡ ስም ፡ ባነሱ ፡ ቁጥር ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ጣራው ፡ እያዩ ።

"እንግዲህ ፡---ልጅቱ ፡ ትፈታ ! ብቻ ፡ መጠንቀቅ ፡ ነው !"

"እንዴት ?"

"ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የደረሰው ፡ ነገርና ፡---የሰውዬው ፡ ስም ---በፊትዋ ፡ እንዳይነሳ ፡ ከሞዛ ፡ ፈዛዛው ፡---እዩተቀነሰ ፡ መንፈሳዊ ፡ ታሪክ ---እንዲተረክላት ፡ ማድረግ ፡ መልካም --- ነው ! "

"እዩ ፡ አባቴ ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ እሱም ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ እጅዋን ፡ ለምኖኝ ፡ ለመስጠት ፡ አስቤያለሁ ፡ ታዲያ --- ምን ፡ ይመስልዎታል ? "

"እሱማ ፡---ድንቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ! እስከዚያ ፡ ግን .----- እንዲህ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። "

"እስከ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ?"

"የሶስት ፡---ያራት ፡ ወር ፡ እድሜ ፡"

"ያን ፡ ያክልስ ፡ መስናዶውም ፡ ይፈጃል ! ታዲያ ----- ለዚህ ፡ አጭር ፡ ጊዜ --- እስዎ ፡ ባጠገብዋ ፡ ሆነው ፡ ቢመክሩዋትና ፡ አሁን ፡ እንዳሉት ፡----የሚስማማውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ታሪክ ፡ እዩመረጡ ፡ ቢተርኩላት ፡ ይመችዎታል ?"

"ምን ፡ ከፋኝ ፡ ነበር ! ነገር ፡ ግን ---- ለብዙ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ባለአደራ ፡ ስለሆንሁ ፡ ጸሎት ፡ እንዳይታጎልብኝና ፡ ደግሞ ----



ከምእመናን ፡ እዩተመጸወትሁ ፡ የምመጸውታቸው ፡ ድውያን ፡ እንዳይቸገሩብኝ ፡ ነው ፡ እንጂ !" አሉ ፡ አባ ፡ ለመስማት ፡ በሚያስቸግር ፡ ዝቅተኛ ፡ ድምጽ ።

"ጸሎትዎን ፡ ሲጨርሱ ፡ የሚሰጡዎት ፡ ምክር ፡ ይበቃል ! ለምጽዋቱ ፡ ግን ፡ ጭራሽ ፡ አያስቡ ፡ እህል ፡ ውሀም ፡ ይሁን ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈልጉትን ፡ ያክል ፡ እንሰጥዎታለን ! ልጄ ፡ ደህና ፡ ሆና ፡ ያባት ፡ ወግ ፡ ከደረሰኝ ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ገንዘብ ፡ ቆጥቤ ፡ የማደርገው ፡ ነገር ፡ የለም ! እንኩዋን ፡ ዛሬ ፡ ድሮም ፡ ገንዘብ ፡ ቆጣቢ ፡ አይደለሁም ።"

"እስቲ ፡ ጸሎት ፡ አድርጌ ፡---የእግዚአብሄርን ፡ ፈቃድ ፡ ልጠይቅና ፡---መልሱን ፡ ነገ ፡ አባቴ ፡ ሞገሴ ፡ መጥተው ፡ ልንገራቸው ። "

"መልካም ! እንግዲህ ፡ መጠጥ ፡ ጠጥተው ፡ ይሂዱ ! የድካምዎንም ፡ አሁን ፡ እሰጥዎታለሁ ! "አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ ገንዘብም ፡ መጠጥም ፡ ለመስጠት ፡ መነኩሴውን ፡ ይዘው ፡ ወደልፍኝ ፡ ለመሄድ ፡ ሲነሱ ፡--- "መጠጡ ፡ ነው ፡ እንጂ --- ገንዘቡ ፡ ለኔ ፡ አይደለም ፡ አሁን ፡ ወስጄ ---ለተቸገሩ ፡ ድሆች ፡ የምመጸውተው ፡ ነው ፡ የምመጸውተውም ፡ ስለራሴ ፡----- አይደለም ፡ ስለመጸወቱኝ ፡ ሰዎች ---ነው ! "አሉ ፡ አባ ፡ ተክሌ ።

" ነው ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ ነው ! እስዎማ ፡ ምን ፡ ሀጢአት ፡ኖሮብዎ ፡ ይመጸውታሉ ! ስለኛ ፡ ስለሁላችን ፡ ነው ! "

በበነጋው ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ መጥተው ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ጸሎት ፡ አድርገው ፡ ፊታውራሪ ፡ የጠየቁትን ፡ ለመፈጸም ፡ የተፈቀደላቸው ፡ መሆኑን ፡ አስታወቁ ።

የሰብለን ፡ መፈታት ፡ እስከ ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ጉዱ ፡ ካሳም ፡ በዛብህም ፡ አያውቁም ፡ ነበር ። ከታሰረች ፡ጀምሮ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንኩዋን ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቤት ፡ ሄዶ ፡ የሳቸውንም ፡ ያክስቱንም ፡ አይን ፡ ማየት ፡ በሩቅ ፡ ሆኖ ፡ ሲያስባቸውም ፡ ሆዱ ፡ መታወክና ፡ ምራቁ ፡ ባፉ ፡ ውስጥ ፡ መምረር ፡ ይጀምራል ። በዛብህ ፡ መቸም ፡ እዩፈራ ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ተሸሽጎ ፡ ነው ፡ የሚውል ። ነፋስ ፡ ለመቀበል ፡ ውጭውን ፡ የሚያየው ፡ ማታ ፡ ጨለማ ፡ ለብሶ ፡ ነበር ።

ሰብለ ፡ በተፈታች ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ማታውን ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ከቤት ፡ ወጥቶ ፡ አጥሩ ፡ ውስጥ ፡ ሲዘዋወር ፡ ቆይቶ ፡ ሲሰለቸው ፡ እቤቱ ፡ ጥግ ፡ በተጋደመው ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ሄዶ ፡ ተቀመጠና ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ ይጠብቅ ፡ ጀመር ።

“ ምን ፡ አግኝቶዋቸው ፡ ይሆን ፡ እስካሁን ፡ የቆዩ ? ይህን ፡ ያክል ፡ አምሽተው ፡ አያውቁም ! ” አለ ፡ ብቻውን ፡ እግንዱ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ።

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ በጊዜ ፡ ነፋስ ፡ ተቀብዬ ፡ ልምጣ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ አልተመለሰም ፡ እውነትም ፡ በዛብህ ፡ እዚያ ፡ ቤት ፡ ከተቀመጠ ፡ ጀምሮ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ እውጭ ፡ አምሽቶ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ ካጥር ፡ ውጭ ፡ የግር ፡ ዳና ፡ የሰማ ፡ መሰለውና ፡ ለማረጋገጥ ፡ እንድ ፡ ጆሮውን ፡ ዳናውን ፡ ወደሰማበት ፡ ደቅና ፡ ቆይቶ ፡ በሁዋላ ፡ ወዳጥሩ ፡ በር ፡ ቢመለከት ፡ ሰው ፡ ሲገባ ፡ አዬ ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ነው ።

“ ማነህ ፡ አንተ ? ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እጥግ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ የተቀመጠውን ፡ ሰው ፡ በሩቁ ፡ ሲያይ ።

“ እኔ ፡ በዛብህ ፡ ነኝ ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ! ምነው ፡ በጤናዎ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ያመሹ ? ”

“ የምስራች ! ”

“ ተፈታች ? ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ከተቀመጠበት ፡ እንደ ፡ ኩዋስ ፡ ነጥሮ ፡ ተነስቶ ። ጩኸቱ ፡ በሩቅ ፡ የተኛ ፡ ሰው ፡ ይቀሰቅስ ፡ ነበር ።

“ ቀስ ፡ ቀስ ፡ ቀስ ፡ በል ! ና ፡ እቤት ፡ እንግባ ! ” አለና ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሲገባ ፡ በዛብህ ፡ እዬሮጠ ፡ ገብቶ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የቀኝ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የግራ ፡ ጉልበቱን ፡ እዬመላለሰ ፡ ይስም ፡ ጀመር ።

ከዚያ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ታግሎ ፡ ቀና ፡ ሲያደርገው ፡ የደስታው ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ ጸደቀች ፡ ነፍስ ፡ የሚያደርገውንም ፡ የሚለውንም ፡ አሳጥቶት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ እንባው ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ጉንጩ ፡ እዬወረደ ፡ “ ተመስገን ፡ ተመስገን ፡ ተመስገን ---- ሲል ፡ ሁኔታውን ፡ ሁሉ ፡ ተመልክቶ ፡ ጉዱ ፡ ካሳም ፡ ልቅሶ ፡ መጣበትና ፡ እንገት ፡ ላንገት ፡ ተያይዘው ፡ እዬሳቁ ፡ ብዙ ፡ እንባ ፡ አፈሰሱ ።



“ ለመሆኑ ፡ ማን ፡ ነገረዎ ? ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ሰውነቱ ፡ ትንሽ ፡ ጸጥ ፡ ካለ ፡ በሁዋላ ።

“ ወዳፋፍ ፡ ሄጄ ፡ ነፋስ ፡ ተቀብዬ ፡ ስመለስ ፡ ሀብትሽን ፡ ውሀ ፡ ልትቀዳ ፡ ስትሄድ ፡ አግኝቻት ፡ ነገረችኝና ፡ ሄጄ ፡ አዬሁዋት ። ”

“ ሰብለን ፡ ራስዎ ፡ ሄደው ፡ አዩዋት ? ”

“አዎን ፡ አዬሁዋት ፡”

“ እንዴት ፡ ናት ? ከስታለች ? ትናገራለች ? ትስቃለች ? ”

“ከስታለች ፡ ገርጥታለች ፤ ምንዋም ፡ ምንዋ ፡ ሰብለን ፡ አይመስል ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ባዘን ፡ ድምጽ ፡ እንገቱን ፡ ደፋ ፡ አድርጎ ። በዛብህም ፡ እንገቱን ፡ ደፋ ።

“ ለመሆኑሳ ፡ እንዴት --- ፈቱዋት ? እስማት ፡ አብነት ፡ ይሉት ፡ የነበረው ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ? አለ ፡ በዛብህ ፡ ሁለቱም ፡ እንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ ከቆዩ ፡ በሁዋላ ።

“ ተፈታ ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ በዛብህ ፡ ቀና ፡ አለና ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ።

“ እንዴት ? ምኑ ? ”

“አንተ ፡ ያደረግህባት ፡ እስማት ! ”

በዛብህ ፡ ከድንጋጤም ፡ ከመገረምም ፡ ብዛት ፡ የሚናገረው ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አይኑን ፡ አፍጥጦ ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ።

“ እስማቱም ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ ያልተለመደና ፡ የጎጃም ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ አዋቂ ፡ ሁሉ ፡ ሊፈታው ፡ የማይችል ፡ ነበረ ፡ አሉ ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ አሁንም ፡ ያሽሙር ፡ ፍርጥምታ ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ።

“እንግዲያ ፡ ማን ፡ ፈታው?”

“ካባይ ፡ ማዶ ፡ ከጉድሩ ፡ የመጡ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት፡ የሚባሉ ፡ ስልብ!”

"በዚህ : ባጭር : ጊዜ : እንዴት - - - አድርገው : ከጉድሩ : ማስመጣት : ቻሉ ?"

"እዚህ : መቃብር : ቤት : ተቀምጠው : ግሁስ : ነኝ : እያሉ : ሰውን : ሲዘርፉ : ቆይተዋል : እንጂ!"

አባ : ተክለ : ሀይማኖት : አባ : ተክለ : ሀይማኖት ! እኒህ - - - ዘግተው : ይኖራሉ : የሚባሉት?"

" አ --- ዎ! ዘግተው : ይኖራሉ : የሚባሉት!"

"እሳቸው : ናቸው : በሙሉ : ጎጃም : ያልተሰመደ : በሙሉ : ጎጃም : የማይፈታ : አስማት --------- የሚሉት ? "

"እሳቸው : ናቸው!" አለ : ጉዱ : ካሳ ፤ እፊቱ : ላይ : ይታይ : በነበረው : አሽሙር : ፈንታ : ቁጣ : ተተክቶ : አይኑ: በቅጥበት: ቀልቶ ::

"እየውልህ! ቤተ : እግዚአብሄራችን : እንደነዚህ : ላሉት : ሽፍቶች : እንደነዚህ : ላሉት : ዘራፊዎች : ዋሻ : ሆነች! እየውልህ! ከካህናቶቻችን : ከሀዋርያቶቻችን : የሚበዙት : ካለቆች : ጀምሮ : በመነኮሳቱ : አልፎ : እስከ : ተራ : ደብተሮች : እስከ : ዲያቆናቱ : ድረስ : አንዱ : አስማት : አድራጊ : አንዱ : አስማት: ፈቺ : ሌላው : ጋኔን : ስቦ : አምጪ : ሌላው : አስወጪ : አንዱ : መቅሰፍት : አምጪ ፥ ሌላው : ምህረት : አስጪ : ነን : እያሉ : ውሽታቸውን : በዬጥምጥማቸው : በዬቆባቸው : በዬደበሎዋቸው : ሸሽገው : ሊመሩት : ሊያስተምሩት : በተሰጣቸው : መንጋ : የሚጫወቱ : ናቸው! ታዲያ : ከነዚህ : ጋር : ማህበርተኛ : ሆኖ : ባንድ : ስመ : እግዚአብሄርን : መጥራት : በተቀደሰ : ስሙ : ማፌዝ : አይደለም ? እየውልህ! ይህ : ነው : ከምወዳት : ቤተ : እግዚአብሄር : ያራቀኝ! ሰው : የሚሰው : ሌላ : ነው : ነገር : ግን : እውነቱ : ይህ : ነው :: አሁን : አንተ : በራስህ : ባይደርስ : ኖሮ : እኒህ : ሰው : እንዲህ : ያለ : ነገር : ያደርጋሉ : ብዬ : ብነግርህ : አታምንም : ነበር :: ታምን : ኖሮዋል?"

"ብጭራሽ : አላምንም : ነበር :"

"እየውልህ : ብዙዎቹ : እንዲህ : ናቸው ::"

"ታዲያኮ : እንደስዎ : ያለ : ሰው : በካህናቱ : ክፉ : ስራ : ተቀይሞ : ከመሸሸ : እመሀከላቸው : ሆነው : ለነሱም : ለሚያታ



ልሉት ፡ ህዝብም ፡ ቢሰብኩ ፡ በጠቅላላው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልካም ፡ ነበር!"

"ያልጀመርሁት ፡ መሰለህ? ለምናገረው ፡ ሰው ፡ ዋጋ ፡ እንዳይሰጠው ፡ እብድ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አስወሩብኝ ፤ እብዱ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የሚባለውን ፡ ስም ፡ ያሰጠኝ ፡ እሱ ፡ ነው ።"

በዛብህ ፡ አንገቱን ፡ ደፋ ፡ አደረገና ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆይቶ ፡ "እንኩዋን ፡ ተፈታች ፡ እንጂ ፡ ግዴለም!" አለ ።

በበነጋው ፡ ጥዋት ፡ ቡና ፡ ተጠጥቶ ፡ እንቆጳም ፡ ሌሎችም ፡ ሁሉ ፡ ወደዬስራቸው ፡ ከተሰማሩ ፡ በሁዋላ ፡

"ምን ፡ አሰብህ ? በዛብህ ?" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

"እንዴት? ስለምኑ?"

"እንግዲህ ፡ ሰብለ ፡ ተፈታች ፤ ስለራስህ ፡ ምን ፡ ለማድረግ፡ ታስባለህ ፡ ማለቴ ፡ ነው!"

"ማሰብማ ፡ ሌሊቱን ፡ እንቅልፍ ፡ አጥቼ ፡ ሳስብ ፡ ነው ፡ ያደርሁ ፤ ብቻ ፡ የምጨብጠውን ፡ ነገር ፡ አጥቼ ፡ ተቸገርሁ ፡ እንጂ!"

"የሚሻል ፡ የመሰለኝን ፡ እኔ ፡ ልንገርህ?"

"ምን ፡ ይሻለኛል? እስቲ ፡ ይንገሩኝ!"

"አዲስ ፡ አበባ ፡ ሂድ! ወደዚያ ፡ መሄድህ ፡ ነው ፡ የሚሻለው ።"

"እንዴት?" አለ ፡ በዛብህ ፡ ደንግጦ ።

"እስክ ፡ መቼ ፡ እዚህ ፡ ተሸሽገህ ፡ መቀመጥ ፡ ትችላለህ? ለመቀመጥ ፡ ብትችልስ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ?"

"እሱስ ፡ እውነት ፡ ነው !" አለ ፡ በዛብህ ፤ አንገቱን ፡ ደፍቶ፡ ሲያስብ ፡ ቆይቶ ። "ብቻ ፡ አዲስ ፡ አበባስ ፡ ሄጄ ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ? ይህን ፡ አደርጋለሁ ፡ የምለውን ፡ ነገርኮ ፡ አጣሁ!"

"አዲስ ፡ አበባ ፡ ሂድ ፡ ያልሁበትን ፡ ምክናያት ፡ ልንገርህ? አንደኛ ፡ በጎጃም ፡ መሬት ፡ መኖርህ ፡ ከታወቀ ፡ ፈታውራሪ ፡ መከታተላቸው ፡ ስለማይቀር ፡ አንተም ፡ ሰብለም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በስጋት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የምትኖሩ ። ሁለተኛ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሄደህ ፡ ስራ ፡ የያዝህ ፡ እንደሆነ ፡ አሳብህ ፡ በስራህም ፤ በሌላውም - - - -መሀከል ፡ ይከፋፈልና ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ እዚህ ፡ የደ

ረሰውን - - - - - ሁሉ ፡ መርሳት ፡ ትችል ፡ ይሆናል ። እንዲያውም ፡ ግልጽ ፡ አድርጌ ፡ ልንገርህ ፤ ቶሎ ፡ ስራ ፡ ይዘህ ፡ ልብህ፡ የሚደነግጥላት ፡ ልጅ ፡ ብታገኝ ፡ ቶሎ ፡ እንድታገባ ፡ ነው ፡ የምመክርህ !"

እሱን ፡ እንኳዋ ፡ ይተውት ! ሰብለ ፡ ከቀረች ፡ እመነኩሳለሁ ፡ እንጂ ፡ ምሽት ፡ አላገባም !"

"ተሳስተሀል ! እግዚአብሄር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሴት ፡ የፈጠረ ፡ ሰብለን ፡ ብቻ ፡ ነው ?"

"ሴትማ ፡ ሞልቶዋል ! ከሰብለ ፡ ጋር ፡ ባልገናኝና ፡ እስዋን ፡ ባላውቅ ፡ ኖሮ ፡ እንድዋን ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ አግብቼ ፡ ለመኖር ፡ ምኞቴ ፡ ነበር ። አገሬንም ፡ የለቀቅሁ ፡ በቀደም ፡ እንዳጫወትሁዎ ፡ ምሽት ፡ አግብቼ ፡ ቤቴ ፡ ሰርቼ ፡ ለመኖር ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሄር ፡ ሲፈጥረኝ ፡ ለዚሀ ፡ አልመደበኝም ፡ መሰለኝ፤ ከስዋ ፡ ጋር ፡ አገናኘኝ ። ከንግዲህ ፡ ወዲያስ ፡ አላገባም ። ሌላ ፡ ምሽት ፡ ከማግባቱ ፡ ላጭር ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እስዋ ፡ የሰጠችኝን፡ ደስታ ፡ እያሰብሁ ፡ መቀመጡ ፡ ይሻለኛል !" አለ ፡ በዛብህ ፤ እንባው ፡ ባይኑ ፡ ሞልቶ ።

"ይገርማል ! ለካ ፡ ከፉም ፡ ሆነ ፡ በጎ ፡ የሚሰሩ ፡ ሰዎች ፡ መሳሪያዎች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ሰራተኛው ፡ እግዚአብሄር ፡ ስለሆነ ፡ እነሱን ፡ መጥላቱና ፡ ማማቱ ፡ ወይም ፡ መውደዱና ፡ ማመስገኑ ፡ ከንቱ ፡ ነው ! እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ ባይኖሩ ፡ ያ ፡ ከፉ ፡ የተሰራበት፡ ወይም ፡ በጎ ፡ የተሰራለት ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ከፉውን ፡ ወይም ፡ በጎውን ፡ በሌላ ፡ አማካይነት ፡ አያጣውም ፡ ማለት ፡ ነው !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ቀጠለና ።

" እንዴት ?"

" በቀደም ፡ እንደነገርሁዎ ፡ እናቴ ፡ ምሽት ፡ ሳላገባ ፤ በድንግልና ፡ ታቦት ፡ እንዳገለግል ፡ በስእለት ፡ ስለሰጠችኝ ፡ በስዋ ፡ አገሬ ፤ ከታሰርሁበት ፡ አምልጬ ፡ ምሽት ፡ አግብቼ ፡ ለመኖር፡ ነበር አገሬን ፡ የለቀቅሁ ። ይዩት ፡ አሁን ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ወደዚያው ፡ ጥንት ፡ ወደተመደበልኝ ፡ ህይወቴ ፡ መመለሴ ፡ ነው !"

" እስቲ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅህ ፡ በዛብህ !"



"መቸም ፡ ዲማ ፡ ከመጣህ ፡ ጀምሮ ፡ ሰብለን ፡ ታውቃታለህ ! መቸ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ከተፈጠረው ፡ ሴት፤ ሁሉ ፡ የተለየች ፡ ሆና ፡ ትታይህ ፡ የጀመረች ?"

"መጀመሪያ ፡ ሳያትም ፡ ልቤ ፡ ደንገጥ ፡ ብሎዋል ፤ ብቻ ፡ እሱ ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ ሴት ፡ ሲታይ ፡ የሚያስደነግጠውን ፡ ያክል ነው ። እንጃ --- እንዲያውም ፡ ትንሽ ፡ እፈራት ፡ ነበር ፡ መሰለኝ። የቀረው ፡ አሁን ፡ በቅርቡ --ነው ።"

"እየውልህ!ብዙ፡ጊዜ፡መተዋወቃችሁ፡የብዙ፡ጊዜ፡ጉዋደኝነታችሁ ፡ ጭዋታችሁ ፡ መላፋታችሁ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ መጨረሻ ፡ አደረሳችሁበት ፡ ላይ ፡ አደረሳችሁ ! ከዚያ ፡ በጣም ፡ ተዋደዳችሁ ! ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ እንደስዋ ፡ በቅርብ ፡ ካወቅሀቸው ፡ ከብዙዎቹ ፡ መሀከል ፡ አንድ ፡ የምትወዳት ፡ የምታጣ ፡ ይመስልሃል ?"

"የሰም ፡ አላገኝም ፤ አለቃ ! ሰብለ ፡ ልዩ ፡ ናት ። ከሌሎች ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ ናት ! ምሽትም ፡ ባላገባ ፡ ብዙ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ አውቃለሁ ። ታዲያ ፡ የማውቃቸው ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ ሁሉ ፡ የሚዋደዱትም ፡ ባሳብ ፡ ባለመስማማት ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ጭቅጭቅ፡ አያጣቸውም ። ይገርምዎታል ፡ ሰብለና ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነፍስ፡ እንደ ፡ ተጋራን ፡ ሁሉ ፡ እስዋ ፡ ያሰበችውን ፡ እኔ ፡ ስናገር ፡ እኔ ፡ ያሰብሁትን ፡ እስዋ ፡ ስትናገር ፡ እንገኝና ፡ ተያይዘን ፡ መሳሳቅ ፡ ብቻ ፤ መደሰት ፡ ብቻ ፡ ነው ! ምነው ፡ አብረን --- እንዲህ ፡ ስንሆን ፡ ቢያዩን ፡ ኖሮ ! አለና ፡ በዛብህ ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ከሰብለ ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ደስታ ፡ መቅረቱ ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ እንባው ፡ ይወርድ ፡ ጀመር ።

"ግሩም ፡ ነው ! አንተም ፡ እንደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ያለ ፡ አባት ፡ ቢኖርህ ፡ ሰብለ ፡ አስማት ፡ አድርጋበታለች ፡ ትባል ፡ ነበር ።"

" ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አይንዋን ፡ የማይበት ፡ ዘዴ ፡ የሚገኝ ፡ ይመስልዎታል ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆይተው ።

" አልነገርሁህም ፡ መሰለኝ ፤ አባ ፡ ተከለ ፡ ሀይማኖትክ ፡ ጠባቂ ፡ ጭምር ፡ እንዲሆኑ ፡ ተቀጥረዋል !"

" አምሳ ፡ ብር ፡ አሰኝ ፤ እሱን ፡ ብሰጣቸውና ፡ አንድ ፡ ማታ

አስገብተውኝ ፡ አይቻት ፡ ብሄድ --- እሺ ፡ የሚሉ ፡ አይመስልዎትም ?

" እንደሳቸው ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሴት ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚመረጡ ፡ በጥብቅነታቸው ፡ የታወቁ ፡ በመሆናቸው ፡ መሆኑን ፡ አታውቅም ?"

" ጥብቆችና ፡ ታማኞች ፡ ናቸው ፡ ሲባሉስ ፡ እሰማለሁ ፤ ብቻ ፡ ተሰናብቼ ፡ ስመሄድ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ልስጥ ፡ ስል ፡ ገንዘቡ ፡ ያጉዋጉዋቸው ፡ ይሆናል ፤ ወዲያውም ፡ እምነት ፡ አጎደሉ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ አይኖርም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ !"

. "-እምነት ፡ እንኩዋ ፡ አይደለም ፤ ቅናት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ ቢወዱ ፡ ቅናታቸው ፡ ከገንዘብ ፡ ፍቅራቸው ፡ ይበልጣል ። ዝም ፡ ብለህ ፡ ሂድ ፡ እንዳያስይዙህ ። ሁላችንም ፡ ደህና ፡ ከሆን ፤ የተመቸ ፡ አጋጣሚ ፡ ካገኘሁ ፤ ከቻልሁ --- ሰብለን ፡ ስርቄ ፡ አንተ ፡ ባለህበት ፡ ለማድረስ ፡ መሞከሬ ፡ አይቀርም ፤ ብቻ ፡ እግዚአብሄር ፡ ይርዳ ። እዚያ ፡ እንደ ፡ ደረስህ ፡ ቶሎ ፡ ስራ ፡ ያዝና ፡ የተቀመጥህበትን ፡ ቦታ ፡ አስታውቀኝ ።"

በዛብህ ፡ እንባው ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ጉንጩ ፡ እዬወረደ ፡ ተነስቶ ፡ የጉዱ ፡ ካሳን ፡ ጉልበት ፡ ሳመ ።

"ግዴለህም ፡ አፈር ፡ ካልተጫነኝ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሰብለን ፡ በጅህ ፡ አገባታለሁ ! ብቻ ፡ ቶሎ ፡ ሂድና ፡ ስራ ፡ ያዝ ፡ ትንሽም ፡ ቢሆን ፡ ስራ ፡ ያዝ !" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

## ምእራፍ ፡ ፳፱

## አዲስ ፡ አበባ ፡

በዛብህ ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ ከግራ ፡ ጌታ ፡ ቀለመወርቅና ፡ ከእዝራ ፡ ጋር ፡ ከዲማ ፡ በጨለማ ፡ ወጥቶ ፡ ድምጽ ፡ የሰማ ፡ በመሰለው ፡ ቁጥር ፡ አሳቡ ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ እዬተገተተ ፡ ተራሮች ፡ እስኪጋርዱት ፡ ድረስ ፡ በዬደቂቃው ፡ ዲማን ፡ እዬዞረ ፡ እያዬ ፡ አባይ ፡ ደረሰ ። ከዚያ ፡ ከወዳጆቹ ፡ በነባ ፡ ተሰነባብቶ ፡ ከሞጣ ፡ ነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ ተጨምሮ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገባ ።

ካባይ ፡ እስከ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ አስር ፡ ቀን ፡ ሲጉዋዝ ፡ ስላዲስ ፡ አበባ ፡ የነገሩት ፡ ወሬ ፡ እሰበሱ ፡ የሚማሩና ፡ ማንኛውን ፡ መያዝ ፡ የሚያስቸግር ፡ ስለነበረ ፡ ሰግቶ ፡ ነበር ።

" ስራ ፡ ለሚያውቅ ፡ ሰው ፡ እግር ፡ እስኪላጥ ፡ ቢሄዱ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ የመሰለ ፡ አገር ፡ ይገኛል ፡ ብለህ ፡ አታስብ !" ይለዋል ፡ አንዱ ።

" አዲስ ፡ አበባ ፡ የሌቦች ፡ አገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰርተው ፡ የሚያድሩ ፡ ሰዎች ፡ አገር ፡ አይደለም ! ያዲስ ፡ አበባ ፡ ሌባ ፡ እንዳገርህ ፡ ሌባ ፡ ጨለማ ፡ ለብሶ ፡ የሚሰርቅ ፡ መሰለህ ? የለም ፡ አይንህ ፡ እያዬ ፡ ብርህን ፡ ከኪስህ ፡ አውጥቶ ፡ ይወስደዋል ! እንዲያው ፡ እንጃ ! ያፍዝ ፡ ያደንግዝ ፡ አለው ፡ መሰለኝ !" ይለዋል ፡ ሌላው ።

" እ --- ! ጽህፈት ፡ የሚያውቅማ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ልፋፈ ፡ ጽድቁንና ፡ ክታቡን ፡ እየጻፈ ፡ ብሩን ፡ በቁና ፡ መስፈር ፡ ነው !" ይለዋል ፡ አንዱ ።

" ምን ፡ ዛሬማ ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ረከሰ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው ! ድሮ ፡ አንድ ፡ ገድል ፡ ወይም ፡ ታምር ፡ ጽፈህ ፡ ላንድ ፡ መኩዋንንት ፡ ብትሰጥ ፡ አንድ ፡ ጠብደል ፡ ባሪያ ፡ ወይም ፡ አምሳ ፡ ስድሳ ፡ ብር ፡ ታገኝ ፡ ነበር ፡ ዛሬስ --- ካንድ ፡ ሊቅ ፡

አንድ ፡ የኔ ፡ ብጤ ፡ ደንቆሮ ፡ ይሻላል ፡ እንጨቱን ፡ ይሁን ፡ ድንጋዩን ፡ ወይም ፡ ውሀውን ፡ ተሸክሞ ፡ ሆዱን ፡ ሞልቶ ፡ ያድራል ! ” ይለዋል ፡ ሌላው ።

“ አዲስ ፡ አበባ ፡ የማውቀው ፡ ሰው ፡ የለኝም ፡ ምን ፡ ባደርግ ፡ የሚሻለኝ ፡ ይመስልዎታል ? እስቲ ፡ ይምከሩኝ ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛውን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሊገቡ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሲቀራቸው ፡ ሱሉልታ ፡ በሰፈሩበት ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጫወቱ ።

“ ገንዘብ ፡ ካለህ ፡ አትቸገርም ፡ ገንዘብም ፡ የምታውቀው ፡ ሰውም ፡ የሌለህ ፡ እንደሆን ፡ ነው ፡ ችግሩ ! እስቲ ---- ለማና ቸውም ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ጉለሌ ፡ ሰፈርና ፡ አንተም ፡ እኛም ፡ ስራ ፡ እስክታገኝ ፡ የምትቆይበት ፡ ሰው ፡ እንፈልጋለን ። ” አሉ ፡ ነጋድራስ ።

“ ገንዘብስ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ያገጣጠሙኝ ፡ ወዳጆች ፡ አዋጥተው ፡ የሰጡኝ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አለኝ ። ”

“ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ካለህማ ፡ ማለፊያ ፡ ቤት ፡ ተከራይተህ ፡ ማለፊያ ፡ ቀላቢ ፡ ቀጥረህ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያቆይሀል ። ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ አገሩን ፡ እስክትለምደው ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ብትቆይ ፡ ይሻላል ። ገንዘብህም ፡ እንዳይጠፋብህ ፡ መጠንቀቅ ፡ ነው ። ”

በዛብህ ፡ ሰፈሩን ፡ ጉለሌ ፡ ከነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ አድርጎ ፡ ጥዋት ፡ አብሮዋቸው ፡ ይወጣና ፡ አራዳ ፡ ሲደርስ ፡ ተለይቶዋቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ የሚሸጥባቸውን ፡ ሱቆች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ትልልቅ ፡ ግቢዎችንና ፡ አደባባዮችን ፡ እዩ ዞረ ፡ ሲያይ ፡ ውሎ ፡ ማታ ፡ ደክሞት ፡ ይመለሳል ። ከገንዘቡ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ አስቀርቶ ፡ የቀረውን ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ እንዲይዙለት ፡ ስለሰጠ ፡ እሰረቃለሁ ፡ ወይም ፡ እቀማለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚሰጋበት ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ቢሄዱት ፡ የማያልቅ ፡ ትልቅ ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ የህዝቡ ፡ ኑሮ ፡ ልማዱ ፡ እንዲያው ፡ በጠቅላላው ፡ ምኑም ፡ ምኑ ፡ ጎጃምን ፡ እስኪለቅ ፡ ከሚያውቃቸው ፡ እንደ ፡ ሞጣ ፡ እንደ ፡ ደብረ ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ ዲማ ፡ ካሉት ፡ ከተሞች ፡ በጭራሽ ልዩ ፡ ሆና ፡ ስለታዩው ፡ ለጊዜው ፡ ድንግርግር ፡ አለው ።



ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ባንድ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ መነገሩ ፡ አስገረመው ። በዚያ ፡ ላይ ፡ አማርኛ ፡ ተብሎ ፡ የሚነገረው ፡ ስብሩም ፡ ሆነ ፡ ቃሉ ፡ አማርኛ ፡ አልመሰለው ፡ አለ ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ልማዱን ፡ አለማወቁ ፡ አንድ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ይጥለኝ ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ ይሰጋ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ኩታውን ፡ ተከናንቦ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሊሄድ ፡ ገና ፡ ከሰፈሩ ፡ ሲወጣ ፡ አንድ ፡ መንገደኛ ፡ አገኘና ፡ “ እንዴት ፡ አደሩ ፡ ጌታው ! ” አለ ፡ ከንንቡን ፡ አውርዶ ።

“ እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ አደርክ ? ” አለ ፡ መንገደኛው ፡ ምን ፡ ሊጠይቀኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቆም ፡ አለና ። በዛብህ ፡ ግን ፡ ኩታውን ፡ እንደገና ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ። ሰውዬው ፡ ገርሞት ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ በዛብህን ፡ እስኪርቅ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ጉድ ፡ ሲመለከተው ፡ ቆይቶ ፡ እሱም ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ መንገደኛ ፡ አገኘና ፡ አሁንም ፡ እንደፊተኛው ፡ ከንንቡን ፡ አውርዶ ፡ “ እንዴት ፡ አደሩ ፡ ጌታው ! ” አለ ።

“ እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ ” አለ ፡ መንገደኛው ፡ እሱም ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ መንገደኛ ፡ ምን ፡ ሊጠይቀኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቆም ፡ አለና ። በዛብህ ፡ አሁንም ፡ ኩታውን ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ገፋ ፡ አድርጎ ፡ መንገዱን ፡ ሲቀጥል ፡ ሲል ፦

“ የት ፡ ታጃኛለህ ? እባክህ ! ” አለው ፡ መንገደኛው ።

“ ኧረ ፡ አላውቅዎም ፡ ጌታው ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ መፍራት ፡ ብሎ ።

“ ታዲያ ፡ ባታጃኝ ፡ ነው --- እንዲሁ ፡ ተነስተህ ፡ እንዴት ፡ አደርክ ፡ ያልከኝ ?”

“ ኧረ ፡ አላውቅዎም ! የእግዚአብሄርን ፡ ሰላምታ ፡ መስጠት ፡ ይገባል ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ።”

“ይህ ፡ አታላይ ፡ መልቲ ፡ እድፍ ፡ ጨርቅ ፡ ብለብስ ፡ ባላ

ገር ፡ መሰልኩህ ?"

" ኧረ ፡ እኔ —"

"አትኬድም ፡ አሁን ? አንት ፡ ሽአባ ! እንዳንት ፡ ያለውን ፡ ሌባ ፡ የማላአ ፡ መሰለህ ? አሁን ፡ ዘበኛ ፡ ጠርቼ ፡ አስኧፈድድህ ፡ ነበር !"

በዛብህ ፡ ምንም ፡ እንኳዋ ፡ ሰውዬው ፡ የተናገረውን ፡ ቃል በሙሉ ፡ አጣርቶ ፡ ለማወቅ ፡ ባይችል ፡ በጠቅላላው ፡ አሳቡ ፡ ስለገባው ፡ ደንግጠ ፡ መንገደኛው ፡ የተቆጣበትን ፡ ምክንያት ፡ ግን ፡ ባለማወቁ ፡ ግራ ፡ ገብቶት ፡ እዚያ ፡ ቆሞ ፡ ሲሳደብ ፡ ትቶት ፡ ሸሸ። ከዚያ ፡ የከተማው ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ እዚያ ፡ የገጠመውን ፡ ችግር፡ ይዞ ፡ የሚቆዩው ፡ ስለመሰለው ፡ በመንገድ ፡ የሚያገኘው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘበኛ ፡ ጠርቶ ፡ የሚያሳስረው ፡ ስለመሰለው ፡ ወደ ፡ ከተማ፡ መሄዱን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ተመለሰና ፡ ተሸሸጎ ፡ ድምጽ ፡ በሰማ ፡ ቁጥር ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ዘበኛ ፡ መጣብኝ ፡ እያለ ፡ ሲሸበር ፡ ዋለ ። ማታ ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛውና ፡ ጉዋደኞቻቸው ፡ ከነበያ ፡ ሲመለሱ ፡ የደረሰበትን ፡ ሲነግራቸው ፡ ጊዜ ፡ ይስቁ ፡ ጀመር ።

" አዬህ ? እዚህ ፡ አገር ፡ እንዳገራችን ፡ በመንገድ ፡ ለምታገኘው ፡ የማታውቀው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሰላምታ ፡ መስጠት ፡ የለብህም !" አሉ ፡ ነጋድራስ ።

" እንዴት ? እንዲያው ፡ እንዲሁ ፡ እንደተቀያዬሙ ፡ ሁሉ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መተላለፍ ፡ ነው ? "

" ልማድ ፡ ሆኖ ፡ ሰው ፡ ለማያውቀው ፡ ሰው ፡ ሰላምታ ፡ አይሰጥም ። መንገድ ፡ ወይም ፡ ቦታ ፡ ሲጠፋህ ፡ ብቻ ፡ የማታውቀው ፡ ሰው ፡ ቢሆንም ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥተህ ፡ የጠፋህን ፡ ብትጠይቅ ፡ ግድየለም ። ያለዚያ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ማለፍ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ጠንካራ ፡ ጸሀይ ፡ ወይም ፡ ዝናብ ፡ ካልሆነ ፡ ተከናንቦ ፡ መሄድ ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ ልማድ ፡ አይደለም ። ያላንድ ፡ ምክንያት ፡ ተከናንበው ፡ የሚሄዱ ፡ ሰዎች ፡ ፊታቸው ፡ እንዲታይ ፡ የማይፈልጉ ፡ ሌቦች ፡ ወይም ፡ ቀማኞች ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ በደህና ፡ ጊዜ፡ ተከናንበህ ፡ ሄደህ ፡ ለማታውቀው ፡ ሰው ፡ ሰላምታ ፡ ስትሰጥ ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡ አታላይ ፡ ትመስለዋለህ ። ለዚህ ፡ ነው ፡ ሰውዬው ፡



የተቆጣ ።"

"ግሩም ፡ ነው ! እንግዲህ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ቁዋንቁዋና ፡ ልማድ ፡ እስካጠና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መፍጀቱ ፡ ስለማይቀር ፡ ስራ ፡ ፈልጌ ፡ ባገኝም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ነው ፡ ማለት፡ ነው !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ቁዋንቁዋና ፡ ልማድ ፡ አለማወቁ ፡ ቶሎ ፡ ስራ ፡ ፈልጎ ፡ ለማግኘት ፡ መሰናክል ፡ ስለመሰለው ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ተስፋ ፡ እንደሰጠው ፡ ሰብለን ፡ ያመጣለት ፡ እንደሆን ፡እብሮቱ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ የሚወድቅ ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ሲያስብ ፡ ቆዩና ፡

" የለም ፡ አይዞህ ፡ ሁሉንም ፡ አሁን ፡ ትለምደዋለህ ። ቁዋንቁዋው ፡ መቼም ፡ ያው ፡ የምታውቀው ፡ አማርኛ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ 'ቀን' ፡ በ'አ' ፡ 'ከ'ን በ'ኸ' ፡ እየለወጡ ፡ ስለሚናገሩ ፡ ጆሮህ፡ ስላለመደው ፡ ለጊዜው ፡ ልዩ ፡ ቁዋንቁዋ ፡ ይመስላል ። " አሉ ፡ ነጋድራስ ፡ ፍርጥም ፡ ብለው ።

'እሺ ፡ ቁዋንቁዋውስ ፡ ይሁን ፡ ልማዱ ፡ እስኪታወቅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይፈጅም ? ለምሳሌ ፡ የግዜርን ፡ ሰላምታ ፡ መስጠት ፡ ነውር ፡ ሆና ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡ አታላይ ፡ የሚያስመስልና ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ የሚያጣላ ፡ ከሆነ ፡ ነውር ፡ ያልሆነው ፡ ምንድር ፡ ነው ? እንዴትስ ፡ አድርጎ ፡ ቀርቦ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ለመተዋወቅና ስራ ፡ ተጠያይቆ ፡ ማግኘት ፡ ይቻላል ?"

" አይዞህ ፡ አትፍራ ፡ ልማዱም ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ካገራችን ፡ የተለዩ ፡ አይደለም ፡ ትንሽ ፡ ብቻ ፡ ነቃ ፡ ማለት ፡ ነው፡ የሚያስፈልግ ። ሰላምታ ፡ መስጠት ፡ ለምን ፡ አታላይ ፡ አስመሰሎ፡ አሳዩ ፡ ለምትለው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከያገሩ ፡ ብዙ ፡ አታላዮች ፡ የሚሰበሰቡበት ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ አንዳንዶቹ፡ አታላዮችም ፡ ካገሩ ፡ ከኔ ፡ አገር ፡ የሚመጡ ፡ ናቸው ። ታዲያ ፡ እንዲህ ፡ ያሉት፡ ሰዎች ፡ እንግዳ ፡ ወይም ፡ የሚታለል ፡ ሰው ፡ ያዩ ፡ ሲመስላቸው ፡ መጀመሪያ ፡ ሰላምታ ፡ በመስጠት ፡ ቀጥሎም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የማታለያ ፡ መንገድ ፡ ደጎችና ፡ ረዳቶች ፡ በመምሰል ፡ ቀርበው ፡ የሰርቆት ፡ የቅምያና ፡ ሌላም ፡ የወንጀል ፡ ስራቸውን ፡ የሚፈጽሙ ፡ መሆናቸው ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የታወቀ ፡ ሆኖዋል ። ስለዚህ ፡ ለማታውቀው ፡ ሰው ፡ ተከናንበህ ፡ ሄደህ ፡ ሰላምታ ፡ ስት

ሰጥ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ተጠራጥሮ ፡ ቢቆጣ ፡ አይግረምህ ። ይልቅ ፡ ቅድም ፡ እንዳልኩህ ፡ አለመፍራት ፡ ነው ። ብትሰጋና ፡ የንግድነት ፡ መልክ ፡ ሲታሳይ ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ አይን ፡ ይከታተልሃና ፡ አንተም ፡ በበኩልህ ፡ ያን ፡ ስታይ ፡ ነውር ፡ የሰራህ ፡ መስሎህ ፡ ፍራት ፡ አይለይህም ፡ ስትባንን ፡ ትኖራለህ ።”

ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ ከተገናኙ ፡ ጀምረው ፡ ትህትናውንና ፡ በጣም ፡ የታረመ ፡ አመል ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ በማየታቸው ፡ ይወዱት ፡ ስለነበረ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ኑሮ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ሊፈራው ፡ እንደማይገባና ፡ በራሱ ፡ እምነት ፡ እንዲኖረው ፡ በየጊዜው ፡ እየመከሩ ፡ ያደፋፍሩት ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከሚኖሩ ፡ አንዳንድ ፡ የሚያውቋቸው ፡ ደህና ፡ ሰዎች ፡ አስተዋወቁት ። ብቻ ፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ በዛብህ ፡ ከመንጋዋ ፡ ለይተው ፡ ከንግዳ ፡ መንጋ ፡ እንደ ፡ ጨመርዋት ፡ ላም ፡ መቡዋዘቷና ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ህዝብ ፡ መሀከል ፡ ብቸኝነት ፡ የሚሰማው ፡ መሆኑ ፡ አልቀረም ። አዲስ ፡ አበባ ፡ ተቀምጦ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚታዩው ፡ የሰብለ ፡ መልክ ፡ የሚሰማው ፡ የሰብለ ፡ ድምጽ ፡ የሚታሰበው ፡ ሰብለን ፡ አስኪብልሎ ፡ ለማግባት ፡ ያቀደው ፡ እቅድና ፡ በመጨረሻ ፡ በስዋ ፡ ፈንታ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የሰጠውን ፡ በጥርጣሬ ፡ የተከበበ ፡ ተስፋ ፡ ይዞ ፡ መምጣቱ ፡ ነበር ። “ሁላችንም ፡ ደህና ፡ ከሆን ፡ የተመቸ ፡ አጋጣሚ ፡ ከተገኘ ፡ ከቻልሁ ---- ሰብለን ፡ ሰርቄ ፡ በጅህ ፡ ሳላገባት ፡ አልቀርም ፡” ብሎ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሲሰናበተው ፡ የተናገረው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡ መሀከል ፡ እንኳ ፡ በተቀመጠበት ፡ በጆሮው ፡ ውስጥ ፡ ጎልቶ ፡ ይሰማበትና ፡ ድንገት ፡ አቋርጦ ፡ “እግዚአብሄር ፡ ደህና ፡ ያድርግዎ ፡ የተመቸ ፡ አጋጣሚ ፡ ያምጣልዎ ፡ ያስችልዎ ፡” ሲል ፡ አብረውት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ይደነግጣሉ ፡ ወይም ፡ ሳይተኛ ፡ ይቃዣል ፡ ብለው ፡ ይስቁበታል ።

“በዛብህ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ቁዋንቁዋና ፡ ልማድም ፡ በተቀር ፡ ልብህ ፡ የሚያስቀልልበት ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ይሰማኛል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምንድነው ፡ ብለህ ፡ ብትጠይቀኝ ፡ ልነግርህ ፡ አልችልም ። ብቻ ፡ ይህ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በንቅልፍ ፡ ተነስቶ ፡ እንደ



ሚሄድ ፡ ሰው ፡ ፍዝዝ ፡ የሚያደርግህ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ባፍላ ፡ ጭዋታ ፡ መሀከል ፡ የሚያቃዥህ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ቁዋንቁዋና ፡ ልማድ ፡ አለማወቅ ፡ ነው ፡ ብትለኝ ፡ የማልቀበለው ፡ ነገር ፡ ነው !” አሉ ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ሲጫወቱ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ያልጠየቁትን ፡ ተናግሮ ፡ ወዲያው ፡ ሲደነግጥ ፡ አይተው ።

“ሌላ ፡ ምን ፡ ልቤ ፡ የሚያስቀልልበት ፡ ነገር ፡ ይኖር፡መሰለዎ?” አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ማፈር ፡ ብሎ ።

“ስሙን ፡ ጠርቸ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ልልህ ፡ አልችልም፡እንጂ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከመድረሳችንም ፡ በፊት ፡ ገና ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ተገናኝተህ ፡ አባይን ፡ ስትሻገር ፡ ጀምሮ ፡ የወለደችውን ፡ ሞጭቀው፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ እንዳስቀሩባት ፡ አራስ ፡ ላም ፡ ልብህ ፡ ወደ፡ሁዋላ፡ ሲጎተትና ፡ ሲያስቀልል ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ ተመልክቻለሁ ።”

“ነገሬ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በመውጣቴ፡ ምናልባት፡በሌሎች ፡ ላይ ፡ የማይታይ ፡ ቅርታ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ አይተው፡ይሆናል።”

“ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከጎጃም ፡ ወጥቶ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ሲመጣ ፡ ያዩሁት ፡ ሰው ፡ አንተን ፡ ብቻ ፡ ይመስልሀል ?”

“አገሩን ፡ ለሁል ፡ ጊዜ ፡ ለቆ ፡ የሚሰደድ ፡ ማለቴ ፡ ነውኮ ፡ ደርሶ ፡ ተመላሽ ፡ አይደለም!”

“ቢሆንም ።”

“እንግዴህ ፡ እንደዩስሜቱ ፡ ቢሆን ፡ ነው ።”

“እይ ፡ በዛብህ! እኔኮ ፡ ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ ነኝ! ጥሩ ፡ ነጋዴና ፡ ጥሩ ፡ ጠንቋዋይ ፡ ግምት ፡ አዋቂዎች ፡ መሆናቸውን ፡ አታውቅም?”

“እንዴት?”

“እዩህ? እገሌ ፡ ጥሩ ፡ ጠንቋዋይ ፡ ነው ፡ እየተባለ ፡ የሚደነቀው ፡ ጠንቋዋይ ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ ከዛርና ፡ ከጋኔን ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡ ሰው ፡ የማያውቀውን ፡ ከነሱ ፡ እያገኘ ፡ አለመሆኑን ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ ምናልባት ፡ አንተ ፡ ደብተራው ፡ ታውቅ ፡ ይሆናል፡ ካብዛኛው ፡ ሰው ፡ የተሻለ ፡ የግምት ፡ ስጦታ ፡ ስላለው ፡ ግምቱ ፡ ከሚናገረው ፡ የሚበዛው ፡ ስለሚያዝለት ፡ ነው ። ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ የሚባለውም ፡ ነገ ፡ ወይም ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ የሚወደደውን ፡

ገምቶ ፡ ዛሬ ፡ የሚገዛ ፡ ነገ ፡ ወይም ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ የሚረክሰውን ፡ ገምቶ ፡ ዛሬ ፡ የሚሸጥ ፡ ነው ። ታዲያ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ግምት ፡ የገብያውም ፡ የሰውም ፡ ሁኔታ ፡ ተጠንቶ ፡ የሚደረስበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲሁ ፡ የሚገኝ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ የገብያና ፡ ያጋሰስ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሰው ፡ ሁኔታ ፡ ቈምር ፡ መገመት ፡ የምችል ፡ ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ ነኝ ፡ ማለቴ ፡ ነው ።" አሉ ፡ ነጋድራስ ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብለው ።

"ይህ ፡ ሁሉ ፡ እውነትዎ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ እስዎ ፡ እንዳሉት ፡ ጥሩ ፡ ጠንቀዋይም ፡ ይሁን ፡ ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ ከሚገምቱት ፡ አብዛኛው ፡ እንጂ ፡ ሁሉ ፡ ስለማይገዝ ፡ ስለኔ ፡ የገመቱት ፡ ከማይዘው ፡ ከጥቂቱ ፡ መሀከል ፡ ሊሆን ፡ አይችልም?"

"ይሁን ፡ ተሰስቼ ፡ ይሆናል ! " አሉ ፡ ነጋድራስ ፡ በዛብህ ፡ ምስጢሩን ፡ ሊነግራቸው ፡ አለመፍቀዱን ፡ ሲያዩ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፋ ፡ አደረጉና ።

"አገርህም ፡ ይሁን ፡ እዚህ ፡ የተቸገርህበት ፡ ነገር ፡ እንዳለ፡ ልረዳህ ፡ እችል ፡ እንደሆነ ፡ ብዬኮ ፡ ነው ፡"አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ነጋድራስ ።

"እስከ ፡ ዛሬ ፡ የረዱኝ ፡ መቼ ፡ አነሰና?"

"እየ----እባክህ ፡ እስከ ፡ ዛሬስ ፡ ምንም ፡ አላደረግሁልህ፡ ልቤ ፡ ወደ ፡ ገብያው ፡ ተሰቅሎ ። አሁን ፡ መሄጃዬ ፡ ስለደረሰ ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ስትይዝ ፡ አይቼህ ፡ እንድሄድ ፡ ነበር ። አንዳንድ፡ ጊዜ ፡ ሩፋኤል ፡ ትሄዳለህ? እዚያ ፡ ካህናቱ ፡ እጅግም ፡ ስለማይጠጉት ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ አይጠፋም ፡ ይባላል ።"

"ከማህሌት ፡ ተለይቼ ፡ አላውቅም ።"

"ካለቃው ፡ ተዋውቀሀል ?"

"የለም ። እሳቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይመጡም ፡ ሲመጡም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ስለሚከባቸው ፡ እንግዳ ፡ ሰው ፡ ሊያገኛቸው ፡ የሚችል ፡ አይመስለኝም ።"

"ቆይ ፡ ነገ ፡ ጥዋት ፡ ገበያ ፡ መሄዱን ፡ ትቶ ፡ እደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ዘንድ ፡ እወስድህና ፡ እሱ ፡ ያገናኝሀል ።"

"ማነው ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ?"

"የኛ ፡ ነው ፡ ያገራችን ፡ የሞጣ ፡ ሰው ፡ ነው ። በቀደምም ፡



እስቤው ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ለመሄድ ፡ ስቸኩል ፡ ረሳሁት ።"

በበነጋው ፡ እሁድ ፡ ጥዋት ፡ ነጋድራስ ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ማር ፡ የሸጡበትን ፡ ገንዘብ ፡ ለመቀበል ፡ ሀሚድ ፡ የሱፍ ፡ ከሚባል ፡ ቱጃር ፡ ጋር ፡ ቀጠሮ ፡ ቢኖራቸው ፡ ወደሱ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ልከው ፡ እሳቸው ፡ በዛብህን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሩፋኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄዱ ።

ሩፋኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅዳሴ ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ አገልግሎቱ ፡ አልቆ ፡ ካህናቱ ፡ ለግብር ፡ ወደ ፡ ግቢ ፡ ሊሄዱ ፡ ሲጠራሩ ፡ ደረሱ ። ደብተራ ፡ መንበሩንም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲሄድ ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ አገኙትና ፡ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ አስተዋውቀው ፡ ብርቱ ፡ ስራቸውን ፡ ትተው ፡ እሱን ፡ ፍለጋ ፡ የሄዱበትን ፡ ጉዳይ ፡ አንድ ባንድ ፡ ዘርዝረው ፡ ነገሩት ።

"ከዛሬና ፡ ከነገ ፡ ማለፍ ፡ የለበትም ፡ ማለትዎ ፡ ነው ፡ እንጂ፡ ያስቸገረኝ ፡ ጊዜ ፡ ከሰጡኝ ፡ ካለቃ ፡ ስርግው ፡ ጋር ፡ ማስተዋወቅም ፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ማስታወሱም ፡ አያስቸግረኝምኮ ፡ ነጋድራስ ! አለቃ ፡ ዛሬ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ እግቢ ፡ ግብር ፡ ስለሚውሉ ፡ ነገ ፡ ጥዋትም ፡ ወደ ፡ ርስታቸው ፡ ይሄዳሉ ፡ ተብሎ ፡ ስለሚወራ ፡ ሳይመቸ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ቃል ፡ አባይ ፡ አድርገው ፡ እንዳይጣሉኝ ፡ ፈርቸዎ ፡ ነው ። መቸም ፡ እስዎ ፡ ስራዎም ፡ ሆነ ፡ ቃልዎ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በሚዛን ፡ ነው !" አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ፍርጥም፡ ብሎ ።

"አደለምኮ ፡ መንበሬ ፡ ግቢ ፡ ቢውሉ ፡ ግቢ ፡ ያድራሉ ? ግታም ፡ ቢሆን ፡ እቤታቸው ፡ ድረስ ፡ ወስደህ ፡ አገናኝተህ ፡ ስራ፡ እንዲሰጡት ፡ አደራ ፡ በላቸው ። በፈለግህበት ፡ ጊዜ ፡ እቤታቸው ፡ የምትገባ ፡ ባለሙዋል ፡ መሆንህንና ፡ አንተ ፡ ካልህቸው ፡ የማይወጡ ፡ መሆናቸውን ፡ ስምቻለሁ ። እንግዲህ ፡ አደራ ፡ ለእሱ ፡ የምታደርገውን ፡ ሁሉ ፡ ለኔ ፡ እንደምታደርገው ፡ ቁጠረው !" ሲሉ ፡ ነጋድራስ ፡ በደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ አይነት ፡ ስልጣን ፡ ያላቸው ፡ ወይም ፡ ባለብርቱ ፡ ውለታው ፡ መሆናቸው ፡ ለበዛብህ ፡ ተሰማውና ፡ ጉዳዩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ቀና ፡ መንገድ ፡ የያዘለት ፡ መስሎ ፡ ታይቶት ፡ ደስ ፡ አለው ።

" እየ --- ብርቱ ፡ ሸክም ፡ ጣሉብኝ ፡ ነጋድራስ ፡" አለ ፡

ደብተራ : መንበሩ : እውነትም : የጣሉበት : ሸክም : እንደ : ከበ
ደው : ሁሉ : ትከሻውን : ትንሽ : ጎበጥ : አንገቱን : ወደታች :
ሰበር : አድርጎ : መሬት : መሬት : እያዩ ።

ከዚያ : ነጋድራስ : ከሁለቱ : ደብተሮች : ተለይተው : ወደ
ስራቸው : ሲሄዱ : " አንድ : ነገር : አሰብሁ :" አለ : ደብተራ
መንበሩ ።

" ምን ?"

"ማታ : እቤታቸው : ሄደን : ከምናስቸግራቸው : ለምን :
አሁን : እግቢ : አንሄድ ? እዚያ : ከግብር : ሲወጡ : እናገኛቸዋ
ለን : ወዲያውም : ግብር : እንበላለን ።"

" ማን : ያስገባናል ?"

"መቸስ : የንጉስ : ግብር : ተጠርቶ : ሄዶ : የሚበላ : የለ :
ያው : እግሩ : ያደረሰውና : እዚያ : የተገኘ : ነው : የሚበላው :
ስለዚህ : ሰው : ሁሉ : እንደሚገባ : እንገባለን ።"

ደብተራ : መንበሩና : በዛብህ : ወደ : ግቢ : ሲሄዱ : ገና :
ከሩቅ : ነጋሪት : እያስተጋባ : "ገብር : እር- እር- ገብር" ሲል : በዛ
ብህ : ሰማና : " የምን : ነጋሪት : ነው : ይህ : የምንሰማው ?"
አለ ።

" ሰውን : ለግብር : የሚጠራ : ነው ።"

" ሁልጊዜም : ሰው : ግብር : የሚበላ : እንዲህ : በነጋሪት
እየተጠራ : ነው ?"

"አዎ : ግብር : ሲሆን : አዎ ። ከዛሬ : ቀደም : አይተህ : አታ
ውቅም ?"

"የለም : አይቼ : አላውቅም ።"

"ማየቱ : ጥሩ : ነው : መብላቱን : ግን : እኔ : አልወደውም:
ስለዚህ : ነው : ዛሬ : እንኳዋ : ካህኑ : ሁሉ : ሲሄድ : እኔ : ተለ
ይቼ : ቀርቼ : የነበረ ። ታዲያ : እየውልህ : በኔ : ጉሮሮ : ውረድ :
ያለው : እህል : ውሀ : የማይቀር : ሆኖ : ነጋድራስን : ምክናያት:
አድርጎ : አመጣኝ ። ነጋድራስ : ባለብርቱ : ውለታየ : ናቸው ።
ካገሬ : አምጥተው : ስራ : እስካገኝ : ስንቅ : ሰጥተው : እዚህ :
ያደረሱኝ : እሳቸው : ናቸው ። ታዲያ : እኔ : ምንም : አድርጌላ
ቸው : አላውቅም : ሲመጡ : እንኳዋ : ጠይቂያቸው : አላውቅም።"



" በጣም : ጥሩ : ሰው : ናቸው ።" አለ : በዛብህ ።

እግቢ : ሲደርሱ : ከመጀመሪያው : አጥር : ውጭ : ያለውን :
ሰፊ : ሜዳ : በቅሎና : በቅሎ : ያዥ : አሽከር : ሞልቶታል ።
ከመጀመሪያው : አጥር : እስከ : ሁለተኛው : ያለውን : ሰፊ :
ሜዳ : ሰው : ብቻ : ሞልቶታል ። ከዚያ : አግብር : መብያው :
አዳራሽ : ድረስ : አለፍ : አለፍ : እያለ : ብዙ : አቁዋራጭ : አጥር :
ይታያል ። በያቁዋራጩ : መሀከል : ያለው : ሜዳ : ሁሉ : እታች :
ሆኖ : ሲመለከቱት : መላወሻ : የሌለበት : ሰው : ብቻ : ጥቅጥቅ :
ብሎ : የሞላው : መስሎ : ይታያል ። ነገር : ግን : ሳያቋርጥ :
የሚጎርፈው : ሰው : ሁሉ : እዬመጣ : በላይ : በላይ : ሲጨመር :
ያ : ጥቅጥቅ : ብሎ : የሞላ : የሚመስለው : ግቢ : ሁሉንም : እዬ
ተቀበለ : ይውጣል ።

እንዳንዶቹ : መኩዋንንት : ታጅበው : መጥተው : ገና :
የመጀመሪያውን : በር : ሳይገቡ : ከበቅሎ : ይወርዱና : እዚያው :
ውጭ : አደግድገው : አጀባቸውን : ትተው : የሁለተኛውን :
በር : ገብተው : እዚያ : ያርፋሉ ። እንዳንዶቹ : በበቅሎ : እንዳሉ :
የመጀመሪያውን : በር : ገብተው : እዚያ : ይወርዱና : አደግድ
ድገው : የሶስተኛውን : በር : ሲገቡ : ይታያሉ ። እንዲሁም : እን
ደዬማእርጋቸው : ከሶስተኛው : እስከ : መጨረሻው : አቁ
ዋራጭ : በር : ድረስ : በበቅሎ : እንደ : ተቀመጡ : ሲገቡ : የሚ
ታዩ : ነበሩ ። ስም : የለሹ : ተራው : ሰው : ግን : እንኩዋን : በበ
ቅሎ : ተቀምጦ : በግሩም : ቆሞ : ሁለተኛውን : በር : መግባት :
አይችልም ።

ያ : ሁሉ : ቁጥሩ : ይህን : ያክል : ነው : ተብሎ : ሊገመት :
የማችል : እጅግ : ብዙ : ህዝብ : የመጀመሪያውን : በር : አንድ :
ላይ : እዬገባ : ከዚያ : እስካዳራሹ : ባሉት : ብዙ : ጠባብ : በሮች :
እዬተጣራ : በዬማእርጉ : ሲቀመጥ : ከረፈደ : በሁዋላ : ከሁለ
ተኛው : ጀምሮ : ወደ : ላይ : ያሉት : በሮች : ሁሉ : ተዘጉና :
እላይ : አዳራሹ : አጠገብ : ከተቀመጡት : መኩዋንንት : ጀምሮ :
ለግብር : መኮልኮል : ተጀመረ ።

በዛብህ : የህዝቡን : ብዛት : ሲያይ : እዚያ : እሱ :
በነበረበት : ለሰፈረው : ተራ : ህዝብ : ያነሉት : ፈንታ : ይደ

ርሰዋል ፡ ብሎ ፡ አልገመተም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ባዳራሹ ፡ አጠገብና ፡ ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ካለው ፡ አቁዋራጭ ፡ ውጪ ፡ በነበረው ፡ ሜዳ ፡ የተቀመጠው ፡ መኩዋንንት ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እዬተኮለኮለ ፡ በጸጥታና ፡ መልክ ፡ ባለው ፡ አሆሁዋን ፡ ከገባ ፡ በሁዋላ ፡ ሌላው ፡ ከዚህ ፡ መሰለ ፡ እዬተባለ ፡ በጅምላ ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ መንጋ ፡ እዬተነዳ ፡ መግባት ፡ ስለ ጀመረ ፡ ከሁለት ፡ ሰአት ፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እላይ ፡ ግብሩ ፡ ከሚበላበት ፡ አዳራሽ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሁለተኛው ፡ አቁዋራጭ ፡ ድረስ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ ሞልቶ ፡ ምን ፡ ቦታ ፡ ይበቃው ፡ ይሆን ፡ ይባል ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ገብቶ ፡ አልቆ ፡ በዛብህ ፡ የነበረበት ፡ የተራው ፡ ህዝብ ፡ ፈንታ ፡ ደረሰ ። ብቻ ፡ ያገባበቱ ፡ ስነ ፡ ስራት ፡ እንደ ፡ በዛብህ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለሚያየው ፡ ሰው ፡ ከማስገረሙም ፡ ሌላ ፡ እጅግ ፡ የሚያስቅቅ ፡ ነበረ ።

ከላይ ፡ ካዳራሹ ፡ አጠገብ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መጀመሪያው ፡ በር ፡ ድረስ ፡ በያቁዋራጩ ፡ በሮና ፡ ባካባቢው ፡ የነበረው ፡ የዘልካይ ፡ ብዛት ፡ ቁጥሩ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ የሚያስቸግር ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ አጋፋሪ ፡ የያዘው ፡ ረጃጅም ፡ ጨፈቃ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ቢሰበሰብ ፡ አንድ ፡ አዳራሽ ፡ ይሰራል ።

የበላይ ፡ አጋፋሪዎች ፡ አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ቦታ ፡ አይተው ፡ ሰው ፡ በርከት ፡ ብሎ ፡ እንዲገባ ፡ ሲያዝዙ ፡ ሰው ፡ በሰፈረበት ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ አጋፋሪ ፡ ከዚህ ፡ መለስ ፡ ተነሱ ፡ ይልና ፡ በመንጋ ፡ ያዝዛል ። ከዚያ ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተነስቶ ፡ እዬተራበሸ ፡ አቅም ፡ የሌለው ፡ ሲወድቅ ፡ አቅም ፡ ያለው ፡ በላዩ ፡ እዬቆመ ፡ አጋፋሪዎች ፡ ሲደበድቡት ፡ ጨፈቃቸው ፡ በላዩ ፡ እየተሰባበረ ፡ በሩን ፡ ለመግባት ፡ ሲሮጥ ፡ ከሞት ፡ የሚሸሽ ፡ እንጂ ፡ መብል ፡ የሚፈልግ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ። እንዲህ ፡ እዬተራበሸ ፡ ሁሉም ፡ አይኑን ፡ እዬጨፈነ ፡ የሚቆምበትን ፡ ሳያውቅ ፡ እጁን ፡ የገዛ ፡ አካሉ ፡ ክፍል ፡ እንዳልሆነ ፡ ሁሉ ፡ በላዩ ፡ ለሚወርድበት ፡ የጨፈቃ ፡ መአት ፡ እዬጋረደ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አጋፋሪዎችንም ፡ አሽንፎ ፡ እንደ ፡



ውሀ ፡ ሙላት ፡ ጠርጎ ፡ ይዞዋቸው ፡ ይገባል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከታች ፡ አመጣጡን ፡ ያዩና ፡ አጋፋሪዎች ፡ ቶሎ ፡ ተረዳድተው ፡ በሩን ፡ ዘግተው ፡ በጨፈቃ ፡ ደብድበው ፡ ይመልሱታል ።

ከሁለተኛው ፡ አቁዋራጭ ፡ ውስጥ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ እዬተነዳ ፡ እዬተነሳ ፡ ሆራ ፡ እንደሸተተው ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ አፍንጫውን ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲንጋጋ ፡ በግድ ፡ እዬተደበደበ ፡ እዬተመለሰ ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲታመስ ፡ ቆይቶ ፡ ገብቶ ፡ ሲያልቅ ፡ በዛብህ ፡ በነበረበት ፡ ሜዳ ፡ የነበረው ፡ ህዝብ ፡ መግባት ፡ ጀመረ ።

እዚያ ፡ የነበረው ፡ ህዝብ ፡ የመጨረሻው ፡ ስም ፡ የለሹ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ዱላው ፡ ረብሻው ፡ ድብልቅልቁ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስመርጥ ፡ ነበር ። በዛብህ ፡ ገና ፡ አጀማመሩን ፡ ሲያይ ፡ እዚያ ፡ ረብሻ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በጤናው ፡ ለመውጣት ፡ የማይችል ፡ ስለ ፡ መሰለው ፡ ግብር ፡ ለመግባት ፡ ጭራሽ ፡ አለመሞከርን ፡ መረጠና ፡ በሩቁ ፡ አጥሩ ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ ሰቀላ ፡ ቤት ፡ ስላዬ ፡ ወደ ዚያ ፡ ሸሸ ።

እሰቀላው ፡ ጥግ ፡ ሁለት ፡ ጭዋ ፡ ሰዎች ፡ አዘን ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ ሁሉ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ይነጋገራሉ ።

በዛብህ ፡ ግብር ፡ መብላቱም ፡ ቢቀርበት ፡ ለመብላት ፡ የሚፈልጉት ፡ የሚያደርጉትን ፡ ተጋድሎና ፡ ያን ፡ የሚያስገርም ፡ ረብሻ ፡ ማየቱ ፡ እንዳይቀርበት ፡ ከሩቅ ፡ የሚመለከትበት ፡ ቦታ ፡ ሲፈልግ ፡ እሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ ቁዋጥኝ ፡ ደንጋይ ፡ ስላዬ ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ተቀመጠ ። ነገር ፡ ግን ፡ ረብሻው ፡ ያስነሳው ፡ አጉዋራ ፡ ግቢውንና ፡ ከግቢውም ፡ በላይ ፡ ጠፈሩን ፡ በሙሉ ፡ እንደ ፡ ከባድ ፡ ጭጋግ ፡ ሸፍኖት ፡ ስለነበረ ፡ እዚያ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ትግልና ፡ ድብልቅልቅ ፡ የሚነሳውን ፡ አጉዋራ ፡ አይቶ ፡ ከመገመት ፡ በቀር ፡ ማየት ፡ አይቻልም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ በዛብህ ፡ አጉዋራውን ፡ ብቻ ፡ እያዬ ፡ አጉዋራው ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ትግል ፡ እዬገመተ ፡ ተቀመጠ ።

“ ሊጋፋሪ ፡ ተምትሜ ፡ ጉቦ ፡ ሳልሰጥ ፡ ኧረቸኮ ፡ ነው --- የምስብ ፡ ጉዋደኞች ፡እመሁዋንንት ፡ ማረፊያ ፡ ሲኸመጡ--- እኔን ፡ ከነሱ ፡ ለይቶ ፡ እዚህ ፡ ተኧምጠህ ፡ ጠብእ ፡ እነሱ ፡ ሲገቡ ፡ ትጠራለህ ፡ ያለኝ ። እየው ፡ አሁን ፡ እኛ ፡ እዚህ ፡ ተኧምጠን ፡ ተራውን ፡ ሰው ፡ መደዴውን ፡ ማስገባት ፡ ጀመሩ ።” አሉ ፡ አዝነው ፡ ከተቀመጡት ፡ አንዱ ፡ እንባቸው ፡ ባይናቸው ፡ ቅርር ፡ ብሎ ፡ እዩታዩ ።

“ እኔስ ፡ ያው ፡ ጉቦ ፡ ባለመስጠቴ ፡ አይደል ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ጥፋት ፡ ተገኝብኝ ! ከጦር ፡ ሜዳ ፡ ስሸሽ ፡ ታዩሁ ? ወይስ ፡ የጌታ ፡ ትእዛዝ ፡ አልፈጽም ፡ አልሁ ? እንደ ፡ ግዞተኛ ፡ ከጉዋደኞቸ ፡ ተለይቼ ፡ ከገዛ ፡ አሽከሮቼ ፡ በሁዋላ ፡ እንድቀር ፡ መደረጉ ፡ ጉቦ ፡ ባለመስጠቴ ፡ ነው ! ” አሉ ፡ ሁለተኛው ።

“ የንጉስ ፡ ግብርና ፡ ኡርባን ፡ አንድ ፡ በመሆኑ ፡ ከረድኤቱ ፡ ለመሀፈልና ፡ ጌታችን ፡ ከተራ ፡ ህዝብ ፡ እንድንለይበት ፡ የሰጡንን ፡ ደረጃ ፡ ለመጠበእ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እንጀራማ ፡ በዬቤታችን ፡ ከኛ ፡ ተርፎ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እናበላ ፡ የለ ? ” አሉ ፡ አይናቸውን ፡ እንባ ፡ የሞላው ፡ ሰው ።

ሁለቱ ፡ መኩዋንንት ፡ እንዲህ ፡ እያዘኑ ፡ ሲወያዩ ፡ ከከልካዮች ፡ አንዱ ፡ እዬሮጠ ፡ መጥቶ ፡ አይናቸው ፡ እንባ ፡ ያዘለውን ፡ መኮንን ፡ ጠራቸው ።

“ አሁን ፡ ከማን ፡ ጋር ? ልታስኧምጡኝ ፡ ነው ፡ የምትጠሩኝ ፡ አጋፋሪ ፡ ጉደታ ? ካሽከሮች ፡ ጋር ፡ ልታስኧምጡኝ ፡ ነው ? ግዴለም ፡ ተውት ፡ እግዚአብሄር ፡ ይስጥልኝ ! ያደባባይ ፡ አምላክ ፡ ያፈራርደን ፡ ብቻ ! እንግዴህስ ፡ እቤቴ ፡ እሄዳለሁ !” አሉና ፡ ሰውዬው ፡ ለመሄድ ፡ ሲነሱ ፦

“ ኢሂ ! ኢንጉሲን ፡ ጊብሪሞ ፡ መርጌጣትኖ ? ና ፡ ማሊስ ! ” አለ ፡ አጋፋሪ ፡ ጉደታ ፡ በብርቱ ፡ ቁጣ ፡ የተሰባበረ ፡ ጩፈቃውን ፡ አስቀድሞ ።

አኩርፈው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሊሄዱ ፡ የተነሱት ፡ ሰውዬ ፡ ታማዶ ፡ የቆዬው ፡ ቁጣቸው ፡ ገንፍሎ ፡ ከልካዩን ፡ ለማነቅ ፡ እዬተንቀጠቀጡ ፡ እጃቸውን ፡ ከዘረጉ ፡ በሁዋላ ፡ የኋጉስ ፡ ግብር ፡ አልበላም ፡ ብለው ፡ ከከልካይ ፡ ጋር ፡ መጣላታቸው ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችለውን ፡ በመገመትም ፡ ይሁን ፡ በሌላ ፡ ቁጣቸውን ፡ እንደገና ፡ ውጠው ፡ በረድ ፡ ሲሉ ፡ ሲያይ ፡ ከልካዩ ፡ በበኩሉ ፡ በጣም ፡ ተቆጣ ።



“ኢንጉሲን ፡ ጊብሪ ፡ ኢናትን ፡ ኢንጀራኖ ፡ ፊሊጋለሽ ፡ በላል ፡ አልፊሊጋለሽ ፡ አልበላል ! አይ ፡ ኢናት ፡ አራዳን ፡ ጎርጊ.....ስ ! ኢስቲ ፡ ቂስቂስን ፡ ብላል ፡ ውርዳቲን ፡ መጣለሽ ! ሊቢን ፡ አርጋል ! ኢንጉሲን ፡ ጊብሪ ፡ ጊዲዳት ፡ ባላልኖንጂ ፡ ውዲዳት ፡ ባላልኖ ? ጎ !” አለ ፡ አጋፋሪ ፡ ጉደታ ፡ እኒያን ፡ ሰውዬ ፡ በመናቅና ፡ በመጸየፍ ፡ ቁጣው ፡ እንደሳት ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ሲነድ ፡ እዩታዩ ።

አጋፋሪ ፡ ጉደታና ፡ አኩርፈው ፡ ለመሄድ ፡ የተነሱት ፡ ሰው ፡ ተፋጠው ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ አንድ ፡ ካለባበሳቸውና ፡ ካጀባቸው ፡ የከልካይ ፡ ብዛት ፡ በግምት ፡ ካጋፋሪዎች ፡ ሹማምንት ፡ አንዱ ፡ የሚመስሉ ፡ ሰው ፡ መጡና ፡ ሁለቱንም ፡ አዝነው ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ሲያስጠሩዋቸው ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ አዘን ፡ ወዲያው ፡ ተረስቶ ፡ ሁለቱም ፡ ፊታቸው ፡ በቅጥበት ፡ በደስታ ፡ በርቶ ፡ ያጋፋሪዎችን ፡ ሹም ፡ ተከትለው ፡ ሄዱ ።

በዛብህ ፡ የንጉስ ፡ ግብር ፡ መብላት ፡ ግዴታ ፡ እንጂ ፡ ውዴታ ፡ አለመሆኑን ፡ ካጋፋሪ ፡ ጉደታ ፡ ሲሰማ ፡ አጋፋሪው ፡ ካኮረፉት ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ እዬተጨቃጨቀ፡ልብ፡ሳያደርገው ፡ ቀስ፡ ብሎ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ደንጋይ ፡ ወረደና ፡ ሄዶ ፡ ግብር ፡ ለመብላት ፡ ከሚተራመሰው ፡ ህዝብ ፡ ጋር ፡ ተጨመረ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የሚበዛው ፡ ሰው ፡ ገብቶ ፡ የቀረው ፡ ጥቂት ፡ ስለ፡ ነበረ ፡ ዱላውም ፡ ረብሻውም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ተቀንሶ ፡ ብዙ ፡ ሳይንገላታና ፡ ዱላም ፡ ሳያገኘው ፡ ገባ ።

እንደ ፡ ገባ ፡ አብሮት ፡ የገባው ፡ ሁሉ ፡ ደህና ፡ ቦታ ፡ ፍለጋ ፡ እዬጣለው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሲሮጥ ፡ እበሩ ፡ አጠገብ ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ ስላገኘ ፡ ሳይገፋ ፡ ለመውጣትም ፡ እንዲመቸው ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ እዚያው ፡ ተቀመጠና ፡ መብላቱን ፡ ትቶ ፡ አዳራሹንና ፡ የግብሩን ፡ ስነ ፡ ስራት ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ።
ያዳራሹ ፡ መጠን ፡ በወርዱም ፡ ሆነ ፡ በቁመቱ ፡ እስ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ሆኖ ፡ ዳርቻውን ፡ አጣርቶ ፡ ለማየት ፡ አይቻልም ።

ልክ ፡ በመግቢያው ፡ በር ፡ እንጣር ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ ሲል ፡ ባንድ ፡ ከፍተኛ ፡ ድልዳል ፡ ላይ ፡ ከራት ፡ በኩል ፡ በሰፊው ፡ ግልጥ ፡ የሆነ ፡ ጠርዙ ፡ ሁሉ ፡ በወርቅ ፡ የተከፈፈና ፡ ራሱም ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ የሆነ ፡ ስፋቱ ፡ ካንድ ፡ መጠነኛ ፡ ቤት ፡ የማያንስ ፡ አጎበር ፡ ይታያል ። እዚያ ፡ አጎበር ፡ ውስጥ ፡ እንዲሁ ፡ በወርቅና ፡ የቀለሙ ፡ ሁብር ፡ የብርሃን ፡ ጸዳል ፡ ተከትሎ እየተለዋወጠ ፡ አይን ፡ በሚያሳስት ፡ ዘር ፡ ያጌጠ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዙፋን ፡ ተዘርግቶ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የለበሰው ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ ጸሀይ ፡ ጮራ ፡ አይን ፡ የሚለግጥ ፡ ሰው ፡ ተቀምጦዋል ፡ "እእ . . . ! እኒያ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ ጃንሆይ ፡ ናቸው ፡ "አለ ፡ በዛብህ። ከዙፋኑ ፡ አካባቢ ፡ እድልዳሉ ፡ ላይ፡የተቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ጸደቁ ፡ ነፍሳት ፡ ከጌታቸው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አብረው ፡ የሚካፈሉ ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ። ስጋውን ፡ በዐሳሳ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ የሲኃ ፡ መልከኞች ፡ ቀሚስ ፡ አልብሰው ፡ እየተሸከሙላቸው ፡ ጠጁ ፡ ባሳላፊዎች ፡ እጅ ፡ የበሰለ ፡ እንኮይ ፡ መስሎ ፡ ተንዠርጎ ፡ እየቀረበላቸው ፡ በጸጥታ ፡ ሲበሉ ፡ ሲጠጡ ፡ በውነት ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ ይመስላሉ ። ከዙፋኑ ፡ አቅራቢያ ፡ ድልዳሉን ፡ ከበው ፡ የቆሙት ፡ አምዶች ፡ እንከርዋ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለም ፡ ባለው ፡ ጨርቅ ፡ ተሸልመው ፡ ከሩቅ ፡ ሲታዩ ፡ ላይን ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ያሰኛሉ ። ከዙፋኑ ፡ ራቅ ፡ ከድልዳሉ ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሲሄድ ፡ ግን ፡ የሁሉም ፡ አይነቱ ፡ ይለወጣል ። ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ከድልዳሉ ፡ በታች ፡ አደራሹን ፡ በወርዱም ፡ በቁመቱም ፡ ከዳር ፡ እስከዳር ፡ የሞላው ፡ ህዝብ ፡ አንዱ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ እየተደራረበ ፡ ሰፍሮ ፡ የሚተራመስ ፡ የንብ ፡ ሰራዊት ፡ እንጂ ፡ በተራ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚበላና ፡ የሚጠጣ ፡ ሰው ፡ አይመስልም ። ስጋውን ፡ መልከኞች ፡ ሙዳ ፡ ሙዳ ፡ አድርገው ፡ እየቆራረጡ ፡ በሳጠራ ፡ ሞልተው ፡ አሸክመው ፡ ያመጡና ፡ ከሩቅ ፡ እየወረወሩ ፡ አንዱን ፡ ፊቱን ፡ ሌላውን ፡ ደረቱን ፡ ሲሉት ፡ ልበኛ ፡ ቀልቡ ፡ ያስቀረዋል ፡ የዘነጋ ፡ እምልጦት ፡ አመራት ፡ ይጠይቅበታል ። ጠጅ ፡ አሳላፊዎች ፡ ጠላት ፡ እንደሚያሳድዳቸው ፡ እየተጣደፉ ፡ ጠጁን ፡ በኩባያ ፡ እየቀዱ ፡ ሲያድሉ ፡ በሚጠጡት ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡



እስኪደርስ : ግማሹ : ያክል : በሰውነታቸውም : በልብሳቸውም : ይፈሳል : ወዲያው : የተረፈውን : ቢጨርሱም : ባይጨርሱም : ላልደረሰው : ለማድረስ : ኩባያውን : ከጃቸው : ነጥቀው : ይወስዱባቸዋል :: ይህ : ሲሆን : የኩባያውና : የቢላዋው : ኩዋኩዋታ : ያሳላፊውና : ያቅራቢው : ያጋፋሪው : ጫጫታ : በውነት : ራስ : ያሳምማል። አዳራሹ : ውስጥ : የቆሙትን : ወጋግራዎች : እየተደገፉ : የቆሙ : ብዙ : አዝማሪዎች: አሉ :: ነገር : ግን : እጃቸው : መሰንቆውን : ሲገዘግዝ : ያንገታቸውም : የደም : ስር : ተገትሮ : አፋቸው : በሙሉና : በከፊል : ሲከፈት : በማየት : የሚያዘምሩ : መሆናቸውን : ከመገመት : በቀር : የመሰንቆውም : ሆነ : የነሱ : ድምጽ : በጭራሽ : አይሰማም :: እንዲሁም : ጥሩምበኞች : እምቢልተኞችና : መለከተኞች : እያደገደጉ : ተደርድረው : መሳሪያቸውን : በያፋቸው : ለግበው : ጉንጫቸው : እንደፊኛ : ተነፍቶ : አይናቸው : ፈጦ : የደም : ስራቸው : በዬግንባራቸው : ተገትሮ : ሲታዩ : ሁሉም : በዬመሳሪያቸው : ሲጫወቱ : ፎቶግራፍ : የተነሱ : ምስሎች : እንጂ : ያነሰት : እዚያ : ቆመው : የሚነፉ : ነፍስና : ስጋ : ያላቸው : ሰዎች : አይመስሉም ::

በዛብህ : ያነሰት : እቤተ : መንግስቱ : አደባባይ : ከደረሰ : ጀምሮ : ሲያየው : የዋለውና : ያንጊዜም : እዚያ : ግብር : ላይ : ተቀምጦ : የሚያየው : ሁሉ : ስለ : ቤተ : መንግስቱ : ከነበረው : አሳብና : ግምት : በጭራሽ : የተለዬ : ሆኖበት : በመገረም : ፊት : ፍዝዝ : ብሎ : ሲመለከት : በጎኑ : የተቀመጠው : ሰው : በክርን : ጎሰም : አደረገና : ወደጆሮው : ቀረብ : ብሎ "ለማህ ? ወንድሜ : እንግዲህኮ : ጠጅ : ከታደለ : ያስወጡናል! ስለዚህ : መቸም : ግብር : በልቼ : መጣሁ : እንጂ : አይቸ : መጣሁ : አይባልምና ይህን : ለማለት : እንዲመችህ : ባይሆን : ከስጋው : ትንሽ : ብላ : " አለው ::

"እእ ? እሺ :" አለና : በዛብህ : አይኑን : ወደንጀራው : መለስ : ቢያደርግ : እንኩዋን : ለመብላት : ለማየቱም : የሚያስፈራራ : ሆነበት :: እንጀራው : ከጥቁር : ጭቃና : ከሳር : በስሉ : ተጠፍጥፎ : የደረቀ : እንጂ : ከህል : የተጋገረ : እን

ጀራ አይመስልም ። ወጡም ፡ እንዲሁ ፡ ወፈር ፡ ብሎ ፡ የተበ ጠበጠ ፡ ጭቃ ፡ ይመስላል ። ከዚያ ፡ እንጀራውን ፡ ተወና፡ ከስጋው ፡ ልብላ ፡ ልተው ፡ እያለ ፡ ሲያመነታ ፡

"ተነሱ ፡ በል ! ተመለሱ ፡ በል!" አለ ፡ እዚያ ፡ አጠገብ ፡ ከቆሙት ፡ ያጋፋሪዎች ፡ ሹሞች ፡ አንዱ ። ከዚያ ፡ መጋፋቱ ማዳፋቱ ፡ ረብሻው ፡ ድብልቅልቁ ፡ እንደገና ፡ ተጀመረ ። በዛብህ ፡ እስዴቃው ፡ መጨረሻ ፡ እበሩ ፡ አጠገብ ፡ ስለነበረ ፡ የተቀመጠ ፡ ቶሎ ፡ ተነስቶ ፡ በገባበት ፡ በር ፡ ሲወጣ ፡ ሲሄድ ፡ አንዱ ፡ ከልካይ ፡ አንገቱን ፡ ይዞ ፡ ቢወረውረው ፡ ከመሬት ፡ ተደባለቀ ። ከዚያ ፡ ተነስቶ ፡ እንደገና ፡ ወደበሩ ፡ ለመሄድ ፡ ሲሞክር ፡ "ወየታባቱ ፡ ሲሄድ ፡ ነው ? በል ! እዬተመላለሰ ፡ ሲበላ ፡ ሲውል ፡ አስቦዋል?" አለ ፡ ከልካዩ ፡ ስመማታት ፡ ዱላ ውን ፡ እያመቻቸ ። በዛብህ ፡ ግራ ፡ ገባውና ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚወጣበት ፡ ሌላ ፡ በር ፡ መሆኑን ፡ ስላዬ ፡ ቶሎ ፡ ወደዚያ ፡ ሮጦ ፡ አመለጠ ። ከዚያ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩን ፡ እበሩ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ሲጠብቀው ፡ አገኘ ።

"የት ፡ ጠፋሽኝ ? " አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ።

"እስዎ ፡ ጠፉኝ ፡ እንጂ ! ጭራሽ ፡ አላገኝዎም ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጬ ፡ ነበር ።"

"ወዲያው ፡ የመጀመሪያውን ፡ በር ፡ እንደገባን ፡ ካንድ ፡ አጋፋሪ ፡ ጋር ፡ ስነጋገር ፡ ባጠገቤ ፡ አልነበርህም ?"

"ያንጊዜማ ፡ አብሬዎ ፡ ነበርሁ ፡ የህዝቡ ፡ ብዛት ፡ አስገ ርሞኝ ፡ ስዚህ ፡ ሁሉ ፡ ህዝብ ፡ የሚበላ ፡ ነገርስ ፡ ቢገኝ ፡ የሚበ ላበት ፡ ቦታ ፡ ይገኛል ፡ ወይ ፡ እያልሁ ፡ በማያገባኝ ፡ ጉዳይ ፡ ገብቼ ፡ ይህን ፡ ሳወጣ ፡ ሳወርድ ፡ ቆይቼ ፡ ዘወር ፡ ብል ፡ አጣ ሁዎ ።"

"እኔማ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ የማውቀው፡ አጋፊሪ ፡ ስላገ ኘሁ ፡ ላንተም ፡ ለኔም ፡ የተሻለ ፡ ቦታ ፡ እንዲሰጠን ፡ ትንሽ ፡ አጎረስሁትና ፡ እዬመራ ፡ የሁለተኛውን ፡ አቁዋራጭ ፡ በር ፡ አስገብቶ ፡ እዚያ ፡ የምቆይበት ፡ ቦታ ፡ ሲሰጠኝ ፡ ተከትለሽ ኛል ፡ መስሎኝ ፡ ዘወር ፡ ብል ፡ ስለጠፋህብኝ ፡ መቸም ፡ ካንተ ፡



ቀድሜ ፡ ገብቼ ፡ መውጣቴ ፡ ስለማይቀር ፡ መውጫውን ፡ ይገር ፡ እስከመጨረሻ ፡ ከጠበቅሁ ፡ አታመልጠኝም ፡ ብዬ ፡ ይሄው ፡ ቅድም ፡ የጠጣሁ ፡ እጠብቅሃለሁ ። "

"አሲቃ ፡ ወጡ ? "

"እሳቸውማ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ገብተው ፡ ወደ ፡ መጨ ረሻ ፡ ከሚወጡት ፡ መሀከል ፡ ናቸው ። እንግዲህ ፡ መውጫ ቸው ፡ ነው ። "

"እኔማ ፡ በገባሁበት ፡ የምንጠጣ ፡ መስሎኝ ፡ ተመለሱ ፡ ሲባል ፡ ሳልገፋ ፡ ቶሎ ፡ ለመውጣት ፡ ወደ ፡ ገባሁበት ፡ በር ፡ ስሮጥ ፡ አጋፋሪው ፡ እዬተመላለስህ ፡ ስትበላ ፡ ልትውል ፡ ነው ፡ ወይ ፡ ብሎ ፡ ወርውሮ ፡ ባለኝና ፡ ይዬትልዎ ፡ ስወድቅ ፡ ፊቴ ፡ ተጋጠ ። "አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ ።

"አዬ ---ጎደቶህል ! አጋፋሪዎች ፡ ጨካኞች ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ የማያዩ ፡ ናቸው ። "

"እኔማ ፡ አዳራሹ ፡ በፊቱ ፡ እዬዋጠ ፡ በሁዋላው ፡ የሚ ተፋ ፡ መሆኑን ፡ ሳላውቅና ፡ የሚገባ ፡ እንጂ ፡ የሚወጣ ፡ ሰው ፡ ስላላዬሁ ፡ እንደ'ት ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ የሚገባ ውን ፡ ሁሉ ፡ እዬከተተ ፡ ዝም ፡ የሚል ፡ ብዬ ፡ ገርሞኝ ፡ ነበር ። "

በዛብህና ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ እመውጫው ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ቆመው ፡ ሲነጋገሩ ፡ የሩፋኤል ፡ አሲቃ ፡ ብቅ ፡ ስላሉ ፡ ሁለቱም ፡ ወደሳቸው ፡ ሄደው ፡ እጅ ፡ ነሱ ።

"አአ ---ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ምን ፡ ታደርጋላችሁ - እዚህ ፡ ቆማችሁ ? ይህ ፡ በቀደም ፡ እማነጋግር ፡ ሲሖሬ ፡ ያዬ ሁት ፡ ልጅ ፡ አይደለም ? "አሉ ፡ አሲቃው ፡ በዛብህን ፡ ትኩር ፡ አድርገው ፡ እያዩ ።

"አዎን ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ እሱን ፡ ከጌታዬ ፡ ጋር ፡ ለማስተ ዋወቅ ፡ ጌታዬን ፡ ነበር ፡ የምንጠብቀው ፡ "አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ።

"ማለፊያ ፡ ማለፊያ ፡ ከየት ፡ መጣህ ? "

"ከጎጃም ፡" አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ማፈር ፡ ብሎ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡

"ድንቅ ፡ ድንቅ ፡ ሩፋኤል ፡ ማገልገል ፡ ትሻለህ ? "
"ቦታ ፡ ቢገኝልኝማ —ለሱ ፡ ደጅ ፡ ለመጥናት ፡ ነበር ። "
"እይነተኛ ፡ ሙያህ ፡ ምንድነው ?"
"ለዜማና ፡ ለቅኔ ፡ መምህርነት ፡ ተመርቄያለሁ ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ ሳለሁ ፡ መጽሀፍም ፡ አስቀጥል ፡ ነበር ። "

"እንዲያው ፡ ድምጼ ፡ መልካም ፡ ብቻ ፡ አይደለህም ፡ ባለሙያም ፡ ነህና ! "አሉ ፡ አለቃ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብለው ።

"ነገ ፡ እቤት ፡ ድረስ ፡ ይዘሽው ፡ ና ፡ "አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ዞወር ፡ ብለው ።

ከዚያ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩና ፡ በዛብህ ፡ አለቃን ፡ በቅሎ ዋቸውና ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ባሉበት ፡ አድርሰዋቸው ወደ ፡ ጉለሌ ፡ ሲሄዱ ፡–

"እንኩዋን ፡ ደሳለህ ! እንግዲህ ፡ ምንድነው ፡ የደስደስ ፡ የምትሰጠኝ ? "አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ።
"ስለምን ? "አለ ፡ በዛብህ ።
"ስራ ፡ ስላገኘህ ፡ "
"ገና ፡ መቼ ፡ አገኘሁ ? "

"አለቃ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ከተናገሩ ፡ ስራ ፡ ሰጡህ ፡ ማለት ፡ ነው ። እኛ ፡ ዘንድ ፡ የነበሩ ፡ ደብተሮች ፡ እየለቀቁ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስለሄዱ ፡ አንዳንድ ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ አለ ፡ የቅኔ ፡ መምህ ራችንም ፡ በቅርቡ ፡ ሞተው ፡ ቦታቸው ክፍት ፡ ነው ። ልጅ ፡ ነህ ፡ ይሉ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እሱንማ ፡ ቢሰጡህ ፡ ጌትነት ፡ ነበር ። "

"ደመወዙ ፡ ምን ፡ ያክል ፡ ነው ? "

"ባመት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አንድ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ለም ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ማደሪያና ፡ በወር ፡ ሶስት ፡ ዳውላ ፡ እህል ፡ አለው ። "

"እንግዲህ ፡ እሱም ፡ ይረዱኝ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ ዘመድ ፡ አለኝ ? ስለሙያዩ ፡ ልብዎን ፡ ሞልተው ፡ ቢናገሩ ፡ የማሳፍርዎ ፡ አይደለሁም ። ለቅኔ ፡ መምህርነት ፡ መመረቅ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ዲማ ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ መምህራን ፡ ወንበር ፡ ተሰጥቶኝ ፡ ብዙ ፡ ተማሪ ፡



አስተምር ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ታሪክ ፡ ይሁን ፡ ሰምና ፡ ወርቅ ፡ ወይም ፡ ሀብር ፡ ቅኔ ፡ ከጉባኤ ፡ ቃና ፡ እስከ ፡ መወድስ ፡ እስከ ፡ እጣንሞገር ፡ እፊታቸው ፡ ዘርፌ ፡ ላሳይ ፡ እችላለሁ ። "

"ትልቅ ፡ እድል ፡ ነው ! ትልቅ ፡ እድል ! በል ፡ እስቲ ፡ ለሁሉም ፡ እግዚአብሄር ፡ ይርዳ ፡ እንኩዋን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሙያ ፡ እያለህ ፡ ባይኖርህም ፡ ለነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ ስል ፡ የምችለውን ፡ ያክል ፡ ብደክም ፡ ደስታዬ ፡ ነው ። መቼም ፡ ቀድሞ ፡ እንዳልሁህ ፡ አለቃ ፡ ስራ ፡ ሰጥተው ፡ ሩፋኤል ፡ እንድትሆንላቸው ፡ መፈለጋቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ መሆኑን ፡ አውቃለሁ ፡ ብቻ ፡ ላረጋግጥልህ ፡ የማልችልና ፡ እግዚአብሄር ፡ እንዲረዳን ፡ መለመን ፡ የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ እንዲሰጡህ ፡ ነው ። ብችል ፡ እስቲ ፡ ማታ ፡ ሄጄ ፡ እሞክራለሁ ። "

በዛብህ ፡ ያን ፡ ሌሊት ፡ እንቅልፍ ፡ አልተኛም ። የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ ቦታ ፡ አግኝቶ ፡ ጥሩ ፡ ቤት ፡ ተከራይቶ ፡ ስልጡን ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አሽከሮች ፡ ቀጥሮ ፡ ሰብለን ፡ ጉዱ ፡ ካሣ ፡ ሰርቆ ፡ አምጥቶለት ፡ ምሽቱ ፡ ሆና ! ማንንም ፡ ሳይፈሩና ፡ ከማንም ፡ ሳይሸሽጉ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ " ሊቅ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ " እያለ ፡ እየተገረመባቸው ፡ የሚኖሩት ፡ የደስታና ፡ የፍቅር ፡ ኑሮ ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ይታዩውና ፡ ወዲያው ፡ ይህ ፡ ምኞት ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ሁሉ ፡ ልቡን ፡ የደስታ ፡ ሙቀት ፡ ሲያግለው ፡ ይሰማዋል ። ከዚያ ፡ ትንሽ ፡ ይቆይና ፡ "አለቃ ፡ እንቢ ፡ ይሉ ፡ ይሆን ? የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ ባይሰጡኝ ፡ ሌላ ፡ ስራ ፡ እንደማላጣ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ አረጋግጦ ልኛል ። ለመሆኑ ፡ ከኔ ፡ የተሻለ ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ያገኛሉ ? እስቲ ፡ ለሁሉም ፡ እግዚአብሄር ፡ ይርዳ ! " ይላል ። ከዚያ ፡ ቀን ፡ እግቢ ፡ ሄዶ ፡ ሲያየው ፡ የዋለው ፡ ሁሉ ፡ ይታየዋል ። ህዝቡ ፡ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከላይ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ በዱላ ፡ እየተደበደበ ፡ ሲነዳ ፡ እንዲያ ፡ እየተ ደበደበ ፡ ከገባ ፡ በሁዋላ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ እጅግ ነሆዶ ፡ ፊት ፡ እንዲበላ ፡ ተሰናድቶ ፡ የቀረበለት ፡ የእንጀራውና ፡ የወጡ ፡ አይነት ፡ አጋፋሪዎችና ፡ አሳላፊዎች ፡ የሚያስተናግዱበት ፡ ሁኔታ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ታዩው ።" የንጉስ ፡

ግብር ፡ ማለት ፡ ለካስ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነው ! ” አለ ፡ቀን ፡ ሲያየው ፡ የዋለው ፡ ሁሉ ፡ እንደገና ፡ ባይኑ ፡ ህሊናው ፡ ፊት ፡ ተራ ፡ ገብቶ ፡ ሲሄድ ፡ እዩ ተመለከተ ፡ “ ኧረ ፡ ለመሆኑ ! ሙሉ ፡ ኢትዮጵያን ፡ እየገዙ ፡ ከዚያ ፡ የተሻለ ፡ እንጀራና ፡ ወጥ ፡ አጥተው ፡ ነው ፡ ሰውን ፡ በነጋሪት ፡ ጠርተው ፡ እንዲያ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አቅርበው ፡ ብሉ ፡ የሚሉ ? ወይስ ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ባይቆጥሩት ፡ ይሆን ? ሰውስ ፡ ያን ፡ ለማየት ፡ እንኳዋ ፡ የሚያስፈራራ ፡ ነገር ፡ ለመብላት ፡ ያን ፡ ያክል ፡ የሚሰገበገብበት ፡ ምን ፡ ይሆን ?” የንጉስ ፡ ግብር ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንጀራማ ፡ እቤታችን ፡ መች ፡ አጣን ? ” አሉ ፡ ከክል ካዩ ፡ ጋር ፡ የተጣሉት ፡ መኮንን ፡ የንጉስ ፡ ግብር ፡ ዛሬ ፡ እንዳዩሁት ፡ ከሆነ ፡ ጭራሽ ፡ አያስመኝም ! ከድህ ፡ ቤት ፡ ተለምኖ ፡ የሚበላው ፡ ቁራሽ ፡ በስንት ፡ ጣሙ ! የለም ፡ የንጉስ ፡ ግብር ፡ ለመብሉ ፡ አይደለም ፡ የሚፈለገው ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ይኖረዋል ! ምን ፡ ይሆን ? የንጉስ ፡ ግብር ! ግብር ፡ መቸም ፡ እዳ ፡ ነው። ታዲያ ፡ ንጉስ ፡ እዳ ፡ ይከፍላል ? የለም ፡ ህዝብ ፡ ነው ፡ ለንጉስ ፡ እዳ ፡ የሚከፍል ። ነገር ፡ ግን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አልተስማማም ። ህዝቡ ፡ በላ ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ እዳ ፡ ከፈለ ? አአ - - - -? አሁን ፡ አገኘሁት ! ህዝብ ፡ ለንጉስ ፡ የሚከፍለው ፡ የክብር ፡ እዳ ፡ ነው ! ህዝብ፡ ከሰውነት ፡ ወደ ፡ እንስሳነት ፡ ደረጃ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ተገፍቶ ፡ ተመትቶ ፡ የሰውነት ፡ መብቱንና ፡ ክብሩን ፡ ሁሉ ፡ ትቶ ፡ የማይበላ ፡ ነገር ፡ በልቶ ፡ ተንቆ ፡ ተደቅድቆ ፡ ለንጉስ ፡ የሚገዛ ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳይበትና ፡ ንጉሱም ፡ ያን ፡ እያዩ ፡ ደስ ፡ የሚሰኙበት ፡ ዘዴ ፡ ነው ! ከህብቱ ፡ ሀብት ፡ ከፍሎ ፡ እንደሚገብር ፡ ከሰውነቱ ፡ ከፍሎ ፡ ለንጉስ ፡ የሚገብረው ፡ የመንፈስ ፡ ግብር ፡ ነው! ልክ ፡ መሰረቱ ፡ ይህ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ማስረጃውም ፡ ከንጉስና፡ ከትልልቅ ፡ መኰዋንንት ፡ ቤት ፡ በቀር ፡ በተራ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ግብር ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ የለም ። ብዙ ፡ ሰው ፡ ተጠርቶ ፡ የሚበላው ፡ ድግስ ፡ ባዘቦት ፡ የሚበላው ፡ ራትና ፡ ምሳ ፡ ነው ፡ የሚባለው ። ብቻ ፡ ሰው ፡ መሰረቱን ፡ ሳያውቅ ፡ በረዥም ፡ ጊዜ ፡ ልማድ ፡ የውርደቱን ፡ ምልክት ፡ እንደ ፡ ክብር ፡ ምልክት ፡ ቆጥሮት ፡ ለምን ፡ ቀረብኝ ፡ ብሎ ፡ እንደኒያ ፡ ከጉደታ ፡ ጋር ፡ እንደተጣሉት፡



ሰውዬ ፡ ያለቅሳል ። ጉደታ ፡ ይልቅ ፡ ጎበዝ ፡ ነው ። አማርኛው ፡ ይጥፋው ፡ እንጂ ፡ የግብር ፡ መሰረት ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ የሚያውቅ ይመስላል ።” አለ ። ከዚያ ፡ ጉደታ ፡ ኢንጉሲን ፡ ጊብሬ ፡ ጊዲዳት ፡ በላልኖንጂ ፡ ውድዳት ፡ በላልኖ ?” ያለው ፡ ትዝ ፡ አለውና ፡ ብቻውን ፡ ከት ፡ ብሎ ፡ ሳቀ ።

እንጋት ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ እንቅልፍ ፡ ሊወስደው ፡ ሲል ፡ ነጋዴዎች ፡ ሲንጫጩ ፡ ተነሳ ። ከዚያ ፡ ቡና ፡ ጠጥቶ ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ሄደ ።

“አንተ ፡ እድላም ፡ ነህ ፡ እባክህ !” አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ በዛብህን ፡ ከሩቁ ፡ ሲያይ ፡ እንዴት ፡ አደርህ ፡ ከማለቱ ፡ እንኳዋ ፡ አስቀድሞ ።

“ እንዴት ? ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ልቡ ፡ በደስታ ፡ ፈንጥዞ ፡ ካፎቱ ፡ ሊወጣ ፡ እንደ ፡ ፈለገ ፡ ሁሉ ፡ በደረቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲንደፋደፍ ፡ ከሩቅ ፡ እዩተሰማ ።

“እድላም ፡ ነህ ፡ የቅኔ ፡ ችሎታህን ፡ እንደ ፡ ነገርኸኝ ፡ አደርጌ ፡ ትንሽም ፡ ፊዉማምሬ ፡ ስነግራቸው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ “ ደህና ፡ ነው ፡ ስራውን ፡ ይጀምር ፡ ” አሉ ። “ ብቻ - - - - ረስቸ - - - - - - - - ትናንት ፡ ያልነገርሁህ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ። ”

“ምን ?”

“ ቦታው ፡ ከፍተኛ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መሾዋሚያ ፡ ይከፈልበታል፡

“ ምን ፡ ያክል ? ”

“ መቶ ፡ ብር ። ”

“ መቶ ፡ ብርማ ፡ የት ፡ አገኛለሁ ? ”

“ መቶ ፡ ብር ፡ ከሌሎች ፡ የሚቀበሉት ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግ / ፡ አንተን ፡ አጥብቀው ፡ የሚፈልጉህ ፡ ስለሚመስሉ ፡ መቶም ፡ ባይሞላ ፡ ይቀበሉ ፡ ይሆናል ፡ እንዲያው ፡ ግን ፡ እንደማይሰጡህ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። ”

ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ ይሆን ፡ ሲሰሙ ፡ አንድ ፡ ጀምብ ፡ ማርና ፡ አንድ ፡ ጀምብ ፡ ቅቤ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብለው ፡ ለደብተራ ፡

መንበሩ ፡ ቃል ፡ ሰጡ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ በዛብህ ፡ ከራሱ ፡ ሀያ ፡ ብር ፡ ጨምሮ ፡ የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ አገኘ ። ከዚያ ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ ወዳገራቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ስራ ፡ መያዙንና ፡ የሚኖርበትን ፡ ቦታ ፡ ዘርዝሮ ፡ ጽፎ ፡ እግረ ፡ መንገዳቸውን ፡ ሲያልፉ ፡ ዲማ ፡ ለጉዱ ፡ ካሣ ፡ ሰጥተውለት ፡ እንዲያልፉ ፡ አደራ ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸው ።

## ምእራፍ ፡ ፴

## መርዶ ፡

ሰው ፡ ደስታ ፡ የሚያገኘው ፡ ሀብት ፡ በማግኘት ፡ ለነገ ፡ ኹመትና ፡ ሽልማት ፡ በመታጨት ፡ ዜናው ፡ ተስፋፍቶ ፡ በመሰማት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዛብህ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በደረሰ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አገኘ ።

የያዘው ፡ ስራ ፡ ባገልግሎት ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከቆዩት ፡ እንኩዋ ፡ ጥቂት ፡ እድላሞች ፡ ብቻ ፡ ሊደርሱበት ፡ የሚችሉ ፡ እሱም ፡ አገኘዋለሁ ፡ ብሎ ፡ በጭራሽ ፡ ተበፋ ፡ ያላደረገው ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ ስራ ፡ ነው ። ባመት ፡ መቶ ፡ ብርና ፡ በወር ፡ ሶስት ፡ ዳውላ ፡ እህል ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ለም ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ማደሪያ ፡ እንኩዋንስ ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ በወጡ ፡ ማግስት ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ አገልግሎት ፡ በሁዋላም ፡ ቢሆን ፡ ብድር ፡ ይከፍላል ፡ የሚባል ፡ ወገንና ፡ ጉቦ ፡ የሚሰጡት ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ የሌላቸው ፡ የሚያገኙት ፡ አይደለም ። ስሙም ፡ እንደ ፡ የሩሳሌም ፡ ባላዩት ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀና ፡ የገነነ ፡ ሆነ ።

" ከስመጥሩ ፡ ካለቃ ፡ ክንፉ ፡ ተመርቆ ፡ የወጣ ፡ ሊቅ ፡ የሩፋኤልን ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ወንበር ፡ ያዘ ፡ " ተብሎ ፡ እንደተወራ ፡ መልኩን ፡ ያላዩት ፡ ቅኔውን ፡ ያልሰሙት ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ እንዱ ፡ ደመወዙን ፡ እጥፍ ፡ ላድርግ ፡ ሲል ፡ ሌላው ፡ ሁለት ፡ እጥፍ ፡ ላድርግ ፡ ሲል ፡ ደግሞ ፡ ሌላው ፡ ሶስት ፡ እጥፍ ፡ ላድርግ ፡ ሲል ፡ እንዲሁ ፡ እንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ የደመወዝ ፡ ብልጫ ፡ እሰጣለሁ ፡ በማለት ፡ እባብለው ፡ ወደየደብራቸው ፡ ለመውሰድ ፡ ይሻሩበት ፡ ጀመር ። ያዲስ ፡ አበባ ፡ ካህናት ፡ በዩመሀራው ፡ የሚያወሩት ፡ አዲሱ ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ያለቃ ፡ ክንፉ ፡ ደቀመዝሙር ፡ መሆኑንና ፡ የሩፋኤልን ፡ ወሬ ፡ ነበር ። ሩፋኤል ፡ እንኩዋ ፡ በበዛብህ ፡ ምክንያት ፡ ለጊዜው ፡ ስመጥር ፡ ሆነ ፡

ካዲስ ፡ አበባም ፡ ሆነ ፡ ከውጭ ፡ ሩፋኤል ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ የተሰበሰበው ፡ ተማሪ ፡ ቁጥሩ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ አይባልም ። የበዛብህን ፡ ቤት ፡ ከቦ ፡ የተሰራው ፡ የተማሪ ፡ ጎጆ ፡ ሜዳውን ፡ የዘማች ፡ ሰፈር ፡ አስመስለው ። ያውም ፡ ከዬቤቱ ፡ ተመላልሶ ፡ ከሚማረው ፡ ሌላ ፡ ነው ። ጊዜ ፡ ባለፈ ፡ መጠን ፡ እዬተቀነሰ ፡ ሄደ ፡ እንጂ ፡ እመጀመሪያው ፡ ላይማ ፡ ከተማሪ ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ ሜዳው ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፡ የሰፈሩም ፡ ሰው ፡ መመረር ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ።

መቸም ፡ እንኳዋንስ ፡ እንደ ፡ በዛብህ ፡ ያሊቃ ፡ ከንፉን ፡ ትልቅ ፡ ስም ፡ ያስከተለ ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ አዲስ ፡ አስተማሪ ፡ አዲስ ፡ እንደ ፡ ፈለቀ ፡ ጠበል ፡ ዜናው ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ገናና ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በዬጠበሉ ፡ ዞረው ፡ ተስፋ ፡ የቆረጡ ፡ እውሮችና ፡ ደንቆሮዎች ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ በሽተኞች ፡ አዲስ ፡ ጠበል ፡ ፈለቀ ፡ ሲሉዋቸው ፡ ባዲስ ፡ ተስፋ ፡ ወዳዲሱ ፡ ጠበል ፡ እንደሚሽቀዳደሙ ፡ እንዲሁም ፡ የቅኔ ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ ተሰወራቸው ፡ የዜማ ፡ ጣም ፡ ስላልተሰማቸው ፡ ከትምርት ፡ የሸሹ ፡ ትምርት ፡ አልገባቸው ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ በመቁረጥ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ያዲስ ፡ አስተማሪ ፡ ወሬ ፡ ሲሰሙ ፡ ደነዝ ፡ አእምሮዋቸውን ፡ አውጥቶ ፡ ጥሎ ፡ አዲስ ፡ ስለት ፡ አእምሮ ፡ እንደሚተካላቸው ፡ ወደሱ ፡ መጉረፋቸው ፡ የተለመደ ፡ ነው ። እንደነሱ ፡ ባሉት ፡ ላይ ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ እንሄዳለን ፡ ብሎ ፡ ማውራቱ ፡ ክብር ፡ የሚመስላቸው ፡ ዲያቆናት ፡ ተጨምረው ፡ ቅኔ ፡ ቤቱን ፡ የሜዳ ፡ ገበያ ፡ አስመሰሉት ። በሁዋላ ፡ ብቻ ፡ ለመብራት ፡ በተስፋ ፡ የመጡት ፡ የቅኔ ፡ እውሮችና ፡ ለወሬ ፡ የመጡት ፡ ዲያቆናት ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ወደዬመጡበት ፡ ተመልሰው ፡ በውነት ፡ ቅኔ ፡ ለመማር ፡ ፈቃዱም ፡ ችሎታውም ፡ ያላቸው ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ፡ የሩፋኤል ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ የቅኔ ፡ ቤት ፡ መልክ ፡ አገኘ ። ያም ፡ ሆኖ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ ሁሉ ፡ በሩፋኤል ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ ተማሪ ፡ ሩብ ፡ እንኩዋ ፡ ያለው ፡ አንድም ፡ አልነበረ ።

አለቃ ፡ ስርግው ፡ የሩፋኤሉ ፡ አለቃ ፡ በበኩላቸው ፡



ያዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ አለቆች ፡ በዛብህን ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ ቀን ፡ እህል ፡ ሲሻሙትና ፡ እያከፈሉ ፡ ከፍለው ፡ ለመውሰድ ፡ ሲፈልጉ ፡ ሲያዩ ፡ ሁሉንም ፡ አሸንፈው ፡ ከሳቸው ፡ ጋር ፡ ሊያስቀሩት ፡ የሚችሉበትን ፡ ዘዴ ፡ ይፈልጉ ፡ ጀመር ። በደመወዝ ፡ በኩል ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ ጭማሬ ፡ ቢያደርጉ ፡ የጊዮርጊስና ፡ የሌሎች ፡ ሀብታም ፡ አድባራት ፡ አለቆች ፡ ከሚሰጡት ፡ ጋር ፡ ለመወዳደር ፡ እንደማይችሉ ፡ ያውቃሉ ። ስለዚህ ፡ በደመወዝ ፡ ብልጫ ፡ ላይ ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ማግኘት ፡ አለባቸው ። ጸአዳ ፡ ስርግው ፡ ያለጥርጥር ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሊሰጡ ፡ ከሚችሉት ፡ ደመወዝ ፡ ትበልጣለች ! ጸአዳ ፡ ለአለቃ ፡ ስርግው ፡ ተቀዳሚ ፡ ተከታይ ፡ የሌላት ፡ አንዲት ፡ ልጃቸው ፡ ናት ። ባል ፡ ባገባች ፡ በሶስት ፡ ሳምንትዋ ፡ ተፋታ ፡ ተመልሳ ፡ አባትዋም ፡ እንደ ፡ ፈታችው ፡ ባልዋ ፡ ከምሽት ፡ ጋር ፡ ወር ፡ የሞላ ፡ አብረው ፡ መቆዬት ፡ ስለማይችሉ ፡ እንድዋ ፡ ምሽት ፡ ሄዳ ፡ ሌላዋ ፡ እስክትመጣ ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ አስማሪና ፡ ተቆጣጣሪ ፡ ቤታቸውን ፡ አስተዳዳሪ ፡ እስዋ ፡ ናት ። እንደ ፡ ምሽት ፡ መለወጫ ፡ የሌላት ፡ አለችኝ ፡ ብለው ፡ የሚኩራሩባት ፡ እስካሉ ፡ የምቾት ፡ ይሁን ፡ የችግር ፡ ተካፋያቸው ፡ ሲያልፉ ፡ ወራሻቸው ፡ ናት ። እስዋን ፡ ከዳሩለት ፡ የጸአዳ ፡ ባል ፡ ያሊቃ ፡ ስርግው ፡ የልጅ ፡ ባል ፡ ከሆነ ፡ በዛብህ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ የሚያስለውጥ ፡ ዋጋ ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ እንደማይስብ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ሩፋኤል ፡ የቅኔ ፡ መምህራን ፡ ሁሉ ፡ ካዲስ ፡ አበባም ፡ ሆነ ፡ ከየት ፡ እዬተሰበሰቡ ፡ የሚመረቁበት ፡ ስመጥር ፡ ይሆናል ! ሰው ፡ ሁሉ ፡ “ እድሜ ፡ ላሊቃ ፡ ስርግው ፡ ሩፋኤልን ፡ ከወደቀበት ፡ አንስተው ፡ የሊቃውንቱ ፡ የቅኔ ፡ መመስከሪያ ፡ አደረጉት ! ከሁሉ ፡ በታች ፡ የነበረውን ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ አደረጉት ! ” ይላል ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ይህ ፡ ድንቅ ፡ ስራቸው ፡ ለከፍተኛ ፡ ሹመት ፡ ባያሳጫቸው ፡ ሩፋኤልን ፡ እሻራለሁ ፡ ብለው ፡ እንዳይሰጉ ፡ የታመነ ፡ ዋስ ፡ ይሆናል ! ከዚያ ፡ ልጃቸውን ፡ ላንድ ፡ ስም ፡ የሌለው ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ሰጡ ፡ እንዳይባሉ ፡ የበዛብህን ፡ ሙያና ፡

የልጃቸው ፡ ባል ፡ መሆኑን ፡ ለጃንሆይ ፡ ነግረው ፡ በቅኔ ፡ መምህርነቱ ፡ ላይ ፡ ሹመትና ፡ ሽልማት ፡ ሲያስጡት ፡ የሳቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሱም ፡ የልጃቸውም ፡ ጥቅም ፡ ይጠበቃል ! ጎደቶ ፡ መጠቀም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጠቅሞ ፡ መጠቀም ፡ በሰውም ፡ ሆነ ፡ በእግዚአብሄር ፡ ዘንድ ፡ አያስወቅስም ! አዎ ! እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ክብር ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ የግዜር ፡ ስጦታ ፡ የሚያስለውጥ ፡ ከጊዮርጊስም ፡ ይሁን ፡ ከሌላ ፡ ደብር ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ፡፡ ይህ ፡ ነው ፡ ማሸነፊያቸው ፡ ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ፡፡

እውነትስ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የግዚአብሄር ፡ ስጦታ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ድንገት ፡ ሳይታሰብ ፡ እንዲሁ ፡ ከጥሩ ፡ ሰማይ ፡ ሲዘንብለት ፡ ደስ ፡ የማይለው ፡ ማነው ? ልቡ ፡ ከፍቱ ፡ ወጥቶ ፡ በደስታ ፡ ክንፍ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የማያርግ ፡ የማይሰርግ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነው ?---------- የምቾትን ፡ የደስታን ፡ የስልጣንንና ፡ እነሱን ፡ የመሰሉትን ፡ የሰው ፡ ፍላጎቶች ፡ ይዞ ተፈጥሮ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ እድል ፡ ሲያጋጥመው ፡ ደስ ፡ የማይለው ፡ ሰው ፡ አይገኝም !

በሃብህ ፡ ራሱ ፡ እንዲያ ፡ በቅኔ ፡ ገብያ ፡ ብቻውን ፡ ተገኝቶ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚመኬረትበት ፡ መሆኑን ፡ ሳይረዳ ፡ የፋፋ ኤልን ፡ ተራ ፡ የቅኔ ፡ መምህርነት ፡ በማግኘቱ ፡ እንኩዋ ፡ የነበረው ፡ ደስታ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ያስቸግራል ፡፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ የመጣው ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ከሱ ፡ በጣም ፡ የራቀ ፡ ስለነበረ ፡ እደርስበት ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ አስቦትም ፡ ተመኝቶትም ፡ የማያውቅ ፡ ነገር ፡ ነው ፡፡

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ በልሙ ፡ ወይም ፡ ሰብለን ፡ የሚያኖርበት ፡ በዶ ፡ ፍሲጋ ፡ ራሱን ፡ ሲበጠብጥ ፡- ያንድ ፡ ደብር ፡ አለቅነት ፡ ወይም ፡ ሊቀጠበብትነት ፡ ይሾምና ፡ ሀር ፡ ሲለብስ ፡ ባለድግድግ ፡ መረሻት ፡ በቅሎ ፡ ሲያስጭን ፡ እቤቱ ፡ ስጋ ፡ እንደ ፡ ጎመንና ፡ ዱባ ፡ ሲቆረጥ ፡ ጠጅና ፡ አረቂ ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ ሲፈስ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍራሽና ፡ ለሰላሳ ፡ ሀር ፡ ምንጣፍ ፡ ላይ ፡ ከሰብለ ፡ ጋር ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ ተቀምጦ ፡ ከግራቀኝ ፡ መከዳዎች ፡ መሀከል ፡ ሲንፈላሰስ ፡ ይቆይና ፡ ድንገት ፡ ከንቅልፉ ፡ ሲነቃ ፡



ወይም ፡ እእምሮውን ፡ ሲገዛ ፡- ያ ፡ ሁሉ ፡ ውሸት ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ጨዋታ ፡ መሆኑን ፡ ሲያይ ፡ ሲቀልድበት ፡ ቆይቶ ፡ በሄደው ፡ እልም ፡ ወይም ፡ ከንቱ ፡ አሳብ ፡ ብቻውን ፡ ይስቃል ፡፡ ይህ ፡ መቸም ፡ እልም ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አእምሮ ፡ ሲታወክ ፡ የሚመጣ ፡ ከንቱ ፡ አሳብ ፡ ነው ፡፡ አእምሮውን ፡ ገዝቶ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ስለኑሮው ፡ ሲያስብ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ማድረግ ፡ ይቅርና ፡ ምኞት ፡ እንኩዋ ፡ አልነበረውም ፡፡

ግ ስራ ፡ ሳልደግ ፡ ሰብለ ፡ ትደርስና ፡ ትቸገርብኛለች ፡ ብሎ ፡ ሲፈራና ፡ ሲሸበር ፡ ለሰው ፡ ፍቅር ፡ የታደለ ፡ በመሆኑ ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ ከመንገዳቸው ፡ ወጥተው ፡ ረድተውት ፡ የፋፋኤልን ፡ የቅኔ ፡ መምህርነት ፡ ሲያገኝ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለው ፡፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ የከበበው ፡ ቤት ፡ ካቅሙ ፡ በላይ ፡ ተከራይቶ ፡ በውስጥ ፡ ግርግዳውንና ፡ ወለሉን ፡ ባመድ ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ አስለቅልቆ ፡ ሰብለ ፡ እውጭ ፡ ተቀምጣ ፡ ሜዳውን ፡ የምትመለከትበት ፡ ባርጩማና ፡ ሌላም ፡ እወዳለሁ ፡ ስትል ፡ ከሰማው ፡ እቃ ፡ የሚችለውን ፡ ያክል ፡ ገዝቶ ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አሽከር ፡ ቀጥሮ ፡ ሰብለን ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ ይዞ ፡ ይደርሳል ፡ እያለ ፡ በናፍቆት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ፡፡ ቤተ ፡ ክርስተያን ፡ አገልግሎቱንና ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ ማስተማሩን ፡ ሲጨርስ ፡ ግረፍ ፡ ወይም ፡ መሜወት ፡ ሳያምረው ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴ ፡ ይሰፍርበታል ፡ በሚባለው መደብር ፡ ሁሉ ፡ እዩዞረ ፡ ከዲግ ፡ ወይም ፡ ከሞጣና ፡ ከቢቸና ፡ የመጣ ፡ ነጋዴ ፡ ሲፈልግ ፡ ራስዋን ፡ ተሸፍና ፡ በበቅሎ ፡ ተቀምጣ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ ወንዶች ፡ ያጀብዋት ፡ ወይዘሮ ፡ ባዩ ፡ ቀጥር ፡ እንደ ፡ ሰላይ ፡ ያላዩ ፡ መስሎ ፡ ለማየት ፡ ሲከተል ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ አራት ፡ ወር ፡ አለፈ ፡፡ እንኩዋን ፡ ሰብለን ፡ ወሬዋን ፡ የሚያመጣ ፡ ሰው ፡ ጠፋ ፡፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ እንኩዋን ፡ ደህና ፡ ከሆንሁ ፡ ገናን ፡ ተመልሼ ፡ እቤቴ ፡ ለመዋል ፡ እንድችል ፡ ቀደም ፡ ብዬ ፡ እመጣለሁ ፡ ያሉት ፡ ሳይመጡ ፡ ቀሩ ፡ የሚያደርገውን ፡ አጣ ፡፡ ግራ ፡ ገባው ፡፡ ማንን ፡ ይጥራ ? የማን ፡ ያለህ ፡ ይበል ?

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሽምብራ ፡ ብቻ ፡ ቆርጥሞ ፡ ውሀ ፡ እዩጠጣ ፡ ሶስትም ፡ ሰባትም ፡ ቀን ፡ እዩጾመ ፡ ሲጸልይ ፡ እንኳ ፡ እንደ ፡ ድሮው ፡ እልም ፡ አያይም ። የሚያየውም ፡ ያክል ፡ የሚያስፈራራ ቅዠት ፡ እንጂ ፡ የሚያጽናና ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጥ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ጊዜ ፡ እያለፈ ፡ ሲሄድ ፡ ሰብለን ፡ የማግኘቱ ፡ ተስፋ ፡ እዩተቀነሰ ፡ እያነሰ ፡ መሄድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ያ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ እያለ ፡ አብሮት ፡ የሚኖረው ፡ በሄደበት ፡ ሁሉ ፡ የሚከተለው ፡ ፍራት ፡ ባሳቡ ፡ ውስጥ ፡ እዩጎላ ፡ ይታዩው ፡ ጀመር ። ገና ፡ ሲፈጠር ፡ ፈጣሪው ፡ የመደበለትን ፡ ህይወት ፡ በመሸሹ ፡ ወላጆቹንም ፡ እግዚአብሄርንም ፡ የበደለ ፡ መሆኑ ፡ ቅጣት ፡ የሚገባው ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኑ ፡ በጉልህ ፡ ድምጽ ፡ ራሱ ፡ ውስጥ ፡ ሲጮህ ፡ ይሰማው ጀመር ። ለመስዋትነት ፡ እንጂ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ኖሮ ፡ ለማለፍ ፡ ያልተፈጠረ ፡ መሆኑን ፡ ይጠረጥር ፡ ጀመር ።

"ብቻ ፡ ለምን ? ከተወለድሁ ፡ ጀምሮ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ሊያስፈርድብኝ ፡ የሚችል ፡ በደል ፡ እግዚአብሄርን ፡ አልበደልሁም ! ሳልወለድም ፡ ልበድለው ፡ አልችልም ! ታዲያ ፡ ሳልበድል ፡ ለምን ፡ የግዞት ፡ ኑሮ ፡ እንድኖር ፡ ይፈረድብኛል ? " ይላል ፡ በዛብህ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ እግዚአብሄር ፡ ባልበደሉት ፡ ላይ ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ የሚፈርድበት ፡ ምክናያት ፡ አልገባው ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ለሚ ፡ ያለ ፡ ዳኛ ፡ እዩተሟገተ ።

ከዚህ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ከደረሰው ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በጠቅላላው ፡ ሰው ፡ የሚኖርበት ፡ የማህበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ስራት ፡ ይታዩዋል ። በጌታና ፡ በባሪያ ፡ በስጋዊም ፡ ሆነ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ገዢዎችና ፡ በተገዢው ፡ ህዝብ ፡ መሀከል ፡ ያለው ፡ በግፍ ፡ ባድልዎና ፡ በጭካኔ ፡ ላይ ፡ የተመሰረተ ፡ ስራት ፡ ይታዩዋል ። ከዚያ ፡ ደካማ ፡ ይደገፍበታል ፡ የተበደለ ፡ ይካስበታል ፡ የሰው ፡ መብትና ፡ ነጻነት ፡ ይከበርበታል ፡ ብሎ ፡ ይገምተው ፡ የነበረው ፡ የንጉሱ ፡ አደባባይ ፡ ደካማ ፡ በመደገፍ ፡ ፈንታ ፡ ወድቆ ፡ የሚረገጥበት ፡ የተበደለ ፡ ሰው ፡ እንኳዋንስ ፡ ሊካስ ፡ ተበደልሁ ፡ ብሎ ፡ ለማኩረፍ ፡ ነጻነት ፡ የማያገኝበት ፡ መሆኑን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እግ



ብሮ ፡ ላይ ፡ ያዩው ፡ ትዝ ፡ ይለዋል ። ከዚያ ፡ የመንፈሳዊ ፡ መሪዎችና ፡ አስተማሪዎች ፡ ነን ፡ በሚሉት ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ስጋውያን፡ ገዢዎች ፡ ከሚያደርጉት ፡ የማያንስ ፡ መገበያየት ፡ ጉቦ ፡ ግፍ ፡ በደል ፡ ተንኮል ፡ ሁሉ ፡ ይታዩዋል ።

" አዎ ፡ አለሙ ፡ እንደ ፡ ለማኝ ፡ እህል ፡ ድብልቅልቅ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ባለጌዎች ፡ ሸንጎ ፡ ትልቅ ፡ ድምጽ ፡ ያላቸው ፡ ብቻ እንዲሰሙበት ፡ ብርቱ ፡ ጡንቻ ፡ ያላቸው ፡ ብቻ ፡ እንዲያሸንፉበት ፡ ሆኖ ፡ የተሰራ ፡ ነው ! እኔም ፡ ተሰሚ ፡ ድምጽና ፡ ብርቱ ፡ ጡንቻ ፡ ከሌላቸው ፡ አንዱ ፡ ነኝ ! ብቻ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ እንዲሆን ፡ ያደረገው ፡ ማነው ? እግዚአብሄር ፡ ነው ? ወይስ፡ ጉዱ፡ ካሳ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደሚለው ፡ ልማድ ፡ ነው ? " ይላል፡ በዛብህ፡ የማያዩ ፡ አይኖቹን ፡ ፍጥጥ ፡ አድርጎ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተክሎ ። "ይህ ፡ ሁሉ ፡ አይንና ፡ ጆሮ ፡ በሌለው ፡ አድልዎ ፡ ላይ ፡ የተመሰረተ ፡ ስራት ፡ እውነት ፡ አዋቂው ፡ ትክክለኛው ፡ ቸሩ፡ ትልቁ፡ እግዚአብሄር ፡ የሰራው ፡ ነው ? እሱስ ፡ ባይሰራው ፡ የሰሩትንና ፡ ሲሰሩት ፡ የሚኖሩትን ፡ ለምን ፡ ዝም ፡ ይላቸዋል ? እንጃ ! የሱ ፡ ስራት ፡ አይደለም ፡ እንዳልል ፡ ጌታና ፡ ባርያ ፡ ገዢ ፡ ንጉስና ፡ ተገዢ ፡ ህዝብ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ ልጆቻቸውን ፡ እንደ ፡ ያእቆብ ፡ መስዋእት ፡ አድርገው ፡ ማቅረብ ፡ ሁሉ ፡ ከኦሪት ፡ ጀምሮ ፡ በመጽሀፍ ፡ ይገኛል ! እሱ ፡ የሰራው ፡ ስራት ፡ ነው ፡ እንዳልል ፡ ፍጥረቱን ፡ ያላንዳች ፡ ምክናያት ፡ በበዳይና ፡ በተበዳይ ፡ መሀከል ፡ እንዲከፋፈል ፡ ማድረግ ፡ ያልበደለ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንደ ፡ ተቀጣ ፡ የበደለ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ በደለ ፡ እንዲኖር ፡ ማድረግ ፡ እንኳዋንስ ፡ ያዋቆች ፡ ሁሉ ፡ አዋቂ ፡ የሆነው ፡ እግዚአብሄር ፡ የመንደር ፡ ዳኛም ፡ የሚፈርደው ፡ አይደለ ! ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ነው ? እንጃ ! "

በዛብህ ፡ እንዲህ ፡ ሊኖር ፡ ወይስ ፡ ላይኖር ፡ የተፈጠረ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ አቅቶት ፡ ይህ ፡ አለም ፡ ተጠይፈው ፡ ጥለውት ፡ ሊሄዱ ፡ ወይስ ፡ በውስጡ ፡ ተቀምጦ ፡ ግፍ ፡ ሊቀበሉበት ፡ ወይም፡ ከግፍ ፡ ሰሪዎች ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ግፍ ፡ ሊሰሩበት ፡ የሚገባ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ አቅቶት ፡ ሲጨነቅ ፡ " የጊዮርጊስ ፡ አለቃ ፡ ደመወዝህን ፡ እጥፍ ፡ አደርግልህለሁና ፡ መጥተህ ፡ እንነጋገር፡ አሉህ፡

የመድሀኔ ፡ አለም ፡ አለቃ ፡ ሶስት ፡ እጥፍ ፡ አደርግልሀለሁ፡ ብለው
ሀል ፤ የስላሴ ፡ አለቃ ፡ ከጃንሆይ ፡ ጋር ፡ አገናኝሀለሁ ፡ ብለው
ሀል ፡ አለቃ፡ስርግው ፡ አደራህ ፡ በሞቴ ፡ አፈር ፡ ስሆን ፡ ዛሬ ፡
ሰራት ፡ እንዳትቀር ፡ እጠብቅሀለሁ ፡ ብለውሀል ።" የሚል ፡ መላ
ክተኛ ፡ ከዬወገኑ ፥ ይላክበትና ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ የሚጠ
ይቁትን ፡ ለመቀበልም ፤ ላለመቀበልም ፡ በሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡
ስላልሆነ ፡ ከሁሉም ፡ መሸሽን ፡ ይፈልጋል ። ነገር ፡ ግን፡ ከሁሉም፡
ቢያመልጥ ፡ ካለቃ ፡ ስርግው ፡ ማምለጡ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡
ነበር ።

አለቃ ፡ ስርገው ፡ በዛብህን ፡ በልጃቸው ፡ ለመማረክ ፡ ሰለ
ወሰኑ ፡ ልማድ ፡ አድርገው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከራት ፡ በሁዋላ ፡ ከልጃ
ቸው ፡ ጋር ፡ ትተውት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክናያት ፡ እዬፈጠሩ ፡
ሲወጡ ፡ ብቻውን ፡ ከጸአዳ ፡ ጋር ፡ የሚቆይበት ፡ጊዜ ፡ ከተወለደ፡
ጀምሮ ፡ ከኖረው ፡ እድሜ ፡ ረዝሞ ፡ ይታዬዋል ።

ጸአዳ ፡ ቁንጅናዋን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያደንቀው ፡ ቀጠን ፡
ረዘም ፡ ያለች ፡ ፊትዋ ፡ ሰልከክ ፥ አይኖችዋ ፡ ጎላ ፡ ያሉ ፡ አፍን
ጫዋ ፡ ከላይ ፡ ቀጥ ፡ ክመሀከል ፡ ሰጉደድ ፡ ያለ ፡ ከንፈሮችዋ ፡
አነስ ፡ አነስ ፡ ብለው ፡ የሸፈኑዋቸውን ፡ ያልማዝ ፡ ድርድር ፡ የመ
ሰሉ ፡ ጥቃቅን ፡ ጥርሶችዋን ፡ ገለጥ ፡ ሲያደርጉ ፡ ደስ ፡ የምትልና ፡
ልቅም ፡ ያለ ፡ መልክ ፡ ያላት ፡ ጥሩ ፡ ልጅ ፡ ናት ። ለበዛብህ ፡ ግን ፡
ህይወትና ፡ ሙቀት ፡ የሌለው ፡ ቀዝቃዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ገና ፡ ቀለም ፡
ያልተቀባ ፡ የስእል ፡ ንድፍ ፡ እንጂ ፡ አጥንትና ፡ስጋ ፥ ደምና ፡
ቆዳ ፥ በዚያ ፡ ላይ ፡ ነፍስ ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ መስላ ፡ አትታዬውም ፡
ነበር ። ጸአዳ ፡ ሴቱን ፡ ሁሉ ፡ ካስጠሉት ፡ አንድዋ ፡ ናት ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አባትዋ ፡ እንደ ፡ ነገሩዋት ፡ እጠገቡ ፡ ተቀምጣ፡
እያጫወተች ፡ ጠጅ ፡ ቀድታ ፡ ስትሰጠው ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተነካ
ኩና ፡ ልክ ፡ በረዶ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ቅዝቃዜዋ ፡ የሰራ ፡ አካላቱን ፡
ያደነዘዘው ፡ መሰለው ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ መጥላት ፡ ብቻ ፡ ሳይ
ሆን ፡ እንደ ፡ ጣረሞት ፡ ይፈራት ፡ ጀመረ ። እሰዋም ፡ ብትሆን ፡
አብራው ፡ በተቀመጠች ፡ ቁጥር ፡ ሲጨነቅና ፡ መድረሻ ፡ ሲያጣ፡
እያዬች ፡ እንደሚጠላት ፡ ተረድታ ፡ ያባትዋን ፡ ፈቃድና ፡ ትእ
ዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ሆኖባት ፡ አብራው ፡ ተቀምጣ ፡ መ



ጠጥ ፡ ስትጋብዘው ፡ ትቆያለች ፡ እንጂ ፡ የራስዋ ፡ ፈቃድ ፡
ቢኖራት ፡ ጠልቶዋት ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ሲቸገር ፡ ማየት ፡ ልክ ፡
የሞት ፡ ያክል ፡ የምትጠላው ፡ ነገር ፡ ነው ።

ከጸአዳ ፡ ቀጥላ ፡ በዛብህን ፡ ለማጥመድ ፡ የሞከረች ፡ ተዋ
በች ፡ ናት ። ተዋበች ፡ ቤትዋ ፡ በዛብህ ፡ በሚወጣ ፡ በሚገባበት ፡
መንገድ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይተያያሉ ። ከመተያየትና ፡
ሰላምታ ፡ ከመለዋወጥ ፡ ያለፈ ፡ እውቂያ ፡ ግን ፡ አልነበራቸውም።
በቁጥር ፡ መልክም ፡ ሆነ ፡ በደም ፡ ግባት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ የሚያደ
ንቃትና ፡ ብዙ ፡ መኩዋንንት ፡ የሚጣሉባት ፡ በመሆንዋ ፡ በዛ
ብህ ፡ እንዲሁ ፡ ሰላምታ ፡ ብቻ ፡ እዬሰጣት ፡ ማለፉና ፡ በውበ
ትዋ ፡ አለመማረኩ ፡ አስቆጭቶዋት ፡ ኩርፊያውንም ፡ ግልምጫ
ውንም ፡ ሌላውንም ፡ ሴቶች ፡ የወንዶችን ፡ አሳብ ፡ ወደነሱ ፡ የሚ
ስቡበትን ፡ ዘዴ ፡ ሁሉ ፡ ሞክራ ፡ ሲያቅታት ፡ ጊዜ ፡ የሴቶችን ፡
ትታ ፡ የወንዶችን ፡ መንገድ ፡ ለመከተል ፡ ወሰነች ። አንድ ፡ ቀን፡
በዛብህ ፡ አራዳ ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴ ፡ ፍለጋ ፡ ሄዶ ፡ ቆይቶ ፡ ሲመ
ለስ ፡ ተዋበች ፡ እቤትዋ ፡ ጥግ ፡ ተቀምጣ ፡ ጠብቃ ፡ " እንዴት ፡
አመሸህ ፡ አለቃ ፡" አለችው ። "እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡
ማነው ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ መሽቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ተዋበች ፡ መሆን
ዋን ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ስላልቻለ ።

"እኔ ፡ ነኝ ፡" አለች ፡ ተዋበች ፡ ከተቀመጠችበት ፡ ተነስታ ፡
ወደሱ ፡ እዬሄደች ። "ወንድሜ ፡ ካገር ፡ ቤት ፡ ወረቀት ፡ ልኮልኝ ፡
የሚያነብልኝ ፡ አጣሁ ፡ እባክህ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እቤት ፡ ግባና ፡
አንብብልኝ ።"

"የማስተማር ፡ ጊዜ ፡ ደርሶብኛል ፡ እንጂ ፡ ደስ ፡ ባለኝ ፡
ነበር።"

"መጻፍኮ ፡ አይደለም ፤ ማንበብ ፡ ነው ። ማንበብ ፡ ጊዜ ፡
ይወስዳል?"

እቤት ፡ ሲገቡ ፡ ተዋበች ፡ ከጉዋዳ ፡ በወረቀት ፡ ፈንታ ፡
ሁለት ፡ ብርሌ ፡ ጠጅ ፡ አምጥታ ፡ አንዱን ፡ ለሱ ፡ ሰጠችና ፡
አንዱን ፡ እሰዋ ፡ ይዛ ፡ አጠገቡ ፡ ተቀመጠች ።

"ወረቀቱ ፡ የታል?" ላንብብልሽና ፡ ልሂድ ፡ እባክሽ ።"

"ፈጥኖ ፡ ከመሄድ ፡ ያድንህ ፡ ይላል ፡ መራቂ ! ፈጥኖ ፡
መሄድ ፡ ደግ ፡ አይደለም !"

"እቤቴ : ነው : ወደሌላ : ልሂድ : አላልሁም! "

"ምሽት : የሌለው : ወንድ : ሴት : ያለችበት : ሁሉ:ቤቱ : ነው!" አለችና : እንገቱን : በሁለት : እጅዋ : ጥምጥም : አድርጋ : ይዛ : ለመከላከል : ብርሌውን : እስኪያስቀምጥ : ድረስ : እፋን.: ባፍዋ : ጎርሳ : ሳመችው :: በዛብህ : ብርሌውን : አስቀምጦ : ልክ : ከጣረሞት : ለማምለጥ : እንደሚጣጣር : ሀይሉን : ሁሉ : አጠራቀመና : ከላዩ : ገፍትሮ : ጥሎዋት : ተነሳ : ፍራት: ከቁጣ : ጋር : ተጨምሮ : እያንቀጠቀጠው :: ተዋበች : በበኩልዋ: ከወደቀችበት : ለመነሳት : ስትጣጣር : ዘቅዝቆ : ቢመለከታት: ጠጉርዋ : ጭብርርር : ፊትዋ : ክርር : አይንዋም : አፍዋም : በሰፊው : ክፍት : ብሎ : እውነትም : ጣረሞት : መስላ : ታዩችው:: ከዚያ : እፉን : እዬጠረገ : ወጥቶ : ወደ : ቤቱ : ሮጠ ::

ከዚያ : በሁዋላ : በተዋበች : ቤት : በኩል : ማለፉን : እንኩዋ : እዬፈራ : ወደ : ቤተ : ክርስቲያንም : ይሁን : ወደ : ሌላ: የሚሄድበትን : መንገድ : ለወጠ :: ስለዚህ : በጸአዳና : በተዋበች : ምክናያት : ሴቱን : ሁሉ : መጥላት : ብቻ : ሳይሆን : ይፈራ: ጀመር :: በጸአዳና : በተዋበች : ምክናያት : ከሰብለ : በቀር : ሌላው : ሴት : ሁሉ : እንደ : ተዋበች : የሚባላ : እንደ : ጸአዳ : ቅዝቃዜው : የሚያደነዝዝ : መስሎ : ታዩው :: በተዋበችና : በጸአዳ : ምክናያት : እግዚያብሄር : በሰፊ : መሬቱ : ከሰብለ : በቀር : ሌላ : ሴት : ያልፈጠረ : መስሎ : ታዩው :: ሰብለን : ካላገኘ:ሌላ: ምሽት : አግብቶ : ንብረት : አበጅቶ : መኖር :የማይችል:መስሎ: ታዩው :: አገሩን : ለቆ : የተሰደደበት : ወላጆቹ : እንደ : መካኖች : ያላስታማሚ : በባዶ : ቤት : ታመው : እንዲሞቱ : ያደረገበት : ዋና : አላማው : ከንቱ : ሆኖ : መቅረቱ : ታዩው ::

በዛብህ : ገና : ድሮ : አገሩ : ማንኩሳ : ዲያቆን : ሆኖ : ሲቀድስ : ጀምሮ : ከሁሉ : አብልጦ : የሚመኛቸው : ሁለት : ነገሮች : ነበሩ :: የመጀመሪያው : እንደ : ሰው : ሁሉ : ምሽት : አግብቶ : ንብረት : አበጅቶ : መኖር : ሁለተኛው : በተሰይ : የቅኔ : ሊቅ : መሆን : ናቸው :: ሀብታም : መሆን : ሰብለን : ከወደደ : በሁዋላ : የጨመረው : ሶስተኛ : ምኞት : ነው :: የሰብለ : ወሬ : እዬራቀው : ሲሄድ : እንኩዋ : የሀብት : የመኖር : ምኞቱም :



እዬተቀነሰ : ሄደ ።

ብዙ : ጊዜ : ስራውን : ጨርሶ : ቁጭ : ሲል : ወይም : ሌሊት : አልጋ : ላይ : ተጋድሞ : ቃልኪዳን : ከተገባላቸው : ታቦቶችና : ከወላጆቹ : በመሸፈቱ : እግዚአብሄር : የተጣላው : በደለኛ : መሆኑ : ትዝ : ይለውና : ፍራት : ሲይዘው : በጾምና : በጸሎት : ከእግዚአብሄር : ለመታረቅ : ሁሉንም : ጥሎ : መመነን : ያስባል ።

"ሽፍታ : ቀማኛ : ሌባ : ወይም : አመንዝራ : ልሆን : አልሸሸሁ ! በህግ : አግብቼ : ቤት : ንብረት : ይዤ : ቤተ : ክርስቲያን : እያገለገልሁ : ለመኖር : ብሸሽ : ምን : ጥፋት : አደረግሁ : ብሎ : እግዚአብሄር : ይቆጣኛል? የለም! በዚህ : የሚቆጣ : አይመስለኝም! ብቻ : እኔ : መበደል : አለመበደሌን : እሱ : መቆጣት : አለመቆጣቱን : እንዴት : ማወቅ : ይቻላል?" ይላል : እንደገና : መልሶ ።

አንድ : ሌሊት : ይህኑ : ሲያሰላስል : ድምጽ : የሰማ መሰለውና : በጣም : ደንግጦ : አይኑንም : አፉንም : በጨለማ : ውስጥ : በሰፊው : ከፍቶ : እሳቡን : ጥቅልል : አድርጎ : ያዳምጥ : ጀመር ። የሰማው : ድምጽ : አእምሮው : በአሳብ:ተውጦ : ሳለ : ሳይታወቀው : ከራሱ : ይውጣ : ወይም : ከሌላ : በጭራሽ: ሊረዳው : አልቻለም ።

"ይህ : እኮ : ቀላል : ነገር : ነው : ይህን : ያክል : ሊያስቸግርም ። ሰብለ : እስከ : ፋሲካ : ካልመጣች : እግዚአብሄር : ያልፈቀደ : መሆኑን : ተረድቶ : ንቱን : እግዚአብሄር : የመደበውን : መንገድ : መከተል : ነው ።" የሚል : ነበር : ድምጹ ።

"ጥሩ : መልስ : ነው !" አለ : በዛብህ : ዝም : ብሎ : ሲያዳምጥ : ቆይቶ ። "እንግዴህ : አምላኬ : እስከ : ፋሲካ : ከሰብለ : ጋር : ያገናኘሽኝ : እንደ : ሆነ : ለሌላው : ፍጥረትህ : ሁሉ : የፈቀድኸውን : ህይወት : ለኔ : ያልነፈግኸኝ : መሆንህንና : እስከዛሬም : የነበረኝ : ፍራት : ከንቱ : መሆኑን : እረዳለሁ!ካልመጣች: ግን : ያው - - - - የምጠረጥረውና : የምፈራው : እውነት : መሆኑ: ነው!"

በልማዱ ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴ ፡ የገናንም ፡ ይሁን ፡ የፋሲካን ፡ አመትባል ፡ ተመልሶ ፡ በዬቤቱ ፡ ለመዋል ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ካመትባሉ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የንግድ ፡ እቃውን ፡ እዬጫነ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መድረስ ፡ አለበት ፡፡ በዛብህ ፡ ይህን ፡ ስላጠና ፡ የገና ፡ አመትባል ፡ እስኪያልፍ ፡ ያደርገው ፡ እንደነበረ ፡ ሁሉ ፡ ከፋሲካ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ያክል ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴ ፡ የሚሰፍርበትን ፡ መደብር ፡ ሁሉ ፡ በቀን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳይረግጠው ፡ ውሎ ፡ አያድርም ፡፡

አንድ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ በዬመደብሩ ፡ ሲዞር ፡ አምሽቶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲመለስ ፡ ሁለት ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴዎች ፡ እዬተጫወቱ ፡ ወደ ፡ ጉለሌ ፡ ሲሄዱ ፡ ደረሰባቸው ፡፡

" አሁንኮ ፡ አሲ ፡ ጀብሪ ፡ ቆዳችነን ፡ መዝንልንና ፡ ዋጋ ፡ እንነጋገር ፡ ብንለው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሚዛኑ ፡ ተሰብሮዋል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መዛኙ ፡ ታሙዋል ፡ እያለ ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ የሚለን ፡ ፋሲካ ፡ እስኪደርስለት ፡ ነው ! " አለ ፡ አንዱ ፡ ነጋዴ ፡፡

"ፋሲካ ፡ ሚዛን ፡ ይሆናል ? ወይስ ፡ መዛኝ ! " አለ ፡ ሁለተኛው ፡፡

"የለም ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ እያልሁ ፡ ፋሲካ ፡ እስኪለግት ፡ ካቆዬሁዋቸው ፡ ለማጫረት ፡ ጊዜ ፡ ያጥራቸውና ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ ጥለውልኝ ፡ ይሄዳሉ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ! "

"እረግ ፡ የዲማው ፡ አባቴ ! ዋጋ ፡ ሰብረን ፡ ከምንሸጥ ፡ በምናውቀው ፡ አገር ፡ አስቀምጠነው ፡ አንሄድም ?"

" ላዲስ ፡ አበባ ፡ እንግዶች ፡ መስለነው ፡ ይሆናል፡፡"

ነጋዴው ፡ የዲማን ፡ ስም ፡ ሲጠራ ፡ በዛብህ ፡ ልቡ ፡ ተር ተር ፡ ብሎ ፡ በህዋሳቱ ፡ ሁሉ ፡ ወራሪ ፡ ተነዝቶ ፡ የሚበዘብዘው ፡ መሰሎ ፡ ተሰማው ፡፡ ጉልበቱ ፡ እንደ ፡ መብረክረክ ፡ አይኖቹ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መድበዝበዝ ፡ አሉና ፡ ወዲያው ፡ የተናወጸ ፡ አካላቱ ፡ ጸጥ ፡ አሳቡም ፡ ጠቅሰል ፡ አለ ፡፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ነጋዴ ዎች ፡ የተነጋገሩትን ፡ አልሰማም፡፡

"ጌቶች ፡ ከየት ፡ ጎጃም ፡ ነው ፡ የመጣችሁ? እኔ ፡ ጎጃሜ ፡ ስለ ሆንሁ ፡ ያገሬ ፡ ሰዎች ፡ መሆናችሁን ፡ ስለተረዳሁ ፡ ነው ፡



ደፍሬ ፡ የምጠይቃችሁ ፡፡" አለ ፡ አስተካክሎ ፡ ለመናገር ፡ እስኪችል ፡ ትንሽ ፡ ቆይቶ ፡፡

" ከነማይ ፡፡ " አለ ፡ አንዱ ፡ ነጋዴ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ በዛብህን ፡ አዬና ፡፡

" የት ፡ እነማይ ? "

" ዲማ ፡፡ "

" ዲማ ፡ ደብሩ ? "

" ዲማ ፡ እምብርቱ ፡፡ "

" ዲማ ፡ ማንን ፡ ታውቃላችሁ ? ፊታውራሪ ----- መሸሻን ፡ ታውቃላችሁ ?"

"እሮ ! ምን ፡ ማለታቸው ፡ ነው ፡ አያ ! ዲማ ፡ እዬኖርን ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ይጥፉን ? "

"አለቃ ፡ ካሳ ፡ ዳምጤንስ ?"

"እዋ! ጉዱ ፡ ካሳን ?"

" ታዲያ ፡ ሁሉም ፡ ደህና ፡ ናቸው ? "

" ደህና ፡ ናቸው ፡፡ "

" አለቃ ፡ ካሳ ፡ እመጣለሁ ፡ ብለው ፡ ጽፈውልኝ ፡ ስጠብቃቸው ፡ ስለቀሩ ፡ ደህና ፡ ባይሆኑ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ሰግቼ ፡ ነበር ፡፡"

" ሁሉም ፡ ደህና ፡ ናቸው ፡ ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ልጃቸውን ፡ ለፋሲካ ፡ ሊድሩ ፡ ይሰናዳሉ ፡፡ ሰርጌም ፡ ተስካሬም ፡ የልጇ ፡ ሰርግ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አስታውቀው ፡ እነማይ ፡ በሙሉ ፡ ይደግሳል ፡፡ እኛ ፡ እንኩዋ ፡ ከዚህ ፡ ለሙሽራዋም ፡ ለሙሽራውም ፡ የሚሰጡት ፡ ሽልማት ፡ ገዝተን ፡ እንድንወስድላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥተውን ፡ ነበር ፡ አይነቱን ፡ የሚመርጥልን ፡ አጥተን ፡ ገና ፡ አልገዛንም ፡፡ ጌታው ፡ እንግዴህ ፡ እስዎ ፡ ዘመድ ፡ ከሆኑ ፡ ለትልቅ ፡ ሰው ፡ ሽልማት ፡ የሚሆን ፡ ልብስ ፡ መምረጥ ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ቢያጋጥሙን !" አለና ፡ ነጋዴው ፡ መልስ ፡ ሲያጣ ፡ ጊዜ ፡ ዘወር ፡ ቢል ፡ በዛብህ ፡ በሁዋላቸው ፡ የለም ፡፡ በዛብህ ፡ ነጋዴው ፡ "ፊታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ልጃቸውን ፡ ለፋሲካ ፡ ሊድሩ ፡" ሲል ፡ መብረቅ ፡ እንደመታው ፡ በቆመበት ፡ ደርቆ ፡ ቀረ ፡፡ ወዲያው ፡ ሳይታወቀው ፡ እዚያው ፡ ተቀመጠ ፡፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ነጋዴው ፡ የተናገረው ፡ ሁሉ ፡ ከጉዋደኛው ፡

በቀር ፡ ሌላ ፡ ሰሚ ፡ አልነበረውም ። ሁለቱ ፡ ነጋዴዎች ፡ በዛ ብህን ፡ በሩቅ ፡ ተቀምጦ ፡ ሲያዩት ፡ ታምሞል ፡ ብለው ፡ ወደሱ ፡ እዩሮጡ ፡ ሄዱ ። ለጊዜው ፡ መነሳት ፡ ያቅተው ፡ እንጂ ፡ አእም ሮውን ፡ ገዝቶ ፡ አገኙት ።

“ ምነው ? አመመዎ ? ” አለ ፡ ከነጋዴዎቹ ፡ አንዱ ፡

“ ትንሽ ፡ ራሴን ፡ አዞሮኝ ፡ ነው ፡ ግዴለም ፡ ሂዱ ፡ አሁን ፡ ይተወኛል ። ”

“ መጠጥ ፡ ጠጥተው ፡ ኖሮዋል ! ”

“ የለም ፡ መንሽ ፡ አለብኝ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ማለፉ ፡ ነውና ፡ አትቸገሩ ፡ ሂዱ ። ”

“ እንደ ፡ ያመኛ ፡ አመንገድ ፡ ላይ ፡ ጥለንዎ ፡ እንሄዳለን ? ስፈራችን ፡ እዚህ ፡ ነው ፡ ቡና ፡ ጠጥተው ፡ ሲሻለዎ ፡ እቤትዎ ፡ እናደርስዎ ፡ እንጂ ! ”

በዛብህ ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ነጋዴዎች ፡ ወደ ፡ ተከራዩት ፡ ቤት ፡ አብሮዋቸው ፡ ሄዶ ፡ ቡና ፡ ሲጠጡ ፡-

“ ወደ ፡ ዲማ ፡ መቼ ፡ ለመነሳት ፡ ታስባላችሁ ? ” አለ ።

“ ከዛሬ ፡ ሳምንት ፡ እናልፍም ። ”

“ እስከትሄዱ ፡ ድረስ ፡ እዬመጣሁ ፡ እጠይቃችሁዋለሁ ።”

ከዚያነለት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እንቅ ልፍ ፡ ይሁን ፡ እረፍት ፡ የለው ፡ የመብል ፡ ይሁን ፡ የመጠጥ ፡ ፍላ ጎት ፡ የለው ፡ ገና ፡ መብል ፡ ሲያስብ ፡ አፉን ፡ እዬመረረው ፡ ራሱ ፡ እስበሳቸው ፡ የሚጣሉ ፡ አሳቦች ፡ የሚዋጉበት ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ ሆኖ ፡ ደከመው ።

“እዚያው ፡ ዲማ ፡ ብቆይ ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አይደርስም ፡ ነበር ! ምን ፡ ለማድረግ ፡ እችል ፡ ኖሮዋል ? ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ወዳጄ ፡ መስሎ ፡ አታሎ ፡ ሰዶ ፡ ጉድ ፡ አደረገኝ ! አይ ፡ የለም ፡ ባይሆንለት፡ ነው ! ሰብለ ፡ ካደችኝ ፡ የለም ፡ ተገዳ ፡ ነው ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ፈቅዳ ፡ አይደለም ! በግድ ፡ ነው ! በቃችኝ ፡ ጠላሁዋት ፡ እንግዴህ፡ አባትዋ ፡ በግድ ፡ አንቀው ፡ ሲሸጥዋት ፡ ምን ፡ አደረገሽ ፡ ብዬ ፡ ልጥላት?”

በዛብህ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ያሳብ ፡ ውሽንፍር ፡ ሲያጠናፍ ረው ፡ ሰንብቶ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የታወከ ፡ የአሳብ ፡ ማእበል ፡



ሶስት ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ሲያንገላታው ፡ ሰንብቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ያለ ጥፋት ፡ ከተፈረደበት ፡ ቅጣት ፡ ለማምለጥ ፡ ከሙታን ፡ ኑሮ ፡ የህያዋን ፡ ኑሮ ፡ ለመኖር ፡ በጀመረው ፡ ትግል ፡ ድል ፡ መሆኑን ፡ አምኖ ፡ መሸነፉን ፡ ተቀብሎ ፡ ጸጥ ፡ ማለት ፡ ማረፍ ፡ ጀመረ ። ተንጠልጥሎ ፡ እወድቅ ፡ አልወድቅ ፡ ከማለት ፡ መውደቅ ፡ በስ ንት ፡ ጣሙ! መውደቅ ፡ ያሳርፋል! ስለዚህ ፡ በዛብህ ፡ ወደቀና ፡ አረፈ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ዲማ ፡ ነጋዴዎች ፡ ቤት ፡ ቢሄድ ፡ ወዳገራቸው ፡ ለመነሳት ፡ ጭነታቸውን ፡ ሲቀራቀቡ ፡ ደረሰባ ቸው ።

“እኛስ ፡ ሲቀሩ ፡ ጊዜ ፡ ሳናገኝዎ ፡ልንሄድ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ፈርተን ፡ ነበር ።” አለ ፡ ከነጋዴዎቹ ፡ አንዱ ፡ በዛብህን፡ ሲያይ ፡

“ጤና ፡ እጥቼ ፡ ሰነበትሁ ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ ላሊቃ ፡ ካሳ ፡ዳምጤ ፡ታደርሱልኛላችሁ?” አለ ፡ በዛብህ ፡ አንድ ፡ እንቬሎፕ፡ ከኪሱ ፡ አውጥቶ ።

“የገባሁ ፡ እለት ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ እቤቴም ፡ አላሳድረው፡” አለ ፡ ነጋዴው ፡ እዬሳቀ ።

“ይድረሳቸው ፡ እንጂ ፡ ቢያሳድሩትም ፡ ግዴለ ።”

ነጋዴው ፡ እንዳለው ፡ ዲማ ፡ የገባለት ፡ ደብዳቤውን፡ ለጉዱ፡ ካሳ ፡ አስረከበ ። የተጻፈው ፡ ለሰብለ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በዘነጋው ፡ ደረ ሳትና ፡ በዛብህና ፡ እሰዋ ፡ ላጭር ፡ ጊዜ ፡ የፍቅር ፡ አለማቸውን ፡ ባዩባት ፡ እልፍኝዋ ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጣ ፡ አነበበችው ።የስንብት ፡ ደብዳቤ ፡ ነው!

“ሰብለ ፡ ሰብለ ፡ ሰብለ ፡ ወዳጄ ፡ እመቤቴ ፡-
የመአልት ፡ ምርኩዜ ፡ የሌሊት ፡ መብራቴ ፡-
ስራብ ፡ እንጀራዬ ፡ ስጠማ ፡ ወተቴ ፡-
ሳዝን ፡ መጽናኛየ ፡ ስደክም ፡ ጉልበቴ ፡-
ሳጣ ፡ አለኝታየ ፡ ስጠቃ ፡ ኩራቴ ፡-
የስጋ ፡ የመንፈስ ፡ ያለሽኝ ፡ አንድ ፡ ሀብቴ ፡-
ቁርጥ ፡ ከሆነማ ፡ እኔ ፡ እንቺን ፡ ማጣቴ ፡-
ምን ፡ ዋጋ ፡ ሊኖረው ፡ ከንግዴህ ፡ ህይወቴ?
የለም! ህይወት ፡ በቃኝ! ይገላግለኝ ፡ ሞቴ ፡-
ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ ፡-

ጥፉሽ ፡ የሄድሁለት ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሬ ፡-
የደም ፡ እንባ ፡ አልቅሼ ፡ በድሌ ፡ አግርሬ ፡-
የሁዋሊት ፡ ስንተት ፡ በፍቅርሽ ፡ ታስሬ ፡-
ወደፊት ፡ መራመድ ፡ እያቃተው ፡ እግሬ ፡-
አሁንም ፡ አሁንም ፡ ቆሜ ፡ እያዩሁ ፡ ዞሬ ፡-
ምን ፡ ልቤ ፡ ቢፈራ ፡ ባይቀር ፡ መጠርጠሬ ፡-
በተስፋ ፡ ነበረ ፡ የወጣሁ ፡ ከገሬ ፡-
እስከዛሬም ፡ ድረስ ፡ በሀይወት ፡ መኖሬ ፡-
ተስፋ ፡ ሆኖኝ ፡ ነበር ፡ ፍቅርሽና ፡ ፍቅሬ ፡-
ግን ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ የነገሩኝ ፡ ወሬ ፡-
ሊያገባሽ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ባለብዙ ፡ በቅሎ ፡ ባለብዙ፡ በሬ፡-
በፍቅር ፡ ለሞተ ፡ መታሰቢያ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ መቃብሬ ፡-
መኖር ፡ አልፈልግም ፡ ሞቼ ፡ ልደር ፡ ዛሬ ፡-
ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ ፡
ለብለ ፡ ልጠይቅሽ ፡ እስቲ ፡ ተናገሪ ፡
ከሁሉ ፡ እኔን ፡ ብቻ ፡ እንደምታፈቅሪ ፡-
ከኔ ፡ ተለይተሽ ፡ እንዳትችይ ፡ ልትኖሪ ፡-
ላባትሽ ፡ ነግረሻል ፡ በድፍረት ፡ ሳትፈሪ ፡-
እንቢኝ ፡ አሻፈረኝ ፡ ያለሱ ፡ አላገባም ፡ ብለሻል ፡ ሳታፍሪ ?
ወይስ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ታፍና ፡ ተዳሪ ፡-
ዝም ፡ ብለሽ ፡ ተቀበልሽ ፡ ሳትከራከሪ?
ወይስ ፡ ተለይተን ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ስትኖሪ ፡-
መቼም ፡ ሰው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ሲፈጥረው ፡ ፈጣሪ ፡-
ተለውጠ ፡ ይሆን ፡ ከቶ ፡ ያንችም ፡ ባህሪ ፡-
የለም ፡ ግሪኝ! ግሪኝ! ርሺ ፡ አትዘከሪ ፡-
ዱብዳ ፡ ወድቆብኝ ፡ ለሸከሙ ፡ አስቸጋሪ ፡-
ጨንቆኝ ፡ ስለፈልፍ ፡ እንደ ፡ ቀባጥሪ ፡-
ባንቺ ፡ እምነት ፡ የሌለኝ ፡ ብመስል ፡ ጠርጣሪ ፡-
መሆንሽን ፡ አውቃለሁ ፡ ፍቅርሽን ፡ አክባሪ ፡-
በሀብት ፡ ለመደለል ፡ የማትሞከሪ ፡-
ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ ፡
አውቃለሁ ፡ አባትሽን ፡ እንዳማጠንሻቸው ፡-



ነፍስና ፡ ስጋ ፡ ነን ፡ እባክዎ ፡ አይለዩን ፡ አባባ! እንዳልሻቸው፡
ከዚህ ፡ አይሻለሁ ፡ ወድቀሽ ፡ ከፊታቸው ፡-
እዩተስቀዩሽ ፡ ስትለምኛቸው ፡-
እንባሽ ፡ ይታዩኛል ፡ ሲፈስ ፡ በግራቸው ፡-
እዩ ! ያባት ፡ ክፉ ፡ ምቀኝ ፡ የሞላቸው ፡-
እስቲ ፡ እኛ ፡ ደስ ፡ ቢለን ፡ ምን ፡ ጎድሎባቸው ፡-
የሳቸውን ፡ ሀይወት ፡ ኖረው ፡ በፈንታቸው ፡-
የኛን ፡ ሀይወት ፡ እንዲህ ፡ ከንቱ ፡ ማድረጋቸው ?
እኔስ ፡ ባእዳቸው ፡ ነኝ ፡ ይቅር ፡ ልበላቸው !
ደስታ ፡ በብዙ ፡ ሀብት ፡ ይገዛ ፡ መስሎዋቸው ፡-
እንዴት ፡ ይነግዱ ፡ በገዛ ፡ ልጃቸው ?
ዳኛ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ የሚጠይቃቸው ፡-
ከቶ ፡ የሚሰጡት ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ መልሳቸው ?
ዳኑ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !..
ዳኛ ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ ቢኖርማ ፡ ዳኛ ፡-
ሀሊናው ፡ ባድልዎ ፡ በጉቦ ፡ ያልተኛ ፡-
እንዳንቺ ፡ እባት ፡ ያለ ፡ ጨካኝ ፡ አመጸኛ ፡
በልጁ ፡ የሚነግድ ፡ ሲገኝ ፡ ግፈኛ ፡-
እጁን ፡ ወደሁዋሊት ፡ ታስሮ ፡ በመጫኛ ፡-
ይሰቀል ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ወንጀለኛ ፡
ዳኑ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
እግዚእ ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ ለማን ፡ ልጩህ ፡ እኔ ?
ነፍሴን ፡ ወስደውብኝ ሲቀር ፡ ብቻ ፡ በድኔ ፡
አልቅሶ ፡ እንዳይቀብረኝ ፡ እንዳያዝን ፡ ወገኔ ፡-
ቆሞ ፡ ሲንቀሳቀስ ፡ ይታያል ፡ ግብኔ ፡-
በማን ፡ ደርሶ ፡ ያውቃል ፡ እንዲህ ያል ፡ ብየኔ ?
ሳያጠፉ ፡ ቅጣት ፡ ሳይሞቱ ፡ ኩነኔ ?
ዳኑ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
ጉልበቴን ፡ ሳላጥፍ ፡ ወገቤን ሳልፈታ ፡-
ቀን እረፍት ፡ ሳያምረኝ ፡ ወይ ፡ ሌሊት ፡ ምኝታ ፡-
እርም ፡ ብዬ ፡ ትቸ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ጭዋታ ፡-
ስጸልይ ፡ ስማለል ፡ ከጥዋት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡-

ያሳዩኛል ፡ ብዬ ፡ አይንሽን ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡-
አጥፊዎችን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ባዩ ፡ ጌታ ፡-
መቸም ፡ ያልጻፈኝ ፡ ነኝ ፡ ስፈጠር ፡ ለደስታ ፡-
አመጣልኝ ፡ መርዶ ፡ በምስራች ፡ ፈንታ ፡-
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
እግዚአብሄር ፡ ሲፈጥረኝ ፡ ጥንቱን ፡ በዚህ ፡ መሬት ፡-
ሳለቅስ ፡ ተወልጄ ፡ ሳለቅስ ፡ ኖሬበት ፡-
ሳለቅስ ፡ እንድሄድ ፡ ነው ፡ ወይ ማልቀርበት ?
መከራ ፡ ጠግቤ ፡ ደስታ ፡ እንድራብበት ?
ሌሎች ፡ የበሉትን ፡ እዳ ፡ እንድከፍልበት ?
ሌላው ፡ ጠግቦ ፡ ሲያድር ፡ እኔ ፡ እንዳልቀምስበት !
እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ፍርድ ፡ አድሎ ፡ የሞላበት ፡-
አቅም ፡ ስለሌለኝ ፡ የምቃወምበት ፡-
ዝም ፡ ብዬ ፡ እቀመጣለሁ ፡ መቸስ ፡ ምናለበት ፡-
ብቻ ፡ ሳላጠፋ ፡ በተቀጣሁበት ፡-
የሰጠኝ ፡ አእምሮ ፡ ልመራመርበት ፡-
ቅንና ፡ ጠማማ ፡ ለይቼ ፡ እንዳውቅበት ፡
ምንም ፡ እንኳዋ ፡ ባይችል ፡ ቅጣት ፡ ሊጥልበት ፡
ይኖራል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ፈረደበት ፡-
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
እኔንስ ፡ ግዴለም ፡ ይቅጣኝ ፡ ይደብድበኝ ፡-
መቸም ፡ ለመከራ ፡ ለጣር ፡ የመደበኝ ፡-
ሳዝን ፡ ኖሬ ፡ እንድሞት ፡ የተፈጠርሁ ፡ ነኝ ፡-
እንጂቴን ፡ የበላው ፡ አሁን ፡ ያሳዘነኝ ፡-
ታምሜ ፡ እማልድነው ፡ በሽታ ፡ የሆነኝ ፡-
እሱ ፡ የጠላኝን ፡ ተገኝተሽ ፡ ስትወጂ ፡-
እንቺንም ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ መቅጣቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡-
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
ከልብ ፡ የሚያስማማ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ ጠፍቶ ፡-
ጨነቀኝ ፡ ጠበበኝ ፡ ምን ፡ ላርግ ፡ ይሆን ፡ ከቶ !
እንጀራ ፡ በመሶብ ፡ ጠጅ ፡ በንስራ ፡ ሞልቶ ፡-
ጌትነት ፡ ሲጠራኝ ፡ በሩን ፡ በዋ ፡ አርጎ ፡ ከፍቶ ፡-



ሹመት ፡ ሲለምነኝ ፡ እጆቹን ፡ ዘርግቶ ፡-
ልቤ ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ ስብለ ፡ ላንቺ ፡ አድልቶ ፡-
ጌትነት ፡ ያላንቺ ፡ ከንቱነቱን ፡ አይቶ ፡-
አንቺ ፡ በሌለሽበት ፡ መደሰትን ፡ ጠልቶ ፡-
ወዳጁን ፡ ከሀዲ ፡ እንዳይባል ፡ ፈርቶ ፡-
ሁሉንም ፡ እንቢ ፡ አለ ፡ ድምጹን ፡ አሰምቶ ፡-
ምክረው ፡ እባክሽ ፡ አርፎ ፡ እንዲያሳርፈኝ ፡ ከንቱ ፡ ትግሉን
ትቶ ።
ድል ፡ ከሆኑ ፡ በላይ ፡ መዘረፍ ፡ የማይቀር ፡ መሆኑን ፡ ተረ
ድቶ ፡-
ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ !
ልቤን ፡ ባባብለው ፡ ተጸናናልኝ ፡ ብዬ ፡-
እንቢ ፡ አለኝ ፡ ምን ፡ ላርገው ፡ ንገሪኝ ፡ ስብልዬ ፡-
ካንቺ ፡ ከሚወድሽ ፡ ስለተለያዩ ፡-
ቀን ፡ ከሌት ፡ ያለቅሳል ፡ ይላል ፡ ወዬ ፡ ወዬ ፡
በጦር ፡ እንደወጉት ፡ እዩተሰቀዩ ፡
ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ !
ስብለ ፡ የኔ ፡ ተስፋ ፡ የልቤ ፡ ደስታ ፡
የመንፈሴ ፡ ድጋፍ ፡ ያሳቤ ፡ ጸጥታ ፡
መቸም ፡ ልንገናኝ ፡ አልፈቀደም ፡ ጌታ ፡
ብናለቅስ ፡ ኡ ፡ ብንል ፡ ደረት ፡ ብንመታ ፡-
እንግዴህ ፡ እንተወው ፡ ይከተተው ፡ ዝምታ ፡-
ብቻ ፡ እንዳትረሺ ፡ የፍቅሬን ፡ ትዝታ ፡-
ቀን ፡ ስትቀመጪ ፡ ስትተኚ ፡ ማታ ፡-
እንግዲህ ፡ ደህና ፡ ሁኚ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አይለይሽ ፡ የግዚአብ
ሄር ፡ ርዳታ ፡-
መከፋት ፡ አይንካሽ ፡ የልብ ፡ ቅርታ ፡
ካለሽበት ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ባለሽበት ፡ ቦታ ፡-
ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ !
ለባለድል ፡ ከሆንሽ ፡ እኔ ፡ ስላልታደልሁ ፡-
በደስታ ፡ እንድትኖሪ ፡ እመኝልሻለሁ ፡
እኔ ፡ ግን ፡ ከንግዴህ ፡ ካንቺ ፡ ከተለዩሁ ፡-

ልቤን ፡ ለሌላ ፡ ሴት ፡ እንዳልሰጥ ፡ ምያለሁ ፦
እስኪጠራኝ ፡ ድረስ ፡ በህይወት ፡ እስካለሁ ፦
ከትዝታሽ ፡ ጋራ ፡ ቆርቤ ፡ እኖራለሁ ።
እንግዲህ ፡ ደህና ፡ ሁኝ ! ባያሌው ፡ ደህና ፡ ሁኝ ፡ ሰላም ፡ ብዬሻለሁ !
ወይኔ ፡ ወይኔ ፡ ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ !"

" በዛብህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎቱን ፡ የተወበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድነው ? ደብተራ ፡ መንበሩ !" አሉ ፡ አለቃ ፡ ሰርግው ፡ አንድ ፡ ቀን ።

" ከቤት ፡ ከጠፉ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ስለሆነ ፡ ተማሪው ፡ ሁሉ ፡ መበተን ፡ መጀመሩን ፡ አልሰሙም ? ጌታየ !"

# ምእራፍ ፡ ፴፩ ፡

## ሰርግና ፡ ተዝካር ፡

በዛብህ ፡ ዲማን ፡ ትቶ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ከሄደ ፡ በሁዋላ ፡ ወዲያው ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈረ ፡ ድንበሩ ፡ ሰብለን ፡ አጭተው ፡ ሰርጉ ፡ ለገና ፡ እንዲሆን ፡ ተወሰነ ። ነገር ፡ ግን ፡ በመሀከሉ ፡ ሰብለ ፡ በጽኑ ፡ ታማ ፡ የገናን ፡ አመትባል ፡ ሁሉ ፡ ትተርፍ ፡ አትተርፍ ፡ እዬተባለ ፡ ቤተዘመዱ ፡ ገና ፡ በስጋት ፡ ላይ ፡ ስለነበረ ፡ ለገና ፡ የተቀጠረው ፡ ሰርግ ፡ ወደ ፡ ፋሲካ ፡ ተላለፈ ።

ቀኑ ፡ ሲደርስ ፡ ከሰባት ፡ ወር ፡ በላይ ፡ በዬወገኑ ፡ በዝርዝር ፡ ሲሰናዳ ፡ የኖረው ፡ ድግስን ፡ ድግስ ፡ የሚያሰኘው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እዬሆነ ፡ የመጨረሻ ፡ መልኩን ፡ መያዝ ፡ ጀመረ ። ዳሱ ፡ መሰራት ፡ እንጀራው ፡ መጋገር ፡ ጠጁና ፡ ጠላው ፡ በዬጋኑ ፡ መቅዳት ፡ ወጡ ፡ በያይነቱ ፡ መሰራት ፡ ጀመረ ።

እቤት ፡ ከሚሰናዳው ፡ ሌላ ፡ እንደያቅማቸው ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ በላይ ፡ ፍሪዳ ፡ እያረዱ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ካንድ በላይ ፡ እቆልቁዋይ ፡ የሚይዙ ፡ መሆናቸውን ፡ ያስታወቁ ፡ የፊታውራሪ ፡ መሸሻና ፡ የወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ ባለቁርጥ ፡ ዘመዶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። በዚያ ፡ ላይ ፡ ከነጋዴ ፡ ካወባልና ፡ ከጥላትግን ፡ ከጎንቻና ፡ ከሳር ፡ ምድር ፡ ለደስታው ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆኑ ፡ የተጠሩ ፡ መኳንንትና ፡ ስማቸው ፡ የታወቀ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እንደያቅማቸው ፡ ፍሪዳ ፡ በግ ፡ ማር ፡ ወይም ፡ ቅቤ ፡ ያልሰጡ ፡ ጥቂት ፡ ናቸው ። ፊታውራሪ ፡ የራሳቸው ፡ ሀብት ፡ አልበቃቸው ፡ ብሎ ፡ ከዲማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እዬተበደሩ ፡ የገዙትና ፡ ከዬመኳንንቱ ፡ የተላከላቸው ፡ ፍሪዳና ፡ በግ ፡ በዬመንጋው ፡ ታግዶ ፡ ሲታይ ፡ ብዛቱ ፡ የነጋዴን ፡ የጎንቻንና ፡ የሳር ፡ ምድርን ፡ ያወባልንና ፡ የጥላትግንን ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡